የውርስ ህግና ሕገ-መንግስት

ለወረዳ ዳኞችና
ዓቃብያነ ህጐች የተዘጋጀ የስልጠና ማንዋል

አዘጋጅና አቅራቢ፡-

አሊ መሐመድ አሊ

2000 ዓ.ም

ምዕራፍ አንድ፡- ስለውርስ ህግ በጠቅላላውና የአወራረስ ሥርዓት በኢትዮጵያ

1.1 ስለ ውርስ ህግ በጠቅላላው

1.2 የውርስ ህግ ታሪካዊ አመጣጥና እድገት

1.3 የአወራረስ ሥርዓት በኢትዮጵያ

1.4 የተለያዩ የአወራረስ መኖራቸው ያለው ውጤት

1.5 በሸሪዓ እና የፍትሐብሔር ህጉ ልዩነቶች

ምዕራፍ ሁለት፡- የኢትዮጵያ የውርስ አስተላለፍ በጠቅላላው

2.1 የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አደረጃጀት

2.2 የውርስ መከፈትና በውርስ ስለሚተላለፉ መብትና ግዴታዎች

2.2.1 ውርስ የሚከፈትበት ጊዜና ሥፍራ

2.2.2 ከሟች ሊተላለፉ የሚችሉና ሊተላለፉ የማይችሉ መብትና ግዴታዎች

2.2.3 ስለሟች የውርስ ንብረት ልዩ ድንጋጌዎች

ሀ. የጡረታ ካሳ ክፍያ

ለ. በሞት ጊዜ የሚከፈል የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ

ምዕራፍ ሶስት፡- ለመውረስ የሚያስፈልግ ችሎታ

3.1 ጠቅላላ መግቢያ

3.2 ሟች በሞት በህይወት መኖር

ሀ. የተፀነሰ ልጅ

ለ. የህግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች

ሐ. የአብሮ ሟችዎች ውርስ

3.3 ለወራሽነት ያልተገባ አለመሆን

3.3.1 ወንጀል ፈፅሞ መቀጣት

3.3.2 ሌሎች ለወራሽነት ያልተገነባ ነው የሚያሰኙ ምክንያቶች

ምዕራፍ አራት፡- ሳይናዘዝ የሞተ ሰው የውርስ ሥርዓት አፈፃፀም

4.1 ጠቅላላ መግቢያ

4.2 ያለ ኑዛዜ በሚፈፀም ውርስ ሊካፈሉ የሚችሉ የሥጋ ዘመዶች

ሀ. የሚች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች

ለ. በሁለተኛ ደረጀ የሚጠሩ የሚች ወራሾች

ሐ. ሶስተኛ ደረጃ የሚጠሩ የሚች ወራሾች

መ. በአራተኛ ደረጃ የሚጠሩ የሚች ወራሾች

ምዕራፍ አምስት፡- በሚች ኑዛዜ መሰረት የሚፈፀም ውርስ

5.1 የኑዛዜ ፅንሰ ሀሳብ እድገትና ትርጉም

5.2 የኑዛዜ መሰረታዊ ባህሪያት

5.3 የኑዛዜ ዋጋ መኖር ሁኔታዎች

5.3.1 ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ነገር ሁኔታዎች

5.3.2 በህጉ የተቀመጠው ፎርም አሚልቶ መገኘት

ምዕራፍ አንድ

ስለውርስ ህግ በጠቅላላውና የአወራረስ ስርዓት በኢትዮጵያ

1.1. ስለ ውርስ ህግ በጠቅላላው

“ውርስ” የሚለው ቃል የሥነ ቃልና በተለያዩ ሙያዎች የተለያየ ፍች አለው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ “ውርስ” የሚለው ቃል በመውረስ ያተገኘ ንብረት ዕውቀት፣ ባህልና ሌሎች ነገሮች ለመግለፅ እንጠቀምበታለን፡፡ በህግ ሙያ “ውርስ” የግለሰቦችን የሲቪል መብት በሚደነግጉ የህግ ድንጋጌዎችና በአገሮች መካከል ያለውን ዓለም አቀፍ ግንኙነት ግዴታ ላይ ገብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ስምምት ወይም በልምድ የዳበሩ ህግጋት ውስጥ የተለያየ ተርጓሜ አለው፡፡ እኛ ትኩረት ሰጥተን የምናየው “ውርስ” የሚለው ቃል የግለሰቦችን የሲቨል መብት አስመልክቶ በውስጡ አዝሎ የያዛቸው ፍሬ ጉዳዮች ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ውርስ የሚለው ቃል አንድ ማህበረሰብ የሚች ንብረቶች፣ መብቶችና ግዴታዎች በህይወት ለሚኖሩ ሰዎች ለማስተላለፍ የሚከተላቸውን አሰራሮች ለመግለፅ እንጠቀምበታለን፡፡ “ውርስ” የሚለው ቃል የሚች የሚንቀሣቀሡና የማይንቀሣቀሡ ንብረቶች ጥሬ ገንዘብና በሚች መሞት ምክንያት የማይቋረጡ መብቶችና ግዴታዎች ለወራሾቹ የሚተላለፍበትን አሠራር በአጭሩ ለመግለፅ እንጠቀምበታለን፡፡ የውርስ ህግ የሚለውን ፅንስ ሀሳብ የሚች የሚንቀሣቀሡና የማይንቀሣቀሡ ንብረቶች፣ የአክሲዮን ድርሻዎች ገንዘብና ተከፋይ ብድሮች፣ እዳዎች እና በሚች መሞት ምክንያት የማይቋረጡ የሚች መብቶችና ግዴታዎች ለሚች ወራሾች የሚተላለፍበትን ሥርዓት የውርስ ንብረት አስተዳደርና የውርስ ንብረት አከፋፈልና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን የሚወስኑ ደንቦች የሚይዝ የህግ ማዕቀፍ ለመግለፅ እንጠቀምበታለን፡፡

የሚች ውርስ አወራራስ ሥርዓት የሚወስኑት የውርስ አወራረስ ደንቦች በጥንት ጊዜ እና በዘመናችን በይዘታቸውም ሆነ በአፈፃፀም ሒደታቸው የተለየዩ ናቸው፡፡ ጥንታዊ ሰው ሥራ ላይ የዋላቸው የውርስ ደንቦች ልማዳዊ የውርስ አወራረስ ደንቦች ናቸው፡፡ የማህበረሰቡ አባላት ልማዳዊ የአወራረስ ደንቦችን የሚያከብሩት የሚያመልኩበትን መለኮታዊ ሀይል ስልጣንና ቅጣት በመፍራት ለሚች መንፈስ ክብር በመስጠትና ከማህበረሰቡ የሚደርስባቸውን የማግለል እና ሌሎች እርምጃዎች በመፍራት ነበር፡፡

ልማዳዊ የአወራራስ ደንቦቹን የሚያከበሩት በጉለበትና በሐይል ተፈፃሚ የሚያደርጉ የመንግስት እርምጃና ቅጣት በመፍራት አልነበረም።

አሁን በዓለም ዙሪያ ባሉ አገሮች ታውጀው በሥራ ላይ ያሉ የውረስ ህግጋት በአግባቡ ያተቀረፀ ዝርዝርና ውስብስብ የውርስ አወራራስ ደንቦችን የያዙ ከመሆቸውም በላይ መንግስት ሉአላዊ ስልጣኑን በመጠቀም ተፈፃሚ የሚያደርጋቸው ናቸው።

በዓለማችን እየተሠራባቸው ያሉ ዘመናዊ የውርስ ህግጋት በመሠረታዊነት ሶስት አይነት የአወራረስ ሥርዓቶችን የሚዘረዝሩ የውርስ ደንቦችን የያዙ ናቸው። እነርሡም

- የሟች ውርስ ያለኑዛዜ ለሟች የሥጋና የጋብቻ ዘመዶች የሚፈፀሙበትን የአወራረስ ሥርዓት በዝርዝር የሚደነግጉ፣ ደንቦችን የያዙ (Rules of Interstate Succession)
- የሟች ውርስ በሟች ኑዛዜ መሠረት የሚፈፀምበትን ሥርዓት የሚደነግጉ ደንቦች የያዙ (Rules of testate Succession)
- የሟች ውርስ በሟች ከክፍል ኑዛዜና በከፊል ያለኑዛዜ የሚፈፀምበትን ደንቦች የየዙ (Rules of Painterly intestate and patriarchy Testate secession) የያዙ ናቸው።

በአጠቃላም አሁን እየተሠራባቸው ያሉ የውርስ ህግጋት የሟች የሚንቀሣቀሥ እና የማይንቀሣቀሥ ንብረት ገንዘብና ከሌሎች ስዎች የሚሰበሰብ ብድር ወይም ተከፋይ ገንዘብ የአክስዮን ድርሻና ሌሎች በሟች መሞት ምክንያት የማይቋረጡ የሟች መብትቻና ግዴታዎች ለሟች ወራሾች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚተላለፍበትን የአወራረስ ሥርዓት የሚደነግጉ ናቸው። የውርስ ህግ መሠረታዊ ግብ ይኸ ብቻ ነው ብለው ያስባሉ?

1.2. የውርስ ህግ ታሪካዊ አመጣጥና እድገት

የውርስ ህግ ሟችን የአወራረስ ሥርዓት ግዥር የሆኑ ደንቦችን የያዘ የህግ ክፍል እንደሆነ በላይ ተገለፆል። ሆኖም ስለ ውርስ ህግ መሠረታዊ ግብ ለመረዳት

- በሰው ልጅ ማህበራዊ እድገት ውሰጥ የውርስ ህግ አስፈላጊነት የመነጋገሪያ አጀንዳ መሆን የጀመረው መቼ ነው?
- ለውርስ ህግ ደንቦችን መፈጠርና እድገት መሠረታዊ የሆነው ምክንያት ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመርመር ያሰፈልጋል።

የሰው ልጅ ከክርስቶስ ልደት በፊት ረዥም ዘመናት ቀደም ብሎ የአወራራስ ሥርዓትን የሚደነግጉ የውርስ ደንቦች ሥራ ላይ ማዋል እንደጀመረ በርካታ ጥናቶች ያረጋግጣሉ። አንዳንዶች ስለሚች የአወራረስ ሥርዓት የሰው ልጅ አውጥቶ ተፈፃሚ ያደረጋቸው የውርስ ደንቦች የሰውን ልጅ ጥንታዊ ስልጣኔ ያህል እደሜ ያስቆጠሩ ናቸው በማለት ይገልፃሉ። የሰው ልጅ በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ማህበር በነበረበት ዘመን የውረስ ህግ ድንጋጌዎች አልነበሩም። ምክንያቱም ንብረቱ የቤተሠብ ወይም የማህበረሰቡ የውል ባለቤትነት የያዘ በመሆኑ ሚች መሞት ምክንያት ያለ ባለቤት የሚቀር ሀብት ስለነበረ ነው። አንድ ሰው ሲሞት የሚች ንብረት የአወራረስ ሥርዓት ቁልፍ የማህበረሰብ ችግር አንገብጋቢ የመወያያ አጀንዳ መሆን የጀመረው የውል ንብረት ባለቤትነት እያከሰመ ሄዶ የግል ንብረት ባለቤትነት ማቆጥቆጥ ከጀመረ በኃላ ነው፡ የግል ንብረት ባለቤትነት ሲያቆጠቁጥ ግለሰቦች የተለያዩ የሚንቀሣቀሡና የማይቀሣቀሡ ንብረት ባለቤት ሆኑ። ስለሆነም አንድ ሰው ከሞት በላይ ንብረቱ ለማን ሊተላለፍ ይገባል?

- የሚችን ንብረት በቀዳሚነት የመውረስ መብት ያለው ማን ነው?
- ሚች ከአንድ በላይ የሆኑ ወራሾች ካሉት ደግሞ እያንዳንዳቸው የሚች ወራሾች ከሚች ንብረት ምን ያህል ሊደርሳቸው ይገባል?
- ሚች በህይወት ዘመኑ የተበደረውና እዳ እንዴትና በማን ለሚች አበዳሪዎች ይከፈላል?
- ሚች በህይወት ዘመኑ ያበደረውና ያልሰበሰበውን ተከፋይ ገንዘብ የሚች ተበዳሪዎች እንዴትና በምን ሁኔታ እንዲከፍሉ ማድረግ ይቻላል? የሚሉትና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በማህበረሰቡን ሠላማዊ ኑሮና ግኑኝነት ማወክ ጀመሩ። ስለሆኑም ጥንናታዊው ማህበረሰብ አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ ያካበተው ሀብት በሰላማዊ መንገድ በህይወት ለሚኖሩ ወራሾቹ የሚተላለፉበትን መላና ዘዴ በማፈላለግ የሚች የአወራረስ ሥርዓት የሚደነግጉ ደንቦችን ማዳበርና ሥራ ላይ ማዋል ጀመሩ። የውርስ ህግ መፍጠር መሠረታዊ ምክንያት የግል ንብረት ባለቤትነት ማቆጥቆጥና ማደግ ሲሆን የውርስ ህግና የግል ንብረት ባለቤትነት ያጠበቀ ቁርኝትና ተያያዥነት ያላቸው ናቸው።

በርካታ ጥናቶች እንደተረጋገጠው ጥንታዊ ማህበረሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ የዳበረውና ሥራ ላይ የዋለው የአወራረስ ሥርዓት መወለድን ማለትም የዘር

ሀረግንና የሥጋ ዝምድናን መሠረት ያደረገ የአወራረስ ሥርዓት ነው። ይኸውም የአወራረሥ ሥርዓት ሚች በህይወት ዘመኑ ያጠራቀመው ሀብት ለማን ሊተላለፍ እንደሚገባ በኑዛዜ ወይም በሌላ መንገድ እንዲወስን እድል የሚሰጥ አልነበረም። ይልቁንም የሚች የመጨረሻ ቃልና ፍላጎት ከግምት ውስጥ ማያስገባ የሚችን ወራሾች ለእርሱ ባለቸው የሥጋ ዝምድና ቅርበት መሠረት በማድረግ እንዲወርሡ ይፈቅድ ነበር።

የሚች ውርስ ሚች ከመሞቱ በፊት በተናገረው ቃልና ትዕዛዝ መሠረት ለወራሾች የሚተላለፍበት የአወራረስ ሥርዓት ዘርንና መወለድን መሠረት አድርጎ ይፈፀም የነበረው የአወራረስ ሥርዓት ሥራ ላይ ከዋለ ከብዙ ዘመን በኋላ አንደሆነ በመስኩ ያደረጉት ጥናቶች ያሣያሉ። የሚችን ኑዛዜ መሠረት በማድረግ የሚችን ውርስ ለማስፈፀም የሚያሰችል ደንቦች መደንገግና ማዳበር አይነተኛው ምክንያት የዘር ሀረግንና መወለድን ብቻ መሠረት በማድረግ ማህበረሰቡ ያከናውነው የነበረው የአወራረስ ሥርዓት ኃላ ቀርና ያልዳበሩና ሚች በሞት ሲለይ ንብረቱ ለማን ቢተላለፍለት እንደሚፈልግ ያለውን ፈቃድና ፍላጎት ከግምት ውስጥ የማያስገቡ አስገዳጅ የነበሩ መሆናቸው ነው። የዘር ሀረግንና መወለድን መሠረት በማድረግ ብቻ የሚች አወራረስ የሚደነግጉት ጥንታዊ የአወራረስ ደንቦች የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ በንብረት ላይ ለማዘዝ የነበረውን ፍላጎትና መብት ዕውቅና የማይሰጡ ከዚህ መሠረታዊ ፍላጎትና ስሜት በሚቃረን መንገድ አስገዳጅ ሆነው የተደነገጉና በርካታ ጉድለቶች የነበሩባቸው ነበሩ። የዘር ሀረግንና መውረስን መሠረት ያደረጉት የአወራረስ ደንቦች የሚችን ወራሾች በእድሜዓቸው በፆታቸውና በሌሎች ምክንያቶች ልዩነት የሚፈጥሩ መሆናቸውን ጥንታዊውን እንግሊዝ የውርስ ህግና የዳግማዊያን የውርስ ህግ ደንቦች በመርመር ለመረዳት ይቻላል። ሰለሆነም መወለድን መሠራት በማድረግ የሚችን አወራረስ ሥርዓት ለማስፈፀም ጥንታዊ ማህበረሰቦች ሥራ ላይ የዋሉት የአወራረስ ደንብ

- የሚች የቅርብ የሥጋ ዘመዶች የወገኑ ሚች በህይወት እያለ በህይወቱ ሥኬታማ እንዳይሆን በተለያየ መንገድ በደል ሲፈፅሙበት ያኖሩትን ዘመዶቹ ሚች ሲሞት ዝምድናቸውን በመቁጠር ብቻ የሚች ወራሽ የሚያደርግና የሚችን ንብረት እንዲከፍሉ የሚያደርጉ በመሆኑ፣

- በሚች የሥጋ ዝምድና የሌላቸው ነገር ግን ሚችን በህይወት ዘመኑ ደስተኛና ስኬታማ እንደሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ሰዎች ሚች ንብረቱን ሊያስተላልፍላቸው ቢፈልግ እንኳን ይህንን የማይፈቅድና የሚች የዋጋ ዘመዶች ባለመሆናቸው ብቻ የሚች ወዳጆችና ባለውለታዎች በሚች ፍቃድና ፍላጎት ከንብረቱ እንዲካፈሉ የማይፈቅድ ከልካይና አስገዳጅ የነበረ በመሆኑ፣
- ሚች ከሥጋ ዘመዶቹ መካከል የበለጠ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ለመለየት ከንብረቱ ከፍ ያለውን ድርሻ እንዲወሰድ ለማድረግ ለሚች ፍቃድና ፍላጎት ዋጋ የማይሰጥና ሚች ከሞተ በኃላ የንብረቱን አወራረስ ለመቆጣጠርና ለመወሰን ያለውን ፍላጎትና ምኞች ዕውቅና የማይሰጥ ገደብና አስገዳጅ መሆኑ፣ ማህበረሰብ ቀስ በቀስ የሚች ሚስት በሚች ኑዛዜ መሠረት የሚፈፅሙበትን የአወራረስ ሥርዓት ለማዳበር አይነተኛ ምክንያት መሆኑን በመስኩ ጥናት ያደረጉ ሙሁራን በርካታ አብነቶችን በማንሣት ይገልፃሉ፡፡ ይኸም ሆኖ የሚችን ውርስ በሚች ኑዛዜ መሠረት የሚፈፀምበትን የአወራረስ ደንቦች የሰው ልጅ ሥራ ላይ ማዋል የጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት ብዙ ዘመናት ቀደም ብሎ እንደሆነ ጥንታዊ ግብኦች ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ2900 — 2750 ዓመት ዓለም ሥራ ላይ የዋሉት የነበረውን የሀምራቢ ህግ እና የጥንታዊ ግሪኮችን የሳሎን ህግ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ የሰው ልጅ የምርት ማምረቻ መሣሪያዎችን እያሻሻለ በመጠቀም ለዕለት ፍጆታው ከሚያስፈልገው በላይ ተረፈ ምርት ማምረትና የግል ንብረት ባለቤት መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀመሮ የውርስ አወራረስ ሥርዓት ደንቦችን ሥራ ላይ ለማዋልና በየጊዜው በማሻሻል አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ማህበረሰብ በመጀመሪያው ወቅት የዘር ትስስርና የዝምድና ሀረግን ብቻ መሠረት ያደረጉ የውርስ አወራረስ ደንቦች በኃላ ደግሞ የሚችን ፈቃድና ፍላጎት ማለትም የሚችን ኑዛዜ መሠረት በማድረግ የሚችን ውርስ የሚያስተላልፍበት የአወራረስ ሥርዓት ደንቦች በየደረጃው ከሚያጋጥሙት ነባራዊ ዕውነታና ችግር ለመፍታት በሚያስችለው መንገድ እያሻሻለ ሥራ ላይ ሲያውሉ የኖረ የህግ ክፍል ነው፡፡

የውርስ ህግ ታሪካዊ አመጣጥና እድገት ማየት መሠረታዊ ፋይዳ የውርስ ህግ እጅግ በጣም ብዙ ዘመናትን ያስቆጠረና የህግ ክፍል መሆኑን ማሣያት አይደለም። በአንዳሩ የሰው ልጅ የንብረት ባለቤትነት መብት ወስንና አድማስ እስከ ምን ድረስ መሆን አለበት? አንድ ሰው ከሞተ በኃላ ንብረቱ ለማንና እንዴት መተላለፍ እንዳለበትና ለምን አይነት ግልጋሎት ሊውል እንደሚገባ የመቆጣጠርና የመወሰን መብቱ ህጋዊ ዕውቅና እና ጥበቃ ሊሰጠው ይገባል ወይስ አይገባም የሚሉትን ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ መሠረታዊ ምላሽ መስጠት የተደነገገ የህግ ክፍል መሆኑን ለማሣያት ነው። የውርስ ህግ የሰው ልጅ ስልጣኔ ያህል የኖረ እድሜ ጠገብ የህግ ክፍል ከመሆኑ በተጨማሪ በዘመናችን ስሜታዊው ፈጣን የቴክኖሎጅ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ለማፋጠን በቁልፍ መሣሪያነት ከሚያገለግሉት የተለያዩ የህግ ክፍሎች አንደኛው በመሆኑ ነው።

አንድ ሰው እሱ ከሞተ በኃላ ስለ ንብረቱ ሁኔታ የመወሰን ተፈጥሯአዊና ህግ መንግስታዊ መብት አለው ከለው ያስባሉ? ለምን?

1.3. የአወራረስ ሥርዓት በኢትዮጵያ

የውርስ ህግ አወጣጥና እድገት ከግል ንብረት አመጣጥና እድገት ጋር የጠበቀ ግኑኝነት እንዳለው ከላይ ተገልፆል። ከዚህ መሠረታዊ ነጥብ ተነስተን በኢትዮጵያ የገበሬውንና አሁን ያለውን የአወራረስ ሥርዓት ስንመረምር፣ በፊትም ጊዜ ሆነ አሁን፣ አገሪቱ አንድ የወጥ የሆነ የአወራረሥ ሥርዓት የውርስ ደንቦች የሌሏት መሆኑን ለመረዳት ይችላል። ኢትዮጵያ የተለያዩ ማህበረሰቦች ባህልና ልማዳዊ ደንቦች፣ የተለያዩ ሀይማኖቶች የአወራረስ ደንቦችና በዘመናዊ መልክ የተቀረፅ የፍትሐብሔር ህግ የውርስ ደንቦች ጎንበጎን ተፈፃሚ ለማድረግ በተለያዩና በርካታ የሚች ውርስ አወራረስ ሥርዓቶች ዕውቅና የሰጠች አገር ናት።

በኢትዮጵያ ሲሠራባቸው የኖሩና እየተሠራባቸው ያሉ የሚች ውርስ አወራረስ ደንቦች በሶስት የተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች አንፃር መመርመር ይቻላል። እነርሡም

- 1952 የፍትሐብሔር ህጉ ከመውጣቱ በፊት የሚች ውርስ የአወራረስ ሥርዓት ላይ ተፈፃሚነት የነበራቸው የውርስ ደንቦች
- 1952 ዓ.ም የፍትሐብሔር ህጉ ከጣ በኃላ እስከ ነሐሴ1987 ተፈፃሚነት የነበራቸው የውርስ አወራረስ ደንቦችና
- ከነሐሴ ወር 1987 ዓ.ም በኃላ በአገሪቱ እየተሠራባቸው ያሉ የአወራረስ ሥርዓቶች ናቸው።

ሀ. የመጀመሪያውን በተመለከተ፣ 1952 ዓ.ም የፍትሐብሔር ህጉ ከመውጣቱ በፊት በአገሪቱ፣ የሚች ውርስ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ልምድና ባህላዊ ደንቦች፣ የክርስትና ሀይማኖት ተፅዕኖ ያለበትን የፍትሐነገስት ድንጋጌዎች እና የሼሪዓ ህገን መሠረት በማድረግ የሚፈፀሙ፣ የተለያየ ይዘት ባህሪና ውጤት የነበራቸው የውርስ አወራረስ ሥርዓቶች እንደነበሩ በዚህ መስብ የተጠኑ ጥናቶች ያሣያል። ስለዚህ የፍትሐብሔር ህጉ ፀድቆ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ባህላዊና ልማዳዊ የአወራረስ ደንቦች፣ የፍትሐነገስቱ የአወራረስ ደንቦች እና የሼሪዓ የአወራረስ ደንቦች ጎንበጎን ይሠራባቸውና ህጋዊ ውጤትም የነበራቸው መሆኑን እንረዳለን።

ለ. ህግ አውጭው የፍትሐብሔር ህጉን ስያውጅ፣ በአገሪቱ አንድና ወጥ የሆነ የአወራረስ ሥርዓትና የውርስ ህግ እንዲኖር በማሰብ ስለውርስ ዝርዝር ድንጋጌዎችን አውጇል። ህግ አውጪም በአገሪቱ ያሉ የውርስ አወራረስ ሥርዓቶች በፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ድንጋጌዎች ብቻ የማስፈፀም ፍላጎት የነበረው መሆኑን፣ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3347 አንቀፅ 1 ግልፅ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር በዚህ በፍትሐብሔር ህግ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮች ከዚህ በፊት በልምድ ወይም ተፅፈው ይሠራባቸው የነበሩ ደንቦች ሁሉ በፍትሐብሔር ህግ ስለተተካ ተሽረዋል በማለት በግልፅ በማስቀመጥ፣ የውርስ አወራረስ አስመልክቶ ሲሠራባቸው የነበሩ፣ ልማዳዊ ደንቦች ሀይማኖታዊ ህግጋትና የተሻሩና በፍትሐብሔር ህጉ የተተኩ መሆኑን አውጇል። በወቅቱ የነበረው ህግ አውጭ አንድ ወጥነትና ተፈፃሚነት ያለው አንድ የውርስ ህግ እንዲኖር በማሰብ አንድ የአወራረስ ሥርዓት ለማስፈን የምክረ ቢሆንም ይህንን ህግ ተግባራዊ ለማድረግ አልቻለም።

ምክንያቱም የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች በሁሉም ማህበረሰብ ተቀባይነት አለማግኘታቸውና የተለያዩ ማህበረሰቦች የፍትሐብሔር ህጉ ከመጣ በኃላ ባህላቸውንና ልማዳዊ የአወራረስ ደንቦቻቸውን መሠረት በማድረግ የሚችን የአወራረስ ሥርዓት ተፈፃሚ ማድረግ መቀጠላቸው መንግስቱም የፍትሐብሔር ህጉን ከዳር እስከዳር ተፈፃሚ ለማድረግ አቅም ያልነበረው በመሆኑና

- በአዋጅ ቁጥር 62/1936 የተቋቋሙት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሙስሊሙ ህብረተሰብ ባቀረበው አቤቱታ መሠረት የፍትሐብሔር ህጉ ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለ በኃላ በሸሪዓ መሠረት የሙስሊሙን ህብረተሰብ የጋብቻ፣ የልጆች አስተዳደግ፣ የዋቅፍ ስጦታና የውርስ ጉዳይ ዳኝነት ማየታቸውን እንዲቀጥሉ በፍትህ ሚኒስትር በተፃፈ ደብዳቤ መሠረት ሥራቸውን ያለማቋረጥ በመቀጠላቸውን ስናይ ህግ አውጭ አንድ ወጥ የውርስ አወራረስ ሥርዓት ለመዘርጋት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3347 ንዑስ አንቀፅ 1 ያወጀው ግልፅ ድንጋጌ፣ ምንም አይነት ተግባሪዊ ለውጥ አላስከተለም፡፡ ስለሆነም 1952 ዓ.ም የኢ.ፊ.ድ.ሪ. ህገ መንግስት ሥራ ላይ እስከዋለበት ነሐሴ 1987 ዓ.ም ድረስ፣ በኢትዮጵያ የሚች ውርስ ልማዳዊ የውርስ ደንቦችን፣ የሸሪዓ የውርስ ደንቦችንና የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ድንጎጌዎች መሠረት በማድረግ ስፈፀም የቆየ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

ሰለዚህ ሁለተኛው የኢትዮጵያ የአወራረስ ሥርዓት ዘመን መንግስት በግልፅ ድንጋጌ በፍትሐበሔር ህጉ የውርስ ህግ ደንቦች ውጭ ያሉትን ልማዳዊና ሀይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች የሻረበትና ዕውቅና ያነሣበት በተግባር ግን የሚች ውርስ ባህላዊና ልማዳዊ ደንቦች በሸሪዓ እና የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች ሲፈፀም የኖረበት የእድገት ደርጃ እንደሆነ ለማየት ይቻላል፡፡ ይኸ ዘመን ህግ አውጭው በመርህ ደረጃ ያወጀው ድንጋጌ በንድፍ ሀሳብ ብቻ ሆኖ የቀረበት ህብረተሰቡ ደግሞ ልማዳዊና ሀይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦችን ተግባራዊ በማድረግ በህግ አውጭው አንድና ወጥ የሆነ የአወራራስ ሥርዓት የመዘርጋት ፍላጎት ማህበራዊ ተቀባይነትና ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን በተግባር የሚየበት ዘመን ነው፡፡

ሐ) ስለ ኢትዮጵያ የአወራራሽ ስርዓት ስናነሳ በሶስተኛ ደረጃ የሚታየው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ፀድቆ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ያለው፣ የአወራረስ ስርዓት ነው። ህገ መንግስቱ የግል መብቶችን በተለከተ የሚነሱ ክርክሮች በተከራካሪዎቹ ፈቃድ በባህላዊ ወይም ኃይማኖታዊ ፍርድ ቤት የመዳኘት መብትን በአንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 ደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤትና የክልል ምክርቤት ለህገመንግስቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የሀይማኖት እና የባህል ፍርድቤቶችን ሊያቋቁሙ ወይም ዕውቅና ሊሰጡ እንደሚችሉ ከመደንገጉም በላይ ህገመንግስቱ ከመጽደቁ በፊት ዕውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ የኃይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶች በህገመንግስቱ መሰረት በአንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 5 በግልጽ ደንግጓል። በዚህ መሰረት፣ የፌዴራል ሼሪዓ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 188/1992 መሠረት ተጠናክሮ ስራውን የቀጠለ ሲሆን ክልሎችን የክልል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን የማጠናከሪያ አዋጆችን በማወጅ ስራቸውን እንዲቀጥሉ አድርገዋል።

ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለበት ነሐሴ 1 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ባህላዊና ልማዳዊ የአወራረስ ደንቦች፣ ሀይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች ህገ መንግስታዊ ዕውቅናና ጥበቃ አግኝተው ከፍታብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች ጐንበጐን እየተተገበሩ ይገኛሉ። ስለዚህ አሁን ያለው የአወራረስ ስርዓቶች ስንመለከት ሁለት መሠረታዊ እና ልዩ ባህሪያት ያሉት ነው። የመጀመሪያው በእኩል ደረጃ ህገመንግስታዊ ዕውቅናና ጥበቃ በተሰጣቸው

- ባሕላዊና ልማዳዊ የውርስ አወራረስ ደንቦች
- ሀይማኖታዊ የውርስ አወራረስ ደንቦችና
- በፍታብሔር ህጉ የውርስ ድንጋጌዎች መሠረት የማፈፀሙ

የተለያዩ አይነት ባህሪ እና ውጤት ያላቸው የአወራረስ ሥርአቶች በአገሪቱ ውስጥ ተግባራዊ እየሆኑ መሆናቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው በሚች የውርስ አወራረስ ሒደት ሥርዓት ሲፈፀም የሚነሱ ክርክሮች ተፈፃሚነት ያላቸውን የአወራረስ ደንቦች የመምረጥ መብት ሙሉ በሙሉ የተከራካሪዎች መሆኑ ነው። እዚህ ላይ መታየት ያለበት ከተከራካሪዎቹ አንደኛው በልማዳዊ ወይም ሀይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች መሰረት

ለመዳኘት ፈቃደኛ ካልሆነ ጉዳዩ በፍታብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚፈፀም መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡- ስለሆነም ዜጐች የፍታብሔር ህጉን የውርስ ደንቦች ተፈፃሚነት የሚያስቀሩት ጉዳዩ በባህላዊ ወይም ኃይማኖታዊ የአወራረስ ደንብ እንዲፈፀም ሙሉ በሙሉ ሲስማሙና ፈቃደኛ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡

1.4 የተለያየ አይነትና ባሕሪያት ውጤት ያላቸው የውርስ አወራረስ ደንቦች መኖራቸው ያለው ጠንካራና ደካማ ጐን

ከላይ እንደተገለፀው በአገሪቱ አንድ ወጥ የሆነ የአወራረስ ሥርዓት ኖሮ የማያውቅ ሲሆን አንድና ወጥነት ያለው የአወራረስ ሥርዓት ለመዘርጋት የተደረገው ሙከራም ተግባራዊ ውጤት አላስገኘም፡፡ ይህም በመሆኑና ህገመንግስቱ ባህልን፣ ሃይማኖትን መሰረት ለሚያደርጉ የአወራረስ ደንቦች ዕውቅናና ጥበቃ ሰጥቷል፡፡ ይህም ዜጐች በፈቃዳቸውና በፍላጎታቸው የህብረተሰባቸው ባህላዊ የውርስ ደንቦች ወይም ኃይማኖታዊ የውርስ ድንጋጌዎች መሰረት የሚች ውርስ የሚያስፈፅሙበት እድል የሚሰጥ በመሆኑ፣ ዜጐች የግል ጉዳያቸው በመረጡት መንገድ የመጠየቅና የመዳኘት መብታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ይህም ሊመሰገን የሚገባው ጠንካራ ጎን እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ከአንድ በላይ የሆኑ የውርስ አወራረስ ስርዓቶች በአንዲት አገር ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞከር የአንዱ የአወራረስ ሥርዓት ደንቦች ከሌላው የሚለያዩበት ሰፊ ሁኔታ ስለሚኖርና ከሚች ወራሾች መካከል የተወሰኑትን በአንደኛው የአወራረስ ስርዓት ሌሎቹ ደግሞ በሌላ የአወራረስ ሥርዓት መሰረት የሚች ውርስ እንዲፈፀም ለማድረግ የየበኩላቸውን ጥያቄ ስለሚያቀርቡና በሌሎች ምክንያቶች የሚፈጠረው የተለያዩ የውርስ ደንቦችና የአፈፃፀም ግጭት ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮች አሉ፡፡ በኢትዮጵያ ተፈፃሚነት ያላቸው ባህላዊ የአወራረስ ሥርዓቶች ብዛታቸውን፣ ይዘታቸውን የሚያስችል ወጥ ጥናት ባለመደረጉ በእርግጠኝነት ብዛታቸውን፣ ይዘታቸውንና የአፈፃፀም ሒደታቸውን ከሌሎች ኃይማኖታዊና የፍታብሔር ህግ የውርስ ድንጋጌዎች ጋር በማነፃፀር ለመግለጽ አይቻልም፡፡ ሆኖም የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ጎሳዎችና ማህበረሰቦች የየራሳቸው ባህላዊ የውርስ አወራረስ ደንቦች እንዳላቸውና እነዚህም በይዘትም ሆነ በአፈፃፀም የተለያየ ይዘትና በህሪ እንዳላቸው በተለያየ ጊዜ ከተደረጉ አጫጭር የዳሰሳ ጥናቶች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም በኢትዮጵያ ተግባራዊ እየሆኑ ባሉ የባህል አወራረስ ደንቦች መካከል ያለው ልዩነትና አንድነት እንደዚሁም እያንዳንዱ ባህላዊ የውርስ አወራረስ ሥርዓት እየተሰራባቸው ካሉት የፍትሐብሔር ህጉ እና የሸሪዓ የውርስ ድንጋጌዎች ያላቸውን አንድነት እና ልዩነት በንጽጽር ለማቅረብ አይቻልም። በአንጻሩ ጐን በጎን የሚተረጉሟቸው እና የሚያስፈጽሟቸው ፍርድ ቤቶች ተቋቁመው እየተሰራባቸው ባሉት የፍትሐብሔር ሕግ የውርስ ደንቦችና በሸሪዓ የውርስ ደንቦች መካከል ያለውን መሰረታዊ የይዘት ልዩነትም በአፈፃፀም ሒደት እየተከሰቱ ያሉ መሠረታዊ ችግሮች ማየት በአገራችን የተለያዩ ባህላዊ ኃይማኖታዊና የፍትሐብሔር ህግ የተደነገገውን የአወራረስ ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ሒደት ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች ለመረዳት ጠቀሜታ ስለሚኖረው በአጭሩ ማየት ይጠይቃል።

4.1.1. የሸሪዓና የፍትሐብሔር የውርስ ደንቦች መካከል የሚታየው መሠረታዊ ልዩነትና በአፈፃፀም የሚታዩ ችግሮች

ሀ) በሸሪዓና በፍትሐብሔር ህጉ መሰረታዊ የፖሊሲ ሐሳብ ልዩነቶች የሸሪዓም ሆነ የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ደንቦች መሰረታዊ ግብ የሚችን ውርስ ለወራሾቹ ማስተላለፍ ቢሆኑም በይዘታቸው አንድ አንድ መሰረታዊ ልዩነቶች አሏቸው። ይህም ልዩነት ሁለቱ ህግጋት መካከል የተካተቱ የፖሊሲ ሀሳብ ልዩነት ነፀብራቅ ነው። ከልዩነቶቹ ጥቂቶቹን ስንመለከት፣

- የፍትሐብሔር ሕጉ የሚች ወራሾች ከሚች በሀይማኖትና በእምነት መለየታቸው የወራሽነት መብታቸውን አያሳጣቸውም። በሌላ በኩል ሚች ሙስሊም ከሆነ የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ያልሆኑ ወራሻቹ በሚች ውርስ እንዳይሳተፉ የሸሪዓ የውርስ ደንቦች ይከለክላሉ።
- የፍትሐብሔር ህጉ የሚች ሴትና ወንድ ወራሾች በጾታቸው ምክንያት የተለያየ ድርሻ እንዲወስዱ አያስገድድም። በእኩል የዝምድና ደረጃ እስካላቸው ድረስ እኩል ድርሻ ያገኛሉ። በሸሪዓ የሚች ሴት ልጆች ከሚች ውርስ አንድ ሶስተኛ የሚሰጣቸው ሲሆን ወንዶች ሁለት ሶስተኛ ይወስዳሉ።
- በሸሪዓ ሚስት ባሏን የመውረስ መብት ያላትና ከባሏ ውርስ አንድ ስምንተኛ የማግኘት መብት ያላት ሲሆን በፍትሐብሔር ህግ መሰረት ሚስት ባሏን የመውረስ መብት የላትም።

- የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ ሚች ከወራሾቹ አንዱን በኑዛዜ የመንቀል መብት ያለው መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን በሸሪዓ ሚች ወራሾቹን በኑዛዜ የመንቀል መብት የለውም፡፡
- በፍትሐብሔር ህጉ ሚች በኑዛዜ ንብረቱን ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ መብት ያለው ሲሆን በሸሪዓ አንድ ሰው በኑዛዜ ሊያስተላልፍ የሚችለው የንብረቱን አንድ ሶስተኛ ብቻ ነው፡፡

ለ) በአፈፃፀም የሚታዩ ችግሮች

በሁለቱ ህጐች መካከል ያሉት እነዚህ እና ሌሎች መሰረታዊ ልዩነቶች ሚች ሙስሊም በሆነ ጊዜና የሚች ወራሾች የሌላ ኃይማኖት ተከታይ ወይም ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ በሆኑ ጊዜ ወይም ሚች በጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታና ነጠላ የኑዛዜ ስጦታ ንብረቱን ባከፋፈለ ጊዜ በሸሪአ ተጠቃሚ የሚሆኑት ወራሾቹ በሸሪዓ መሠረት ውርሱ እንዲፈፀም ሌሎች ደግሞ በፍትሐብሔር ህጉ መሰረት ታይቶ እንዲወሰን በየበኩላቸው የወራሽነት ማረጋገጫ ለማግኘትና ውርሱን ለመካፈል ክስ የሚያቀርቡበትና የአንድ ሰው ውርስ ጎን በጎን በሁለት ፍርድ ቤቶች የሚታይበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 5 ይህንን ችግር ዘለቄታ መፍትሔ ለመስጠት ታስቦ የተደነገገ ሲሆን ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ለማጠናከር አዋጅ ቁጥር 188/1992 ታውጇል፡፡ በተለያዩ ክልሎችም የክልል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጆች ታውጀዋል፡፡ እነዚህ የህግ ማዕቀፎች ከመውጣታቸው በፊት የነበሩ በርካታ ችግሮችን ለመፍታት እንዲረዱ የሚስተባበል ባይሆንም አሁንም ቢሆን

- በህግ ማዕቀፎቹ ድንጋጌዎች ግልፅ አለመሆንና በአንድ አንድ ጉዳዮች ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ የተነሳና
- መደበኛው ፍርድ ቤት እና የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ህግን በመተርጎምና በማስፈፀም ሒደት የየራሳቸው ችግር ያለባቸው በመሆኑ

ሁለቱን የውርስ ህግጋት በማስፈፀም በኩል በርካታ ችግሮች እንደሚፈጠሩና ችግሮቹ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አልፈው የህገመንግስት አጣሪ ጉባኤና የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመነጋገሪያ አጀንዳ እየሆኑ መሆኑን አንድ አንድ ጉዳዮችን አንስቶ ማየት ይቻላል፡፡

በዚህ በኩል በህግ አተረጓጎምና አፈፃፀም ያሉ ችግሮችን ለመረዳት

- በአንሻ መሐመድና ከድጃ በሽራ
- በወ/ሮ ፈንታየ መሐመድና ወ/ሮ እናትነሽ ከተማ መካከል የተደረጉ ክርክሮችንና በየደረጃው የተሰጡ ውሳኔዎች መመርመሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ በአገራችን እየተሰራባቸው ያሉ በርካታ ባህላዊና ኃይማኖታዊ የአወራረስ ሥርዓቶች ከፍትሐብሔር ህጉ የአወራረስ ደንቦች ጋር ጎን በጎን ሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ የሚከሰቱትን ችግሮች መሰረታዊ ባህሪ ችግሮቹ የሚፈቱበትን የህግ አግባብ በመረዳት ለተግባራዊ እንቅስቃሴ ዝግጁ ለመሆን ስልጠናዎች በአካባቢያችን ያሉትን ባህላዊ ኃይማኖታዊ የአወራረስ ሥርዓቶች መሰረታዊ ደንቦች እና የአፈፃፀም ሥርዓት ላይ ስልጣኖቹ በየአካባቢያቸው የዳሰሳ ጥናት በማድረግ በጥናቱ ግኝት ላይ የጋራ ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግ የላቀ ጠቀሜታ ስላለው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነጥብ ነው፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የአንዲት አገር ፖሊሲና ስትራቴጂ በውርስ ህግ ውስጥ የሚካተትበትና የሚንፀባረቅበት አግባብ አለ ብለው ያስባሉ? እንዴት?
2. የውርስ ህግ አንድ ሰው በህይወት በነበረበት ጊዜ ያለው የንብረት ባለቤት የመሆን መብት ከሞት ከተለየም በኋላ ተፈፃሚነት የሚያደርግ ከንብረት ባለቤትነት መብት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ የህግ ክፍል እንደሆነ የሚገልፁ ጸሐፊዎች አሉ፡፡ የውርስ ህግ መሠረታዊ ግብና ዓላማ ምንድን ነው?
3. የሚች ውርስን በማስፈፀም በኩል በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተቋቋሙ መደበኛ ፍርድ ቤቶችና በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ላይ የተጣለ የህግ ገደብ አለ ብለው ያስባሉ? ለምን?
4. ባህላዊ የአወራረስ ደንቦች ኃይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች እና የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ደንቦች ጎን በጎን ሥራ ላይ መዋላቸው ምን አይነት ጠቀሜታ እና ጉዳት ይኖራቸዋል ብለው ያስባሉ? ያብራሩ፡፡
5. አንድ ሙስሊም ወንድ ከዚህ ዓለም በሞት ይለያል፡፡ የሚች ሚስት በሸሪዓ መሠረት ሚች ያገባት ህጋዊ ሚስት መሆኗን አጣርቶ ማስረጃ እንዲሰጣት በአካባቢዋ ላለው የናኪባ ፍርድ ማመልከቻ ታቀርባለች፡፡ ይህ ማለት የጋራ ንብረት አከፋፈል በሸሪዓ መጣራት እንዲከናወን በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ሰጥታለች ማለት ነውን? ለምን?

6. ወ/ሮ ጸታ ዑመር አ ሰማት አበ ዝ በሸሪዓ ሕ መሠረፔ ተ ብተው ሃቨ ዓመፔ ጸ ሩ በኂላ ባልባው በዚህ ዓመፔ በሞፔ ቭለቨል። በዚህ ወቅፔ ሴፔቮዋ በሸሪዓ መሠረፔ ጸሚኖ ር ብኖ ወኮማ ባቹረኖ ባሚኖ ሕ ዊ ሚስፔ መሆ፟ት ለማረ ጎ ለሸሪዓ ምርታ ቤፔ አቤቱ አቅርባ ሸሪዓ በሚወቅተው መሠረፔ ባተ ባኖ ባሚኖ ሚስፔ መሆ፟ት ባሚቨረ ጎ ማስረ ባሸሪዓ ምርታ ቤፔ ቭሰኃ ል። በሌላ ባወተራል ባክልሉ ባቤተሠብ ሕ ብኖ ባሚቋረጎ በፔ አትተቾው ምክቭፔ ጸተ ቢዎቷ አትተቾው በሞፔ ሲለቭ መሆትት ቭተት ል። ብኖው ሲወርስ ተ ሞ ባ ራ ትብረ ው ጾል ተጸምሎ ባሚኖ ታርሻ ለወራሾቷ ባሚስፔ ታርሻ ተ ሞ ለራሷ ትተሚሆት ባቤተሠብ ሕ ጎ ታት ጋኖ ቨሣቨሉ።

ወ/ሮ ጸታ ዑመር ባሸሪዓ ምርታ ቤፔ ባሚኖ ሚስፔ ስለመሆ፟ አረ ባሰኃፔት ማስረ በማቨቨዝ ባሚኖ ወራሾኖ ማሽ ትብረ ት ት፟ቨካሚሏፔ ባሥረ ስልኃት ላለው መተብቾ ምርታ ቤፔ ክስ ስ ቀርብ ባሚኖ ወራሾኖ ሚስፔ ስለመሆ፟ ማስረ ት፟ሰኃፔ ለሸሪዓ ምርታ ቤፔ ቨመለጸተኖ ስለሆት ባትብረፔ ክምቭውም ጎ ቭ መ ባፔ ቨለበፔ በመተብቾው ምርታ ቤፔ ሣቭሆት ጎ ብት በመ መረቨባባው ባሸሪዓ ምርታ ቤፔ በጾል መሆት አለበፔ በማለፔ ተቃወሙ። ቭህተትም ባሚሉፔ ባትብረፔ ክምቭው በሸሪዓ ሕ በሸሪዓ ምርታ ቤ ኖ በጾል ቢ ቭ በሸሪዓው ሚስፔ ባሏት መውረስ ስለምፔኖል በሸሪዓ ሕ መሠረፔ ጸትብረቱ ባም ገፀው አትታ አራተቾውት ት ማሹት ባለመሆት ቸው።

ሀ. ርሰም ጎ ብት ባቨዙፔ ቾ ቢሆት

ባትብረፔ ክምምሉት አስመልክ ወ/ሮ ጸታ ዑመር ባሕ መት ስቱ አትቀኮ 34/5/ ባወተራል ሸሪዓ ምርታ ቤ ኖት አቋም ለማጎ ጸር በወኃው አዋ 188/1992 አትቀኮ 4 ትዑስ አትቀኮ 2 መሠረፔ በሸሪዓ ምርታ ቤፔ ለመ ገቼ በሸሪዓ ሕ መሠረፔ ጎ ብ ት፟ ቭ ወቃታ ሰጎ ለኖ ብለው ጎ ብት በሸሪዓ ምርታ ቤፔ ትታ ቀርብ ቭወስ ሉት? ለምት?

ለ. ወ/ሮ ጸታ ዑመር ባአ ዑስማት አበ ዝ ል ብፔሆት ባሚኖ ል ወራሽ መሆ፟ት ባሚቨረ ጎ ማስረ ጸሸሪዓ ምርታ ቤፔ አት፟ሰኃፔ አመልክ ባወራሽቼ ማስረ ውት ጸወሰተኖ በኂላ ባውርስ ትብረፔ ክምምሉት በተመለጸተ በሸሪዓ ምርታ ቤፔ ለመ ገቼ ወቃተቾ ባፔሆት ባውርስ ባትብረፔ ክምምሉ በኢፔቮእቨ ባውርስ ሕ መሠረፔ ት፟ወኘም ብፔጎ ቭቅ ጎ ቨቁዋ ተቀባቭቼ ማ ገቼ አለበፔ ብለው ቨስባሉ? ወራሽቼት ት፟ቨረ ጎ

ለሸሪዓ ፆርታ ቤፔ ማመልጸኖ ማቅረብ ባውርስ ትብረፔ ክፆቫ ስርዓቱት ባሸሪዓ ፆርታ ቤፔ አቭ ት ፈወስት ወቃተፖቼት መ ለኮ ት ቨሣቨል ብለው ቨስባሉ? ለምት?

ምዕራፍ ሁለት

የኢትዮጵያ የውርስ አስተላለፍ ሥርዓት በጠቅላላው፣

ይህ ምዕራፍ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሕግ በተለይም የፍትሐብሔር ሕጉ ፣

- ስለ ውርስ ስለሚከፈትበት ጊዜና በውርስ ሊተላለፉ ስለሚችሉ መብትና ግዴታዎች፣
- ለመውረስ ስለሚያስፈልግ ችሎታና አንድን ሰው ለወራሽነት ያልተገባ ነው ሊያሰኙ ስለሚችሉ ምክንያቶች፣
- በተለይም የፍትሐብሔር ሕጉ የውርስ ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች ይዘት አተረጓጐምና በአፈጻጸም ላይ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮች ለሰልጣኞች በማሣየት ስለውርስ ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ታስቦ የቀረበ ነው።

2.1 ባኢፔቮእቨ ባወርስ ሕ ታት ፡ሥኖ አተረ ፔ

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ በአምስተኛው አንቀጽ አገሪቱ የውርስ ስርዓት እንዴት እንደሆነ ዝርዝር የሆኑ ደንቦችን የያዙ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ተደንግገው ይገኛሉ። እነዚህ ስለ ውርስ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች አቀራረጽ ስንመለከት በአንድ በኩል የውርስ ሕግ ጠቅላላ መሪ ደንቦች የሆኑ ጠቅላላ የሕግ ድንጋጌዎች /General Provisions/ ያሉት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሚች ውርስ በኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ የሚተላለፍበትን መንገድ በዝርዝር የሚያስቀምጡ ስለ ውርስ ንብረት አስተዳደር እና የውርስ ንብረት እንዴት ለወራሾች እንደሚከፋፈል የሚዘረዝሩ ልዩ የሕግ ድንጋጌዎች /Special Provisions/ ተደንግገው ይገኛሉ። በፍትሐብሔር ሕጉ ውርስ ስለሚከፈትበት ጊዜና ስፍራ ለወራሾች ሊተላለፉ ስለሚችሉ የሚች መብትና ግዴታዎች እና ሚችን ለመውረስ ስለሚያስፈልግ ችሎታ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826-841 የተደነገጉት የሕግ ድንጋጌዎች ጠቅላላ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሆናቸው በግልጽ ተመልክቷል።

እነዚህ ጠቅላላ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች የሚች ውርስ በኑዛዜ ወይም ያለ ኑዛዜ በሚፈፀምበት ወቅት መሪ ደንቦች በመሆን በእኩልነት ተፈጻሚነት ያላቸው ናቸው። ጠቅላላ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች የኢትዮጵያ ሕግ ስለ ውርስ ያስቀመጠውን አጠቃላይ መርህ የሚያንፀባርቁ እና አንድ ሰው ወራሽ ሆኖ ለመቅረብ ማሟላት ያለበትን ሁኔታ የሚደነግጉ ናቸው። በፍትሐብሔር ሕጉ የሚች ውርስ ያለ ኑዛዜ ወይም በኑዛዜ ለወራሾቹ የሚተላለፍበትን መንገድ በዝርዝር የሚወስኑት ደንቦችና ስለ ውርስ አስተዳደር፣ የውርስ አጣሪ የውርስ ንብረት ክፍፍል

የተደነገጉት ገዥነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ልዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ናቸው:: እነዚህ የኢትዮጵያ የውርስ ሥርዓት አስተዳደርን የሚቆጣጠሩ ዝርዝር ደንቦች የያዙ ሲሆን የውርስ ሕጉን አብዛኛውን ክፍል ሸፍነው እናገኛቸዋለን::አንድ አንድ ጊዜ በውርስ ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች እና ዝርዝር ጉዳዮችን በሚወስኑት ልዩ ድንጋጌዎች መካከል የሰፋ ልዩነት እና የመልእክት አለመጣጣም ያጋጥማል:: የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥመን የመጀመሪያው ጥረታችን መሆን ያለበት ሁለቱ የሕግ ድንጋጌዎች ተቻችለው በስራ ላይ የሚውሉ ከሆነ አቻችለን ሁለቱም ድንጋጌዎች የወጡበትን ግብ እና አላማ እንዲያስፈጽሙ ማድረግ ነው::

ነገር ግን ሁለቱ የሕግ ድንጋጌዎች ተቻችለው በአንድ ላይ በስራ ላይ ለማዋል የሚችሉበት ሁኔታ ካጋጠመን በጠቅላላ የሕግ ድንጋጌዎች እና በልዩ የሕግ ድንጋጌዎች መካከል መሠረታዊ ልዩነት ሲኖር ለልዩ የሕግ ድንጋጌዎች ብልጫ እና ተፈጻሚነት መስጠት አለበት የሚለውን የሕግ አተረጓጎም መርህ መከተል አለብን:: ስለዚህ ለልዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ብልጫ በመስጠት ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ ከሕግ መተርጎም ተግባር ውስጥ የመጀመሪያው ነው::በመሆኑም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 - 841 የተደነገጉት ድንጋጌዎች የውርስ ሕግ ጠቅላላ መሪ ደንቦች መሆናቸውን እና ሌሎች ድንጋጌዎች ዝርዝር ጉዳዮችን የሚያብራሩ ልዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሆናቸውን በመገንዘብ በሁለቱ መካከል መሠረታዊ ልዩነት ሲያጋጥመን የሕግ አተረጓጎም መርሆችን በመጠቀም ለተያዘው ጭብጥ እልባት መስጠት እንደሚገባ መዘንጋት የለበትም::

2.2. የውርስ መከፈትና በውርስ ስለሚተላለፉ መብትና ግዴታዎች

የዚህ ንዑስ ክፍል አይነተኛ ዓላማ

- የሚች ውርስ የሚከፈትበት ጊዜና ሥፍራ፣
- ከሚች ወደ ወራሾቹ ሊተላለፉ የሚችሉ መብትና ግዴታዎች እና ከሚች ወደ ወራሾቹ ሊተላለፉ የማይችሉ መብትና ግዴታዎችን አስመልክቶ በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ያሉትን ክፍተቶችና ከሌሎች ሕጐች ጋር እነዚህ ድንጋጌዎች ያላቸውን ግጭት ማሳየት ነው::

2.2.1. ውርስ የሚከፈትበት ጊዜና ሥፍራ

በብዙ አገሮች ሕግጋት አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ ያገኙ መብትና ግዴታዎች ሊኖረው የሚችለው ከተወለደበት ቀን አነስቶ እስከሞተበት ቀን ድረስ ነው:: የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1'' ሰው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከሞተበት ቀን ድረስ የሕግ መብት አለው'' በማለት በግልጽ ደንግጓል::

በጽንሰ ኃሣብ ደረጃ የሚች ውርስ ተከፈተ የምንለው ሚች በሞት ሲለይ በሕይወት ዘመኑ ሲኖር በነበረው መብቱ ተጠቅሞ ያፈራው ንብረት ባለቤት በማጣቱና ለሚች ግዴታም ተጠያቂ የሚሆን ባለመኖሩ የአንዲት አገር ሕግ የሚችን መብትና ግዴታ ለሌሎች ሰዎች /ወራሾች/ ለማስተላለፍ ስለ ሚች ውርስ አስተዳደር ትኩረት ሰጥቶ ጥበቃ ማድረግ መጀመሩን የምናመለክትበት ነው። የኢትዮጵያ ሕግ በዚህ ላይ ያለውን አቋም ስንመለከት አንድ ሰው የሞተ አንደሆነ በሞተበት ጊዜ ዋና መኖሪያ ሥፍራ በሆነበት ቦታ የሚች ውርስ ይከፈታል'' በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826/1/ ይደነግጋል። ከዚህ የሕግ ድንጋጌ የምንረዳው የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ስለ ሚች ንብረት የውርስ አስተዳደር ትኩረት መስጠትና ጥበቃ ማድረግ የሚጀምረው ሚቹ ከሞተበት ሠዓት ደቂቃና ሠኮንድ ጀምሮ ምንም አይነት የጊዜ ክፍተት ሣይተው መሆኑን ነው።

ሚች ህይወቱ ማለፉ ከተረጋገጠበት ቅጽበት ጀምሮ የሚች ውርስ ይከፈታል። የሚች ውርስ የሚከፈትበትን ጊዜ በሕግ መወሰኑና ግልጽ በሆነ ድንጋጌ ማስቀመጡ፣ ራሱን የቻለ ጥቅም አለው። የመጀመሪያው ሚችን የሚወርሰው ሰው ሚች ከሞተ በኋላ በስንት ጊዜ በህይወት የኖረ ነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በሌላ አነጋገር የሚች ወራሾች እነማን እንደሆኑ ለማረጋገጥ መረዳቱ ነው። በፍትሐብሔር ሕጋችን ሚችን ለመውረስ ሚች ሲሞት በህይወት መኖር አስፈላጊ መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 ተደንግጓል። የሚች ውርስ የሚከፈተው ሚች በሞተበት ቅጽበት በመሆኑ ሚች ከሞተ በኋላ በአንድ ወይም በሁለት ሠከንድ ዘ ቭ የሞተ ሰው ሚችን ወርሶ እንደሞተ ይቆጠራል። ስለዚህ የሚች ውርስ የሚከፈትበትን ጊዜ ትኩረት ሰጥቶ የሕጉ ድንጋጌ በግልፅ ማመልከቱ የወራሽነት ችሎታን እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የተደነገጉትን የሕግ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም እና ለመተርጐም ጉልህ ጠቀሜታ አለው።ሌላው በጥንቃቄ መታየት ያለበት ነጥብ ፣የሚች ውርስ መከፈት የሚለውን ጽንሰ ሀሣብ የሚች ወራሾች ነን የሚሉ ሰዎች የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በፍትሐብር ሕግ ቁጥር 996-1002 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት ፍርድ ቤት ቀርበው ከሚያቀርቡት አቤቱታ እና ከሚያስከፍቱት የሥራ ፋይል ጋር አንድ አለመሆኑን ነው። የሚች ውርስ መከፈት የሚለው ጽንሰ ሀሣብ ሚች በህይወት እያለ የነበረው የፍትሐብሔር መብትና ግዴታ የተቋረጠና የሚች ንብረት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 942 በተደነገገው መሠረት '' እንደ አንድ ልዩ ንብረት ተቆጥሮ '' ሕግ ጥበቃ ማድረግ መጀመሩን የሚያመለክትና ይህም የሚች ህይወት ካለፈበት ቅጽበት ጀምሮ የሚከናወን መሆኑን የሚያሣይ ነው።

የሚች የሕግ ወይም የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ በማስረጃ ከተጣራ በኋላ ይህንኑ የሚያረጋግጥ የፍርድ ቤት ውሣኔ ወይም ትእዛዝ ይሰጠኝ በማለት የሚች ወራሾች ነን የሚሉ ሰዎች የሚያቀርቡት ጥያቄ ውርሱ ከተፈተ በኋላ የሕጉ የይርጋ የጊዜ ገደብ እስከሚገድበው ድረስ የሚቀርብ የወራሽነት መብት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጠኝ ጥያቄ ነው፡፡ ይህም ከሚች ውርስ በወራሽነት ተካፋይ ለመሆን የሚያስችላቸው ማስረጃ እንዲሰጣቸው የሚያቀርቡት ጥያቄ በመሆኑ ከሚች ውርስ መከፈት የተለየ ጽንሰ ሀሣብ ነው፡፡ በመሆኑም የሚች ውርስ የሚከፈትበት ጊዜ ሚች ከዚህ ዓለም በሞት የተለየበት ቅጽበት እንጅ ወራሾቹ የሚች ወራሽ መሆናችንን የሚያስረዳ ማስረጃ ይሰጠ ን በማለት ፍርድ ቤት ቀርበው መዝገብ ያስከፈቱበት ጊዜ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ስለ ሕግ እውቀት የሌላቸው ሰዎች የሚች ውርስ ተከፈተ የሚሉት የሚች አርባ ቀን ካለፈ በኋላ የሚች ቤተሰቦች ዘመዶችና በሕይወት ዘመኑ ያፈራቸው ወዳጆቹ ተሰብስበው የሚችን የኑዛዜ እና የሕግ ወራሾች እንደዚሁም ከሚች የተገኘውን ንብረት ለሌሎች ሰዎች በአደራ ወይም በትውስት የሰጣቸው እቃዎች ወይም ገንዘብ በብድር ለሌላ ሰው የሰጠውን ገንዘብና ሚች ያለበትን የሌሎች ሰዎች እዳ ለማጣራት ምክክር እና ምርመራ የሚያደርጉበትን ጊዜ ነው፡፡ ይህ ስርዓት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 942 እስከ 961 በተደነገጉት የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የሚያደርግ የውርስ ማጣራት ስርዓት እንጅ የሚች ውርስ መከፈት የሚለውን ጽንሰ ሀሣብ ጋር አንድ አለመሆኑን መጠቆም ጠቃሚ ነው፡፡

የፍትሐብሔር ሕጉ የሚች ውርስ የሚከፈተው በሚች ዋና የመኖሪያ ስፍራ እንደሆ ይደነግጋል፡፡ የአንድ ሰው የመኖሪያ ቦታ እና መደበኛ ቦታ በተመለከተ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 174-191 የተደነገገ ሲሆን ተማሪዎች ከዚህ በፊት ስለ ሰዎች ሕግ በተማራችሁበት ጊዜ በቂ ግንዛቤ አግኝታችኃል የሚል ግምት ስላለ የሚች ዋና መኖሪያ ቦታ የሚባለው የትኛው ነው የሚለውን ነጥብ በዝርዝር ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ የሚች ህይወት ካለፈበት ቅጽበት ምንም የጊዜ ክፍተት ሣይተው በሚች ዋና መኖሪያ ስፍራ ውርሱ እንደሚከፈት ይደነግጋል፡፡ የሚች ውርስ የሚከፈትበትን ጊዜ ማወቅ ስለ ወራሽነት ችሎታ እና ሌሎቹን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ለመረዳት እና ለመተርጐም እንደዚሁም በአግባቡ በተግባር ላይ ለማዋል ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ መረሣት የሌለበት ነጥብ ነው፡፡ ዚህ ላቭ በፔጽረፔ መ ባፔ ቨለበፔ ባሚኖ ውርስ ባሚጸወፔበፔት ስምራ በሕ

መወሰት ባማኖት ውርስ አወክ ም ስርዓፔ አስመልክ ባሚችሱ አለመ ባባ ኖት ለመዎ ፔ ፔልቅ ጎ ቀሜ ት ለው ባሚኖ ውርስ ባሚጸወፔበፔ ስዎራ በውርሱ ምክንቨፔ ባሚችሱ ክርክሮኖት ለማባፔ ባ ዛፔ ክልል ስልኃ ት ቨለውት ዎርታ ቤፔ ለመለባፔ አስወላ ፣ ትተሆትበ ቾም አ ር ባዚህት ትኅ ብ አስወላ ፣ትፔ ባዎፔሐብሔር ሥት ሥርዓፔ ሕ ቁጎ ር 23 ድንጋጌዎች በአብትፔ ለማባፔ ይቻላል። በአጎ ቃላቨ ባሚኖ ውርስ መጸወፔ ጎ ቨ ባሚተት ልኮ ባሕ ታት ፣ ማስቀመጎ ተ ቢ ሲሆት ባሕ ጎት ታት ፣ መትወስ ቨዘፔ ባወኃበፔት ዓላማ ተረታ በተ ቢው መት ታ ስራ ላቨ ማዋል አስወላ ፣ ችው።

2.2.2 ከሚች ለወራሾቹ ሊተላለፉ የሚችሉና ሊተላለፉ የማይችሉ መብትና ግዴታዎች

በመጀመሪያው ምእራፍ እንደተመለከተው የውርስ ሕግ ዋናው አላማና ግብ የሚች መብትና ግዴታዎች ወደ ወራሾቹ የሚተላለፍበትን ስርዓት መልክ ማስያዝ ነው። ይህ ሲባል ግን ሚች የነበረው መብት እና ግዴታ በሙሉ ወደ ወራሾቹ ይተላለፋል ማለት አይደለም። በፍትሐብሔር ሕጋችን ለሚች ወራሾች የሚተላፉት የሚች መብቶችና ግዴታዎች በሚች መሞት ምክንያት ተቋርጠው የማይቀሩት ብቻ መሆናቸው በግልጽ ተደንግጓል። ይህንንም ዕንሰ ኃሣብ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀፅ 2 ''በሚች መሞት ምክንያት ተቋርጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አንቀጽ ደንቦች መሠረት በውርስ ውስጥ የሚገኙት የሚች መብቶችና ግዴታዎች ለወራሾቹ እና የኑዛዜ ባለስጦታዎች ይተላለፋሉ'' በማለት በግልጽ አስቀምጦታል።

ከዚህ የሕግ ድንጋጌ የምንረዳው በሚች መሞት ምክንያት ተቋርጠው የሚቀሩ መብቶችና ግዴታዎች ወደ ወራሾቹ ሊተላለፉ እንደማይችሉ ነው። እነዚህ በሚች መሞት ምክንያት ተቋርጠው የሚቀሩ መብትና ግዴታዎች ምንድንናቸው የሚለውን ጥያቄ ስንጠይቅ ሚች በግሉ ብቻ ሊጠይቃቸው እና ሊጠቀምባቸው የሚችሉ መብቶች /Personal rights/ እና ሚች በግሉ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ግዴታዎች /Personal obligations/ ናቸው።የሚች ግላዊ መብቶችና ግዴታዎች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሣሌ ሚች በሙያው በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በአንድ የግል ድርጅት ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ ቢሆን የሚቹ የመሥራት መብት ወራሾቹ ከእሱ ጋር ተመሣሣይ በሆነ ሙያ የሰለጠኑ ቢሆኑም እንኳን ለወራሾቹ በውርስ የሚተላለፍ አይደለም። አንደዚሁም ሚች ከልጆቹ ወይም ከዘመዶቹ የነበረው ቀለብ የመጠየቅ መብት ሚች ሲሞት የሚቋረጥና ለወራሾቹ ሊተላለፍ የማይችል መብት ነው።በሌላ በኩል ሚች በግል ችሎታው ለመፈፀም የገባቸው ግዴታዎች፣ ወራሾቹ በዚያ ሙያ

ከእሱ የበለጠ ችሎታ እና ትምህርት ቢኖራቸውም እንኳን ሚች በግሉ ለመፈፀም የገባውን ግዴታ እነርሱ ተክተው እንዲፈጽሙ አያስገድዳቸውም። ይህም አንድ የህክምና ዶክተር ወይም ጠበቃ በሙያው ለመፈፀም የገባውን ግዴታ እሱ ሲሞት ወራሾቹ ዳክተሮች ወይም ጠበቃ ቢሆኑም እንኳን ሚች በገባው የውል ግዴታ እነርሱ ወርሰውና ተተክተው እንዲፈጽሙ መጠየቅና ማስገደድ አይችልም።ስለዚህ ከሚች ወደ ወራሾቹ የሚተላለፉ መብትና ግዴታዎችን ለመለየት መብትና ግዴታዎቹ በሚች መሞት ምክንያት የሚቋረጡ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን ጥያቄ በማንሣት መመርመር ያስፈልጋል። አብዛኛውን ጊዜ ሚች በውል ወይም በሕግ መሠረት ያገኘው የይዞታ መብት በውሉ ወይም በሕግ በተገለፀው የጊዜ ገደብ እስከሚደርስ ድረስ በአንድ ንብረት የመጠቀም መብት ሙሉ ወይም ሌላ የንብረት ባለቤትነት፣የአክሲዮን፣ የንግድ መደብር እና የሌሎች የንግድ ማህበር ድርሻዎች ሚች ከሌሎች ሰዎች ሊጠይቀው የሚችል የገንዘብ እዳና በውል መሠረት የሚፈፀም ግዴታ እንደዚሁም ሌሎች አበዳሪዎች ከእሱ የሚጠይቁት የገንዘብ እዳና በሚች መሞት ምክንያት የማይቋረጥ የውል ግዴታ ለሚች ወራሾች የሚተላለፉ የሚች መብትና ግዴታዎች ናቸው።

የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ የሚች ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍል ናቸው በማለት የሚች ወራሾች ጥያቄ ማንሣት የማይችሉባቸውን የካሣና የጡረታ ገንዘብ ክፍያወች እንደዚሁም በሞት ጊዜ ሊከፈል ስለተገባ የህይወት ኢንሹራንስ ክፍያ ገንዘብ በምን መልኩ ለሚች ወራሾች እና የሚች ወራሽ ላልሆነ ሰዎች ሊተላለፉ እንደሚችሉ ገዥነት ያላቸውን ደንቦች ደንግጓል እነርሱንም በዝርዝር ስናያቸው፣

2.2.3. ስለሚች የውርስ ንብረት የተደነገጉ፣ ልዩ ድንጋጌዎች

ሀ. የጡረታና ካሣ ክፍያ

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 828 ድንጋጌ ስንመለከት

''በሞት ምክንያት ለሚቹ ዘመዶች ወይም ባል ወይም ሚስት የሚሰጡ ጡረታዎች ወይም ካሣዎች የውርሱ ሀብት ክፍል አይሆኑም'' ይህን የሕግ ድንጋጌ መንግሥት የሚች ንብረት ክፍል እንዳይሆኑ በፖሊሲ ደረጃ ውሣኔ ከሰጠባቸው አንደኛው የጡረታና የካሣ ክፍያ መሆኑን የሚያሣይ ሲሆን የሕጉን ድንጋጌ ይዘት በዝርዝር ስንመለከተው የሕጉ ተፈጻሚነት ሦስት ነገሮችን ሊዳስስ እንደሚችል ያስገነዝበናል። የመጀመሪያው ለሚቹ ዘመዶች ወይም ባል ወይም ሚስት የሚሰጡ ጡረታዎች የውርስ ሀብት ክፍል አይሆኑም በማለት የፍትሐብሔር ሕጉ ይደነግጋል። ይህ የሕግ ድንጋጌ በመንግስት የማህበራዊ -ዋስትና እና ድጐማ ፖሊሲ መሠረት የአገሪቱ ሕግ

ስለሚፈቅድላቸው ለተጣሪዎች የሚከፈልን የጡረታ አበል የሚች ወራሾች እንደ ውርሱ ንብረት ክፍል በመቁጠር ለእነርሱ እንዲሰጣቸው መጠየቅ እንደማይችሉ በግልጽ ገደብ ያደረገ ድንጋጌ ነው።

ሚች የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ ለጡረታ አበል ክፍያ የሚያበቃ ግልጋሎት ሰጥቶ በሞት ቢለይ አካለ መጠን ላላደረሱ ልጆቹ ለሚስቱና ለወላጆቹ የሚከፈለውን የጡረታ አበል የሚች ወራሾች መካፈል ይገባናል የሚል ክርክር እንዳያቀርቡ የሕጉ ድንጋጌ በማናቸውም መልክ የሚከፈል የጡረታ ክፍያ የውርስ ንብረት ክፍል አለመሆኑን በመደንገግ ወራሾች የጡረታው ክፍያ ለእኛ ይገባል የሚል ጥያቄ እንዳያቀርቡ ግልጽ የሆነ ክልከላ አድርጓል።በሁለተኛ ደረጃ ሚች በመሞቱ ምክንያት የሚከፈሉ የካሣ ክፍያዎችም እንደዚሁ የውርስ ንብረት ክፍል እንዳልሆኑ ተደንግጓል። ሚች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሚተዳደር ድርጅት ሠራተኛ ቢሆንና በስራው ላይ እያለ ሚች ለሚደርስበት የሞት አደጋ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅና በድርጅቱ የህብረት ስምምነት መሠረት ለሚች ዘመዶች /ቤተሰቦች/ የሚከፈል የካሣ ክፍያ ቢኖር ይህ የካሣ ክፍያ የውርስ ሀብት ክፍል አይሆንም እንደዚሁም ሚች በአደጋ ምክንያት በሞት በመለየቱ ከውል ውጭ ስለሚመጣ ሀላፊነት በሕጉ በተደነገገው መሠረት ለደረሰው አደጋ ሀላፊ የሆነ ሰው ሚች በመሞቱ ምክንያት ለተጐጅው ባል ወይም ሚስት እንደዚሁም ለልጆቹና ለወላጆቹ በመተዳደሪያ እረገድ ለደረሰባቸው ጉዳት ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2095/1/ ተደንግጓል። በዚህ መሠረት የሚች ባል ወይም ሚስት፣ ልጆቹና ወላጆቹ በየራሣቸው ስም የአደጋው ሀላፊ ከሆነው ሰው የተቀበሉት የካሣ ገንዘብ ወራሾቹ ለእኛ ሊሰጠን ይገባል የሚል ጥያቄ ማንሣት እንደማይችሉ የሕጉ ድንጋጌ ያስረዳል።

ሥናጠቃልለው የጡረታና የካሣ ክፍያዎች በሚቹ መሞት ምክንያት የሚከፈሉ ቢሆኑም የውርስ ንብረት ክፍል ባለመሆናቸው ወራሾች የይገባናል ጥያቄ ሊያቀርቡባቸው የማይችሉ መሆናቸው በሕጉ ድንጋጌ በግልጽ ተመልክቷል። ስለዚህ የህጉ ድንጋጌ መንፈስና ሕግ አውጭ ሊደርስበት ያሰበውን ግብ በሚች መሞት ምክንያት ለባል ለሚስት ፣ ለልጆቹና ለወላጆቹ የሚከፈል የጡረታ እና የካሣ ክፍያ ሚችን ከመውረስ መብት ጋር የተያያዘ ሣይሆን የራሱ የሆነ የፖሊሲ ውሣኔና የራሱ የሆነ ምክንያት ያለው በመሆኑ በሌሎች ሕጐች አፈጻጸሙ ስለሚሸፈን የሚች ወራሾች የወራሽ መብት ስላላቸው ብቻ የጡረታና የካሣ ክፍያ የይገባናል ጥያቄ ሊያቀርቡበት የማይችሉ መሆኑን በመገንዘብ በአተገባበሩ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

ለ. በሞት ጊዜ የሚከፈል የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት አንድ ሰው ከኢንሹራንስ ከፋይ ድርጅት ጋር እሱ ሲሞት ለተጠቃሚው እንደሚከፈልለት በመስማማት የሕይወት ኢንሹራንስ ውል መግባት ይችላል። ይኸ አይነት የኢንሹራንስ ውል በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁጥር 692/2/ በግልጽ የተቀመጠ ነው። ሟች የኢንሹራን ውሉን በሚዋዋልበት ወቅት በኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ የሚሆነውን ሰው በስም ለይቶ ወይም የኢንሹራንስ ውሉን ለወራሾቹ ጥቅም የገባ መሆኑን በግልጽ አስፍሮ ወይም የኢንሹራንሱን ተጠቃሚ ሣይገልጽ እና ኢንሹራንሱን ውል ለማን ጥቅም ሲል እንደገባ ምንም ፍንጭ ሣይተው የህይወት ኢንሹራንስ ውል የሚዋዋልበት ሁኔታ አለ።በመሆኑም ሟች ያደረገው የህይወት የኢንሹራንስ ውል ላይ ወራሾቹ ምን መብት አላቸውዕዕ የሟች ወራሾች መብት አለን ብለው ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት መቼ ነው የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 መልስ ለመስጠት የሞከረ ቢሆንም ጉዳዩ አከራካሪና አወዛጋቢ መሆኑን ሙሉ በሙሉ አላስቀረውም። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ ፣

> ሟቹ ተጠቃሚውን ያልወሰነ እንደሆነ ወይም
> ኢንሹራንሱ ለሟቹ ወራሾች ጥቅም የተደረገ እንደሆነ
> ሟቹ በፈረመው ስለ ህይወት ኢንሹራንስ ውል አፈጻጸም

የሚከፈሉ ገንዘቦች የውርስ ንብረት ክፍል ይሆናሉ ''በማለት የሚደነግግ ሲሆን፣ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ ከተመለከተው ውጭ በኢንሹራንስ ውሉ የተገለፀ ተቃራኒ ነገር ካለ ግን በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት የሚከፈለው ገንዘብ የውርስ ንብረት ክፍል እንደማይሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 8272/ ታቃራኒ ሁኔታ ሲኖር የውርሱ ኃብት ክፍል አይሆኑም በማለት ደንግጓል። ይህ የሕግ ድንጋጌ ሟች ሲሞት ስለ ሕይወት ኢንሹራንስ ውል በገባው ግዴታ መሠረት የኢንሹራንስ ድርጅቱ የሚከፍለው ገንዘብ ለሟች ወራሾች ሊሰጥና የውርሱ ንብረት ክፍል ሊሆን የሚችለው ከሁለቱ አንደኛው መሠረታዊ ሁኔታ ሲሟላ ነው።

የመጀመሪያው ሟች የህይወት ኢንሹራንስ ውሉን የተዋዋለው ለወራሾቹ ጥቅም መሆኑን በውሉ ላይ በግልጽ ሀሣቡን አስፍሮ እንደሆነ ነው። ሟች በስም ሣይዘረዝር የኢንሹራንሱን ውል የገባው ለወራሾቹ ጥቅም መሆኑን ጠቅለል ባለ አነጋገር ሀሣቡን

ከገለፀ ለሞት የሚደረግ ኢንሹራንስ ለአንድ ለተለየ ተጠቃሚ ጥቅም ማድረግ እንደሚቻል በንግድ ሕግ ቁጥር 702/1/ የተደነገገ በመሆኑና ሚች ወራሾቹን የኢንሹራንስ ልዩ ተጠቃሚዎች መሆናቸውን በመግለጽ የኢንሹራንስ ውል ከገባ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ በሚደነግገው መሠረት የሚች ውርስ ከተከፈተ በኋላ የሚች ወራሽ መሆናቸውን በአጥጋቢ ማስረጃ አረጋግጠው የቀረቡ የሚች ወራሾች በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት የሚከፈለው ገንዘብ እንደ አንድ የውርስ ንብረት ክፍል ተቆጥሮ ይከፋፈላል። ሁለተኛው በፍትሐብሔር ሕጉ የህይወት ኢንሹራንስ ውል ክፍያ የሚች ውርስ ንብረት ክፍል ሲሆን የሚችልበት ሁኔታ ሚች የኢንሹራንስ ውሉን የተዋዋለው ለማን ጥቅም እንደሆነ ያልገለፀ እንደሆነና የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ ማን እንደሆነ ፍንጭ ያልሰጠ እንደሆነ በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት የሚከፈለው ገንዘብ የውርሱ ንብረት ክፍል እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 (1) ደንግጓል። የፍትሐብሕር ሕጉ ሚች የኢንሹራንስ ውሉን የገባው ለወራሾቹ ጥቅም መሆኑን ባይገልጽ እና ለሌላ ተጠቃሚ መሆኑን ሣያመለክት በክፍት ቢተወው ምን ይደረጋል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የተወሰደው አቋም በኢንሹራንስ ውሉ ላይ ተጠቃሚው ካልተገለፀ ወይም ካልተመለከተ በውሉ መሠረት የሚከፈለውን ክፍያ እንደ ውርስ ንብረት ክፍል ተቆጥሮ ለወራሾች ማከፋፈል ይገባል የሚል ነው።

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827(1) የተደነገገው እንዳለ ሆኖ በዚሁ ጭብጥ ላይ የንግድ ሕጉ የወሰደው አቋም ከፍትሐብሔር ሕጉ የተለየ መሆኑን ከንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ለመረዳት እንችላለን። የንግድ ሕግ ቁጥር 701 ድንጋጌዎች ስንመለከት፣ በመርህ ደረጃ ለሞት የሚደረግ ኢንሹራንስ ለአንድ የተለየ ተጠቃሚ ሊደረግ እንደሚችል የንግድ ሕግ ቁጥር 701 (1) የደነገገ ሲሆን፣ የንግድ ሕጉ ቁጥር 701(2) በበኩሉ

'' ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም
ሀ/ ጋብቻው የተደረገው የኢንሹራንስ ውል ከተፈፀመ በኋላም ቢሆን
እንኳን ውል የፈፀመው ባል ወይም ሚስት
ለ/ የኢንሹራንሱ ውል ሲፈፀም የተወለዱት የኢንሹራንስ ውል ፈራሚ
ሰው ልጆች ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚወች ተብለው ይጠራሉ''
በማለት ይደነግጋሉ።

ይህ የንግድ ሕግ ድንጋጌ ከፍትሐብሕር ሕግ ቁጥር 827/1/ ጋር መሠረታዊ ልዩነት ያለው ሲሆን ሁለቱ የሕግ ድንጋጌዎች በአፈጻጸምም ወቅት ሆነ በይዘታቸው እርስ በርሣቸው የሚቃረኑ መሆኑን ለመገንዘብ እያዳግትም።

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842 መሠረት የሚች ልጆች የሚች የመጀመሪያ ወራሾች ሲሆኑ ከውርሱ የሚደርሣቸው ድርሻም እኩል ነው። የንግድ ሕጉ ከሚች ልጆች መካከል የኢንሹራንስ ውሉ ሲፈፀም የተወለዱትን ብቻ የኢንሹራንሱ ውል ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ሲደነግግ የፍትሐብሔር ሕጉ የሚች ወራሾች በኢንሹራንስ ውሉ ተጠ ቃሚው ካልተገለፀ በኢንሹራንስ ውል መሠረት በሚከፈል ገንዘብ ላይ የወራሽነት መብታቸው እስከፈቀደ ድረስ ድርሻ እንዳላቸው ይደነግጋል። በፍትሐብሔር ሕጉ የሚች ወራሾች የሚች ልጆች ብቻ ሣይሆኑ ተወላጆቹ ወይም እነሱ ከሌሉ ወላጆቹ ወይም የእነርሱ ተተኪዎች እንደሚሆኑ ይደነግጋል። ከዚህ በተጨማሪ ሚች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሾች ይኖሩታል። በሌላ በኩል በፍትሐብሔር ሕጋችን ሚስት ባሏን ባል ሚስቱን የመውረስ መብት የላችወመወዉ ይህም በመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ የኢንሹራንሱ ውል ሲፈጸም በተወለዱ እና ከዚያ በኋላ በተወለዱ የሚች ልጆች መካከል፣ በሁለተኛ ደረጃ በሚች ሚስት ወይም ባል፣ በሚች ልጆች መካከል በሶስተኛ ደረጃ በሚች ሚስት ወይም ባልና በሚች ወራሾች መካከል የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን በተመለከተ መጠነ ሰፊ ክርክር መነሣቱ የማይቀር ነው። እነዚህም የሚከራከሩት በየበኩላቸው ክራክራቸውን የሚደግፈውን የፍትሐብሔር ወይም የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ ነው።

ለምሣሌ አምሣሉ የተባለ ሰው የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ ማን እንደሆነ ሣይገለጽ ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጋር ብር 20000/ሃያ ሽህ ብር/ እሱ ሲሞት የሚከፈል የመድን ውል ተዋውሏል እሱም፣ አዜብ የተባለች ሚስት አለችው። ውሉን ከመዋዋሉ በፊት ቢኒያም አምሣሉ የተባለ ልጅ ወልዷል። ውሉን ከተዋዋለ ከሶስት ወር በኋላ ደግሞ ጽጌ አምሣሉ የተባለች ልጅ ወልዷል። አምሣሉ ከሞተ በኋላ ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት ሊከፈለው የሚችለውን ገንዘብ አስመልክቶ የፍትሐብሔር እና የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች እየተጠቀሱ መጠነ ሰፊ ክርክር ሊያነሱ ይችላሉ። የመጀመሪያው፣ ቢኒያም አምሣሉና ፅጌ አምሣሉ በወኪላቸው አማካኝነት፣ አባታችን የኢንሹራንስ ውል ሲገባ ተጠቃሚዎችን ያልገለፀ ስለሆነ፣ በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት መከፈል ያለበት ብር 20 000 በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827(1) በሚደነግገው መሠረት የአባታችን የውርስ ንብረት ክፍል ስለሆነ፣ በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ደግሞ ሚስት ባሏን ባል ሚስቱን እንዲወርሱ ስለማይፈቅድ፣ የኢንሹራንስ ገንዘቡ የሚች አባታችን ወራሽ ለሆነው ለእኛ ለልጆቹ ይገባል ብለው ቢጠይቁ የሚች ሚስት ወሐሮ አዜብ በበኩላቸው በንግድ ሕግ ቁጥር 701 (1) መሠረት በኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚው ባይገለፅም እና ጋብቻው የተደረገው

የኢንሹራንስ ውል ከተፈረመ በኋላ ቢሆንም እንኳን፣ ሚስት የኢንሹራንሱ ገንዘብ ተጠ ቃሚ መሆን እንደሚችሉ ስለሚደነግግ፣ ሟቹ ባሌን መውረስ በሕግ ባይፈቀድልኝም፣ እሱ የገባው ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ ከመሆን ልታገድ አይገባኝም በማለት ትከራከራለች።በሁለተኛ ደረጃ ወ/ሮ አዜብና ቢኒያም አምላኩ፣ ፅጌ የኢንሹራንስ ውሉ ከተፈረመ በኋላ የተወለደች ስለሆነ፣ በንግድ ሕጉ ቁጥር 701 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ መሆን አትችልም የሚል ክርክር ቢያነሱ ፅጌ አምላኩ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827(1) ድንጋጌ በመጥቀስ፣ በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት የሚከፈለው ክፍያ የሟች ውርስ ንብረት ክፍል ስለሆነና እኔ የሟች ወራሽ ስለሆንኩ ድርሻየ ይገባኛል በማለት ትከራከራለች።በመሆኑም ለክርክሩ ደጋፊ የሆኑት የንግድ ሕግ ድንጋጌ ወይም የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ እየተጠቀሰ ክርክሩ ሊቀጥል ይችላል።በሌላ ሁኔታ ሟች አምላኩ ጽጌንና ቢኒያምን ባይወልድና ወራሾቹ እናት እና አባቶቹ ቢሆኑ በአዜብ እና በአምላኩ እናትና አባቶች መካከል የፍትሐብሐር ሕጉ እና የንግድ ሕጉ ድንጋጌ በዋቢነት እየተጠቀሱ ክርክሩ አንደሚቀጥል መገንዘብ አያዳግትም።

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ እና በንግድ ሕግ ቁጥር 702/2/ መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት በትርጉም ለመፍታት የተለያዩ ሀሣቦች ሲቀርቡ ይስተዋላሉ። በተለይ ሁለቱም ሕጐች ማለትም የፍትሐብሔር ሕጉም ሆነ የንግድ ሕጉ ከመስከረም 1ቀን 1953 ጀምሮ ሥራ ላይ እንደው የታወጁ መሆናቸው ሲታይ በአተረጓጐም ረገድ ያለውን ችግር ያባብሰዋል ይህም በመሆኑ፣

የንግድ ሕጉ ስለ ሕይወት ኢንሹራንስ ውል ክፍያና ስለ ህይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠ ቃሚ የማደነግግ በመሆኑ ከጠቅላላው የውርስ ሕግ ድንጋጌ ማለትም ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ የበለጠ ተፈጻሚነት ሊሰጠው የሚገባው ለንግድ ሕግ ቁጥር 701/2/ ነው የሚል ነው።

ከላይ የቀረበውን ሀሣብ የማይቀበሉ ወገኖች በበኩላቸው የሚችን የውርስ ሁኔታና የውርስ ንብረት ክፍል የሚወስኑት ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ሕጉ እንጅ በንግድ ሕጉ ተካትተው አይገኙም። ስለዚህ የውርስን ጉደይ ስንመለከት ብልጫ ሊሰጠው የሚገባው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ እንጅ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ አይደለም የሚል ነው።

ሁለቱ የሕግ ድንጋጌዎች አቻችለን በስራ ላይ ማዋል እንችላለን፡፡ የሚች ወራሾች በፍትሐብሔር ሕጉ የተሰጣቸው መብት ሣይጣስ የሚች ሚስት ወይም ባል በንግድ ሕጉ የተሰጣቸው መብት ሣይጣስ የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን በተመለከተ ብቻ ሚስት ወይም ባል ከሚች ወራሾች

ጋር የጋራ ተጠቃሚ ማድረግ እየቻልን አንደኛውን ጠቅሞ ሌላውን በሚጐዳ ሁኔታ ሕጉን መተርጐም የለብንም የሚል አቋም የሚያራምዱ ያሉ ሲሆን አከፋፈሉን በተመለከተም የተለያየ ሀሣብ ይሰነዘራል፡፡ ለምሣሌ ሚስት ወይም ባል ግማሹን መውሰድ አለባቸው የሚል ያለ ሲሆን በሌላ በኩል በህይወት ኢንሹራንስ ውል መሠረት የተከፈለውን ገንዘብ ለመካፈል ባል ወይም ሚስት እንደ ሟች አንድ ወራሽ ተቆጥረው ከወራሾቹ ጋር እኩል መካፈል አለባቸው የሚል ሀሣብ አለ፡፡

ሟች የህይወት ኢንሹራንስ ውሉን ሲዋዋል ተጠቃሚውን ባልገለፀበት ጊዜ ከላይ የተነሣው የሕግ አተረጓጐምና የአፈጻጸም ችግር አለ፡፡ የሕግ አውጭ ሀሣብ ምን እንደሆነ ለመረዳት ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ሕግ አውጭው በዚህ ጉዳይ ያደረገውን ውይይት ይዘት ጭምር መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በተለያዩ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የጽሁፍ አቅራቢ ይህንን እድል አላገኘም፡፡ ስናጠቃልለው በሞት ጊዜ የሚከፈል የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ ተጠቃሚው በግልጽ በተጠቀሰበት ጊዜ ማለትም ለሌላ ሰው ክፍያ ተብሎ ውሉ ከተገባ የሚች የውርስ ንብረት ክፍል አይሆንም፡፡ ይህንንም ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ እና የንግድ ቁጥር 701/1/ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡የኢንሹራንስ ውሉ ለሚች ወራሾች ጥቅም የተደረገ መሆኑ በግልጽ በኢንሹራንስ ውሉ በተገለፀ ጊዜ ምንም ክርክር ሣይቀርብበት እንደ ሚች የውርስ ንብረት ክፍል ተቆጥሮ የሚች ወራሾች ገንዘቡን እንዲከፋፈሉት ይደረጋል፡፡የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚው በግልጽ ያልታወቀ ሲሆን እና ለወራሾቹ ጥቅም የተደረገ መሆኑን የማይገልጽ ሲሆን ከላይ ባየነው መሠረት በንግድ ሕጉ እና በፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ መካከል የሚታየው ልዩነት አወዛጋቢና ለትርጉምም በር የሚከፍት

የ ሙ ከ ራ ጥ ያ ቄ

1ኛ. አሁን በስራ ላይ ያለውን የውርስ ሕግ አንቀጽ 287(1) እና በንግድ ሕግ ቁጥር 702/2/ መካከል ያለውን ልዩነት ለመፍታት ዕርስዎ የትኛውን አተረጓጎም መርህ ይከተላሉ? ለምን?

2ኛ. ተጠቃሚው በግልፅ ባልተገለፀ ጊዜ፣ በሞት ጊዜ የሚከፈል የኢንሹራንስ ውል ክፍያ የውርስ ንብረት ክፍል ማድረጉ ተገቢ ነው ብለው ያስባሉ?

3ኛ. የአንድ አንድ አገሮች የውርስ ህጎች ከሚች ወደ ወራሾች የተላለፉትን መብቶችና ግዴታዎች በጥቅሉ ሣይሆን በዝርዝር ያስቀምጣሉ፡፡ የእኛ ደግሞ ኋበሚች መሞት የማይቋረጡ መብትና ግዴታዎችቃ የሚል መስፈርት ብቻ ያስቀምጣል፡፡ ይኽ አቀራረፅ ተገቢ ነው ብለው ያስባሉ?

4ኛ. በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 41 መሠረት መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የመንግስትና የህዝብ ነው፡፡ ሆኖም አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች እና በግብርና መስክ የተሠማሩ ኢንቨስተሮች በህጋዊ መንግድ በያዙት መሬት ላይ ያላቸውን የመጠቀምና የይዞታ መብት፣ ቋሚ ተክሎችና ሌሎች ንብረቶች ለወራሾቻቸው የማስተላለፍ መብታቸው የፌዴራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 80/1989 እና ይህንን መሠረት በማድረግ በክልላችሁ ምክር ቤት በወጡ ክልላዊ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጆች የተሰጠው ዋስትና እና ጥበቃና የተጣለባቸውን ገደቦች በዝርዝር የብራራሕ ይህንንም ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 826-2? ድንጋጌ አንፃር ይተንትኑ

5. ባለሀብቶች በፌዴራል መንግስት የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝ ያወጣው አዋጅ ቁጥር 272/1994 እና የፌዴራል መንግስት የኢንቨስትመንት አዋጅን እንደገና ለመደንገግ ያወጣው አዋጅ ቁጥር 280/1996 በአዋጅ ቁጥር 375/1996 እንደተሻሻለ መሠረት ያገኙትን የከተማ ቦታ ለወራሾቻቸው የማስተላለፍ መብታቸው በአዋጆቹና አዋጆቹን ልማስፈፀም የክል መንግስታታ ባወጧቸው ደንቦች የተሰጣቸው ዋስትና ጥበቃና የተጣለባቸው ገደቦች መኖራቸውን በዝርዝር ያብራሩ? ይህንንም ከፍትሐብሔር ህግ ቅጥር 826 -2? ድንጋጌ አንፃር ያለውን እድምታ ይተንትኑ፡፡

6. የፌዴራል መንግስት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ያወጣው አዋጅ ቁጥር 270/1994

እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣው ደንብ ቁጥር 101/1996 **በውርስ ህጉ መሠረታዊ መርሆችና ድንጋጌዎች ላይ በግልፅ ውይም በተዘዋዋሪ ያደረገው ማሻሻያ አለብለው ያስባሉሕ ለምንሕ**

ምዕራፍ ሦስት

ለመውረስ ስለሚያስፈለግ ችሎታ

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ፣

- **ለመውረስ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች**
- **ለወራሽነት የማይገባ ነው ስለሚባሉ ምክንያቶች ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው::**

3.1. ጠቅላላ መግቢያ

ሟችን ለመውረስ የሚቀርብ ሰው ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው የሚለውን ጭብጥ አንስተን ትንታኔ ከመስጠታችን በፊት የሟች ውርስ በኢትዮጵያ ሕግ በምን ሁኔታ ይፈጸማል የሚለውን ነጥብ በቅድሚያ ማየቱ አስፈላጊ ነው:: የሟች ውርስ በኑዛዜው መሠረት እንደሚፈፀም እና ሟች ኑዛዜ ያልተወ እንደሆነ ውርሱ ያለ ኑዛዜ ለሕግ ወራሾቹ እንደሚተላለፍ ተደንግጓል:: በሌላ በኩል ሟች በከፊል ንብረቱን በኑዛዜ ያወረሰ እንደሆነ በኑዛዜው ያላደላደላቸው ንብረቶች በመሉ ለሕግ ወራሾች ይተላለፋሉ:: በአጠቃላይ የሟች ውርስ ያለኑዛዜ ወይም በኑዛዜ፣ በከፊል ያሉ ኑዛዜና በከፊል በኑዛዜ ሊፈጸም እንደሚችል፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 829 መሠረታዊ መርሆችን ደንግጓል::

የሟች ወራሽ በመሆን ሊቀርቡ የሚችሉት የተፈጥሮ ሰው የሆነ አንድ ግለሰብ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ የተፈጥሮ ሰዎች እና በኑዛዜ ተጠቃሚነት ሊቀርቡ የሚችሉ ድርጅቶችና ማህበራት ጠቅለል ባለ አነጋገር ሕጋዊ ሕልውና ያላቸው የሕግ ሰዎች /Legal persons / ናቸው:: የተፈጥሮ ሰዎች ሟችን በሚወርሱበት ሥዓት ውርሱ ተፈጥሮአዊ የሆነ ውርስ Natural sucession እየተባለ እንደሚጠራ የብላክስ ሎው መዝገብ ቃላት ያመለክታል::የመውረስ ችሎታ /Capacity to succeed/ስንል፣ ሟችን በኑዛዜ ወይም ያለ ኑዛዜ ለመውረስ የሚቀርቡ የተፈጥሮ እና የሕግ ሰዎች /Legal persons/ በቅድሚያ ማሟላት የሚገባቸውን ሁኔታዎች በአጭሩ ለመግለጽ የምንጠቀምበት ጽንሰ ሀሣብ ነው:: በሟች ውርስ ለመካፈል ወራሽ የሚሆኑ ሰዎች አሟልተው መገኘት ያላበቸው ቅድመ ሁኔታ ምንድን ነው?

ወራሾች የተፈጥሮ ሰዎች በሆኑ ጊዜ ሟችን በኑዛዜም ሆነ ያለኑዛዜ ወራሽ ለመሆን ሁለት መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች እንደ መሠረታዊ መርህ ተቀምጠዋል። እነርሱም ሟች ውርስ ሲከፈት በሕይወት ያለ መሆንና ሟችን ለመውረስ የማይገባ አለመሆን ነው። ወራሾቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች በሆኑ ጊዜ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 835 የተመለከተውን አሟልተው መገኘት አለባቸው።

ከላይ እንደተገለፀው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 የእኛን አገር የውርስ ፖሊሲ የሚያንፀባርቅ ሕግ በመደንገግ በተግባር ላይ አውሏል። አንድ አንድ አገሮች የወራሾችን ዜግነት ሀይማኖት እና የትውልድ ሁኔታ ሣይቀር ለመውረስ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች በማድረግ ሕጋቸውን ቀርፀዋል። አብዛኛዎቹ አገሮች ደገሞ ሟች ሲሞት በህይወት መኖር እና በሟች ላይ ሆን ብሎ የግድያ ወንጀል አለመፈፀምን ለመውረስ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች መሆናቸውን ያሰምሩበታል። ከዚህ በመነሣት፣ በእኛ አገር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 ከተቀመጡት ሁለት መስፈርቶች ውጭ ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ያልተደነገጉ መሆኑን እና የሌሎች አገሮችን ልምድ አስቀድሞ ማየቱ ዋናውን ፍሬ ጉዳይ የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል።

ሀ. <u>ዜግነት፡</u> የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ሰው ወራሽ ሆኖ መቅረብ ይችላል ወይስ አይችልም በሚለው ነጥብ አገሮች የወሰዱትን አቋም ብንዳስስ ግብጽ፣ ቱኒዚያ እና የሶርያ የውርስ ሕግ አንድ የውጭ አገር ዜግነት ያለው ሰው በአገራቸው የሕግ ወይም የኑዛዜ ወራሽ ሆኖ ለመቅረብ የሚችለው የእርሱ አገር የውርስ ሕግ የእነርሱን አገር ዜጐች በወራሽነት እንዲቀርቡ የፈቀደ እንደሆነ መሆኑን በማረጋገጥ / The principle of reciprocity/ የሚለውን መርህ በማራመድ ነው። ስለዚህ በእነዚህ አገሮች ውስጥ ወራሽ ሆኖ የሚቀርብ የውጭ አገር ዜጋ ወራሽ የመሆን ችሎታ ያለው መሆን አለመሆኑ እልባት የሚሰጠው የእርሱ አገር የውርስ ሕግ ተመርምሮ በተመሣሣይ ሁኔታ የውጭ ዜጐች በወራሽነት እንዲቀርቡ የፈቀደ እንደሆነ ብቻ ነው።

ለ. <u>ሀይማኖት፡</u> ሟችን ለመውረስ የሚቀርበው ሰው ከሟች ጋር ተመሣሣይ ሀይማኖት መከተል ያለበት መሆኑ በእስላም አገሮች የውረስ ሕግጋት ውስጥ ተመልክቷል። በዚህም መሠረት ሙስሊም ያልሆነ ሰው ሙስሊም በሆነ ሰው ውርስ ላይ ያለ ኑዛዜ ለመካፈል እንደማይቻል ተደንግጓል። ስለሆነም ሟች ሙስሊም ከሆነ ሙስሊም ያልሆኑ ልጆቹና ሌሎች የሕግ ወራሾቹ ከሟች ውርስ እንዳይከፈሉ ይገደባሉ።

ሐ. **ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ልጅ፡**. በእስልምና ሕግ መሠረት ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ልጅ ከአባቱ ጋር የሚያገናኘው ምንም አይነት ሕጋዊ መተሳሰር እንደሌለ ስለሚቆጠር ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ልጅ በአባቱ ውርስ አባቱም በልጁ ውርስ እንደማይካፈሉ ተደንግጓል። በአጠቃላይ የእስልምና ሕግ ዜግነትን ሀይማኖትን እና የትውልድን ሁኔታን ለወራሽነት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች በማድረግ ያስቀምጣቸዋል።

የኢትዮጵያን የውርስ ሕግ መሠረታዊ መርህ ለመረዳት ሕግ አውጭው በእነዚህ ጉዳዬች ላይ የወሰደውን አቋም ስንዳስስ በመጀመሪያ የፍትሐብሔር ሕግ 836/1/ ’’ የሚቹ ወይም የወራሹ የሕግ ልጅ ወይም የዲቃላ ልጅ መሆን ወራሾችን ወይም የያንዳንዳቸውን ድርሻ ልክ ለመወሰን በሚመለከተው ምንም ዋጋ የለውም እንደሌለው የደነገገ ሲሆን። የወራሹ ጸታ፣ እድሜና ዜግነት በወራሽነት መብቱቹ ውሣኔ አሰጣጥም ላይ ምንም ልዩነት የሚያስከትሉ እንዳልሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 837 ተደንግጐ እናገኘዋለን። ጸዚህ በተ ማሪ ባክልሎችና ባወያሬሉ ሕ መት ስፔ ጸ ብኖ ው ባተወለተ ል ጸ ብኖ ጸተወለተ ል ር ጹል መብፔ ት ላ ው የሚያረጋግጥ መርህ ይደነግጋሉ።

ከእነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች የምንረዳው ከጋብቻ ውጭ መወለድ ዜግነት እድሜና ጸታ በወራሽነት መብት ላይ የሚያስከትሉት ልዩነት የሌለ መሆኑን ነው። የፍትሐብሔር ሕጉ የሀይማኖ ልዩነት በወራሽነት መብት ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ ያለ መሆን አለመሆኑን በግልጽ አልደነገገም። ስለሆነም ሀይማኖት በወራሽነት መብት ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ አለን የሚል ጥያቄ ይነሣል። ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 837 ድንጋጌ ለመረዳት እንደሚቻለው፣ ዜግነት እድሜ እና ጸታ በወራሽነት መብት ላይ አንዳችም ልዩነት እንደማያስከትሉ የደነገገ ሲሆን ይህ የሕግ ድንጋጌ ስለ ሀይማኖት አያነሣም። ሆኖም ይህ የሕግ ድንጋጌ አመልካች የሕግ ድንጋጌ እንጅ አሰሪ /Exhausitive/የሕግ ድንጋጌ አይደለም። ስለዚህ የሀይማኖት ልዩነት በወራሽነት መብት ላይ የሚያስከትለው ለውጥ የለም በማለት በማመሣሠል / Analogy/ ትርጉም መስጠት ይቻላል።በሌላ በኩል የፍትሐብሔር ሕጉ አንድ ሰው ወራሽ ለመሆን የማይችልባቸውን ምክንያቶች በግልጽ ደንግጓል። ይህ ከሆነ በሕግ በግልጽ ያልተከለከለ እንደተፈቀደ ይቆጠራል በሚለው መርህ መሠረት የሀይማኖት ልዩነት በወራሽነት መብት ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ የለም በማለት ከላይ የተነሣውን ሀሣብ ለማጠናከር ይችላል።

እንደዚሁም የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ባዕድ ሰው በሚች ውርስ እንዲካፍል ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚጋብዘው የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የሚች ወራሾችን ከሚች በሀይማኖት በመለየታቸው ብቻ ከውርስ ውጭ እንዲሆኑ በማሰብ ሕግ አውጭ ሆነ ብሎ አልፎታል በማለት ትርጉም መስጠት ሎጅካል ስለማይሆን ከላይ ካነሣናቸው የሕግ አተረጓጐም መሠረተ ሀሣቦች በመነሣት የሀይማኖት ልዩነት በወራሽነት መብት ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ለውጥ የለም ብሎ ለመደምደም ይቻላል። ከላይ ካነሣናቸው፣ ምክንያቶች በላይ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 25 የተደነገገው መርህ በዚህም ጉዳይ ገዥነትና ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ የሀይማኖት ልዩነት የወራሽነት መብትን የሚያስከለክል አይደለም።

ዜግነትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ሕግ በወራሽነት መብት ላይ የሚያስከትለው ልዩነት እንደሌለ ደንግጓል። ይህ ማለት ግን በንብረት ክፍያ ወቅት የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች በተመለከተ ከውጭ አገር ዜጐች ይልቅ ኢትዬጵያዊ ለሆኑ ወራሾች በቅድሚያ እንዲሰጡ በሕግ አልተደነገገም ማለት አይደለም።እንደሚታወቀው የውጭ አገር ሰው በመንግስት ልዩ ትእዛዝ መሠረት ካልሆነ በቀር በኢትዮጵያ የማይንቀሣቀስ ባለሀብት ሊሆን አይችልም። ይህም በፍ/ሕ/ቁ 390 ተደንግጓል። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1089 ከወራሾቹ መካከል አንዳንዶቹ የኢትዮጵያ ዜግነት አንዳንዶቹ ደግሞ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው የሆኑ አንደሆነ በኢትዮጵያ ያሉት የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች የሚቻል ቢሆን ኢትዮጵያዊ ለሆኑ ወራሾች ቅድሚያ ይሰጣሉ በማለት የደነገገው ከዚህ መሠረታዊ ፖሊሲ በመነሣት ነው።

ሆኖም የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ የውጭ አገር ዜጐች ኢትዮጵያ ውስጥ የማይንቀሣቀስ ንብረት በወራሽነት ሊረከቡ እንደሚችሉ የሕጉ ድንጋጌ ያሣያል። የውጭ አገር ዜጐች በልዩ የኑዛዜ ስጦታ ወይም በውርስ ክፍያ ወቅት የማይንቀሣቀስ ንብረት ቢደርሣቸው ምን ይደረጋል የሚለውን ጥያቄ ስናነሣ ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ ያለ መንግስት ልዩትእዛዝ በቅን ልቦና የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብት ሆኖ ከተገኘ አግባብ ያላቸው ባለስልጣኖች በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያዊ ርስቱን እንዲያስተላለፍ ሊያስገድዱት የሚችሉበት ሁኔታ ያለ መሆኑ ተደንግጓል። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 391 ይደነግጋል።

ሆኖም ይኸ ድንጋጌ አገሪቱ ካወጣቻቸው የኢንቨስትመንት ህጐችና በትውልድ ኢትዮጵያ ስለሆነ ሌላ አገር ዜትነት ስላላቸው ኢትዮጵያ ተወላጆች አስመልክቶ ከወጣ

አዋጅ ቁጥር 270/94 እና አዋጁን ለማስፈፀም ከወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 101/1996 ጋር በማገናዘብ ስራ ላይ ማዋል ይገባል። ከላይ ከተገለፁት የህግ ድንጋጌዎችና በኢንቨስትመንት ህጉ መብት የሌለው አንድ የውጭ ዜጋ በውርስ ያገኘውን የማይንቀሣቀስ ንብረት ኢትዮጵያዊ ለሆነ ሰው በሽያጭ ወይም በሌላ ሁኔታ እንዲያስተላልፍ ባለስልጣናት ሊጠይቁት ይችላሉ። ይህ የኢትዮጵያ ሕግ የውጭ አገር ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብት እንዳይሆኑ ለመገደብ በፊት የወጣው ፖሊሲ አካል እንጅ የውጭ ዜጋ የወራሽነት መብት ለመገደብ የወጣ የሕግ ድንጋጌ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። የውጭ አገር ዜጐች በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን የወራሽነት መብት ስንመለከተው ኢትዮጵያ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሣታስቀምጥ የውጭ ዜጐች በሕግ ወይም በኑዛዜ ወራሽነት እንዲካፈሉ በሯን በሰፊው የከፈተች አገር ሆና እናገኛታለን። አንዲት አገር የዜጐቿን መብትና የእራሷን ጥቅም የምታስከብረው እያንዳንዱ አገር ለሚወስደው እርምጃ ተመጣጣኝ ምላሽ በመስጠት እንደሆነ ከዓለም አቀፍ ሕግ እና አለም አቀፍ የግንኙነት መርሆች መገንዘብ ይቻላል።

ይህም /The principle of reciprocity/ በዓለም አቀፍ ሕግ ብቻ ሣይሆን በዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ መርሆች ውስጥ የተካተተና አንዲት አገር የዜጐቿን መብትና ጥቅም የምታስረክብበት መንገድ መሆኑ ተመልክቷል። ስለዚህ ኢትዮጵያዊያንን በአገራቸው በሚከፈት ውርስ ሕግ ወይም በኑዛዜ ቀርበው እነዳይካፈሉ የሚከለክል ሕግ ያላቸው አገሮች ዜጐች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ በተከፈተ ውርስ ቀርበው ወራሽ እንዲሆኑ መፍቀድ ሚዛናዊ ሆኖ አይታይም። ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ለተከፈተ ውርስ በወራሽነት የሚቀርቡት የውጭ አገር ዜጐች ኢትዮጵያዊያንን ወራሽ እንዲሆኑ የሚፈቅድ የውርስ ሕግ ካላቸው አገሮች የሚመጡትን ብቻ የሚመለከት በማድረግ/The principle of reciprocity/ በመከተል አቋሟን በማስተካከል እና ድንጋጌውን ማሻሻል ይኖርባታል። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ዜግነት ሀይማኖት ጸታ እድሜና ከጋብቻ ውጭ መወለድ በወራሽነት መብት እና በሚደርሣቸው ድርሻ ላይ ለውጥ እንደማያመጣ በውርስ ሕጓ የደነገገች ሲሆን የማደጐ ወይም የጉድፍቻ ልጅ እንደሚች ልጅ ተቆጥሮ በውርሱ መካፈል እንደሚችል በግልጽ አስቀምጣለች። በመሆኑም በማስከተል በኢትዬጵያ ሕግ ወራሽ ለመሆን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ተብለው የተደነገጉትን በዝርዝር እንመለከታለን። የፍትሐብሔር ሕጉ ሚችን ለመውረስ አስፈላጊ ናቸው በማለት ያስቀምጣቸው ትድመ ሁኔታዎች ሚች ሲሞት በህይወት መኖር እና ሚችን ለመውረስ ያልተገባ ነው አለመባል ናቸው።

3.2 ሟች ሲሞት በህይወት መኖር

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 ስንመለከት ለሟች ሀብት ወራሽ መሆን መቻል በህይወት ያለ መሆንና ለወራሽነት የማይገባ አለመሆን ነው'' በማለት ይደነግጋል። ሟች ሲሞት ወራሹ በህይወት መኖር አለበት የሚለው ቅድመ ሁኔታ ሟች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይና የሟች ውርስ በተከፈተበት ጊዜ በእውን በህይወት መገኘትን ወይም የሕግ ህልውና ያለው መሆኑን /Existance of aperson either in fact or inlaw/ የሚመለከት ነው።አንድ የተፈጥሮ ሰው ሟች ሲሞት በህይወት ነበር የሚባለው በሟቹ በጥቂት ጊዜ ዘግይቶ መሞቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው። በሟች በአንድ ሠከንድም ቢሆን ዘግይቶ መሞቱ በአጥጋቢ ማስረጃ የተረጋገጠ ሰው ሟችን ወርሶ እንደሞተ እንደሚቆጠር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826/1እና 830 ድንጋጌዎች አጣምሮ በመመልከት ለመረዳት ይችላል።

ሟች ሲሞትና የሟች ውርስ ሲከፈት በህይወት የነበሩ የተፈጥሮ ሰዎች ውርስ ከተከፈተ በኋላ ቢሞቱ የወራሽነት መብታቸውን አረጋግጠው እንደሞቱ ይቆጠራል። በመሆኑም በሟችን ውርስ የመቀበል ወይም የመተው መብታቸው ለእነርሱ ወራሾች እንደሚተላለፍ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 833 ይደነግጋል።ሟች ሲሞት በህይወት መኖር ሟችን ለመውረስ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው። ይህ የውርስ ሕግ አጠቃላይ መሪ ደንብና መርህ ሲሆን ሟች ሲሞት በእውን ያልነበሩ ሰዎች በወራሽነት የሚሣተፉበት ልዩ ሁኔታዎች እንዳሉ የፍትሐብሐር ሕጉ ድንጋጌዎች ያሣያሉ። እነዚህም ልዩ ሁኔታዎች:.

/ ሀ / የተፀነሰ ልጅ:

በገሀዱ ዓለም ሰው ሆኖ ተወልዶ በህይወት የሚኖር ነው ብለን የማንይዘው ቢሆንም የተፀነሰው ልጅ ጥቅምና ፍላጐቱ በሚሻበት ጊዜ ሁሉ እንደተወለደ መገመት ያለበት መሆኑ በፍትሐብሔር ሕጋችን ተደንግጓል። በዚህ የሕግ ግምት መሠረት የተፀነሰው ልጅ ሟች ሲሞት ያልተወለደ ቢሆንም በሟች ውርስ በወራሽነት የማካፈልበትን ሁኔታ ሕግ አውጭው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 834'' የተፀነሰ ልጅ በዚህ ሕግ ስለ ሰወች በሚለው አንቀጽ በተመለከቱት መሠረትወራሽ ለመሆን ይችላል '' በማለት ያመቻቸ በመሆኑ የተፀነሰው ልጅ ሣይወለድ በፊት በዚህ የሕግ ግምት መነሻ በወራሽነት የሚካፈልበት እና መብቱ የሚጠበቅበት ሁኔታ አለ።የተፀነሰው ልጅ: ከመወለዱ በፊት ሕጉ ባስቀመጠው ግምት አና በተሰጠው የሕግ ህልውና /Legal

existance/ የተጠበቀለት የወራሽነት መብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው በህይወት ተወልዶ ለአርባ ስምንት ሠዓት ያህል የቆየ እንደሆነ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2 እስከ 4 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በማንበብ ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ ሟች ከሞተበት ቀን አንስቶ ባሉት በሶስት መቶ ቀጥታ ውስጥ ያተወለደ እንደሆነ ነው።

በሌላ በኩል የተፀነሰው ልጅ በህይወት ተወልዶ በተፈጥሯዊ ጉድለት ምክንያት ሣይሆን በሌላ ሰው ሠራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ከአርባ ስምንት ሠዓት በፊትም ህይወቱ ቢያልፍ የወራሽነት መብቱ ተጠቃሚ እንደሚሆን እና እሱ ያረጋገጠው የወራሽነት መብት ለእናት ለአባቱ ወይም ለእነርሱ ተተኪዎች ሊተላለፍ እንደሚችል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 4/3/ እና 833 ድንጋጌዎች መልእክት አጣምሮ በማየት ለመረዳት ይቻላል። ስለዚህ ሟች ሲሞት ያልተወለደ የተፀነሰ ልጅ የሟች ወራሽ የሚሆንባቸው ከላይ በአጭሩ የገለጽናቸው ልዩ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ፤ ሟች ሲሞት የተፀነሰ ልጅ ካለና በህይወት ከተወለደ፣ ለሟች ኑዛዜ ውድቅ መሆን ምክንያት አንደሆነ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 904 የተደነገገ ሲሆን፣ ፅንሱ እስኪወለድ የሟች ወራሾች ያወረሰ ንብረት ሣይከፋፈሉ ለመቆየት እንደሚገደዱ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1063 ተደንግጓል።

ለ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች እና ማህበራት /Legal persons/

በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች ማሕበራት የሚች ወራሽ ሆነው የሚቀርቡበት ሁኔታ አለ። በአብዛኛው ወራሽ ሆነው የሚቀርቡት የኑዛዜ ተጠቃሚ በመሆን ነው። መንግስት በሕግ በኩል እንደ አንድ ሰው የሚቆጠርና በመስሪያቤቶቹ አማካይነት ከተፈጥሮው ጋር የሚስማሙትን መብቶች ሁሉ ሊያገኝና ሊሰራባቸው እንደሚችል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 394 ተደንግጓል።ከሕግ ሰዎች /Legal persons/ ውስጥ መንግስት ብቻ የሕግ ወራሽ በመሆን የሚች ዘመዶች በሌሉ ጊዜ በውርስ እንደሚካፈል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 852 ተመልክቷል። በመሆኑም ከሕግ ሰዎች ውስጥ መንግስት የሚች ያለኑዛዜ ወራሽ እና ኑዛዜም ሟቹ ከተወለት የኑዛዜ ተጠቃሚ ለመሆን የሚችል ተቋም ነው። ሌሎች የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች እና ማህበራት፣ የሚች ኑዛዜ ተጠቃሚ በመሆን ብቻ በወራሽነት የሚቀርቡ ናቸው። እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች የሚች ኑዛዜ ተጠቃሚ ለመሆን ሟች በሚሞትበት ሠዓት አስፈላጊውን የምዝገባ እና ሌሎች

ፎርማሊቲዎች አሟልተው የህጋዊ ህልውናቸው ማረጋገጫ የሆነ ሰርተፊኬት ይዘው መገኘት አለባቸው ወይ? የሚለው ነው::

በመሠረታዊ መርህ ደረጃ እነዚህ ድርጅቶች እና ማህበራት ወራሽ ለመሆን በሕጉ መሠረት ሕልውናቸው ሟች ሲሞት የተረጋገጠ መሆን አለበት በማለት መናገር ቢቻልም በልዩ ሁኔታ ሟች በሚያደርገው የኑዛዜ ስጦታ ከዚያ በፊት ያልነበረ የበጐ አድራጐት ድርጅት ማቋቋም እንደሚችል በሕጉ ተመልክቷል::በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 484/1/ የበጐ አድራጐት ድርጅት በቁም ስጦታ ወይም በኑዛዜ ስጦታ ሊቋቋም እንደሚችል የሚደነግግ ሲሆን በውርስ ሕግ ውስጥ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 835 ድንጋጌዎችም ይህንኑ የሚያመለክቱ ናቸው:: በመሆኑም በሟች የኑዛዜ ስጠታ መሠረት የሚቋቋም ግን ከዚያ በፊት ያልነበረ የበጐ አድራጐት ድርጅት የሟች የኑዛዜ ተጠቃሚ እና ወራሽ የሚሆንበትን ሁኔታ የውርስ ህጋችን አመቻችቷል::

ይህም ከውርስ ሕግ መሠረታዊ መርህ ማለትም ወራሽ ለመሆን ሟች ሲሞት በእውን መኖር ወይም ሕጋዊ ህልውና ማግኘት / Legal existance/ አስፈላጊ ነው ከሚለው በተለየ ሁኔታ ሟች ባደረገው ኑዛዜ ሟች ከሞተ በኋላ የሚቋቋም የበጐ አድራጐት ድርጅት የሟች ንብረት የኑዛዜ ወራሽ የሆነበት ሁኔታ ያለ መሆኑን እንረዳለን:: በመሆትም ጸመት ስፔ ው ሌሎኖ ባሕ ሰዎኖ በሟኖ ውርስ ተካዊቭ ባሚሆትፔ በትዛዜ ወራሽትፔ ት ቨለ ትዛዜ ባሚወርሱበፔ ስርዓፔ ትተሌለ መ ትዘብ የዚህን ጎ ቅላላ ታት ፣ አቀማመጎ በሌላ አቨትፔ መት ታ ለመተር ሞም መሞጸር ትተሌለብት ትዛቤ መቨዝ ጎ ቃሚ ትው::ስለዚህ በተራ ቁጥር አንድ እና ሁለት ከላይ በገለጽናቸው ልዩ ሁኔታዎች ሟች ሲሞት ያልነበሩ ሰዎች / የተፀነሰ ልጅ እና በሟች የኑዛዜ ስጦታ የሚቋቋም የበጐ አድራጐት ድርጅት/ የሟች ወራሽ ሆነው የውርስ ተካፋይ እና ተጠ ቃሚ የሚሆኑበት አጋጣሚ ያለ መሆኑ መረሣት የለበትም::

/ሐ/ የአብሮ ሟችወች ውርስ

በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ወራሽ ሆኖ ለመቅረብ ሟች ሲሞት በህይወት መኖር አስፈላጊ መሆኑን ከላይ አይተናል:: ብዙ ሰዎች አብረው በሞቱ ጊዜ ከእነዚህ ማንኛው በኋላ እንደሞተ ለማስረዳት የማይቻል ሲሆን የተባሉት ሰዎች ሁሉ በአንድ ጊዜ እንደሞቱ እንደሚቆጠር የፍትሐብር ሕግ ቁጥር 6 ይደነግጋል:: እዚህ ላይ ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ ሁለት ሊወራረሱ የሚችሉ ሰዎች ለምሣሌ አባትና ልጅ ባልታሰበ አደጋ በአንድ ላይ ሞተው ቢገኙ እና ማንኛው በኋላ የሞተ እንደሆነ ለማረጋገጥ

ባይቻል የውርስ ስርዓታቸው እንዴት ይመራል የሚለው ንወዉዉይህንን ጉዳይ በተመለከተ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 832 '' ሁለት ወይም ብዙ ሰዎች የሞቱ ሲሆንና ከነዚሁ ሰዎች መካከል በኋላ የሞተው የትኛው እንደሆነ ለማወቅ ያልተቻለ እንደሆነ ከአብሮ ሚችወች ሰዎች ወራሽነት ምንም ሣያገኝ የእነዚሁ ሰዎች የእያንዳንዳቸው ውርስ በመጨረሻ እንደሞተ አይነት ተቆጥሮ ይወስናል'' በማለት ይደነግጋል። ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው ከሚችወች መካከል በኋላ የሞተው የትኛው እንደሆነ ከተረጋገጠ ከላይ የተነሣው ጥያቄ ሊቀርብ የማይችል መሆኑንና በኋላ የሞተው ሰው በፊት የሞተውን ወርሶ እንደሞተ እንደሚቆጠር ነው። ከሁለቱ አንደኛው በኋላ የሞተ መሆኑን ማረጋገጥ ካልተቻለ ግን አንዱ አንዱን የመውረስ መብቱን ሣያረጋግጥ እንደሞተ እንደሚቆጠርና የእያንዳንዱ ውርስ ሲታይ እሱ የመጨረሻ ኗሪ ነው ተብሎ እንደሚገመት ከሕጉ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል።ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ አቶ አስማማው ከልጃቸው ከ ሰይፉ ጋር በመኪና ሲጓዙ በደረሰባቸው አደጋ ሁለቱም ቢሞቱ እና መጨረሻ የሞተው ማን እንደሆነ ባይታወቅ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 832 የሚለው

/i/ የአቶ አስማማውን ውርስ ስንመለከት አቶ አስማማው ከሰይፉ በኋላ እንደሞቱ አድርገህ ትገምታለህ። ነገር ግን ከሰይፉ ውርስ የመካፈል መብት የላቸውም።

/ii/ የሰይፉን ውርስ ስትመለከት ሰይፉ ከአቶ አስማማው በኋላ እንደሞተ አድርገህ ትገምታለህ ነገር ግን ከአባቱ ከአቶ አስማማው ውርስ የመካፈል መብት የለውም የሚል ገዥነት ያለው ቃል በማስቀመጥ አቶ አስማማው ከሰይፉ ውርስ እንዳይካፈል ሰይፉም ከአቶ አስማማው ውርስ እንዳይካፈል ይገድባል።

በመሆኑም የአብሮ ሚችወች ውርስ በሚታይበት ጊዜ ሕጉ አንደኛው ሌላውን ከመውረሱ በፊት እንደሞተ በመገመት አብሮ ሚችዎች እርስ በርሣቸው እንዳይወራረሱ በመገደብ ሚችን ለመውረስ ሚች ሲሞት በህይወት መኖር አስፈላጊ ነው የሚለውን መርህ ያስፈጽሚል። ሆኖም ይኽ መሠረታዊ መርህ በተተከነት የሚደረግ ወራሽነትን ይገድባል ወይ የሚለው ጥያቄ በውል መታየት አለበት።

3.3. <u>ለወራሽነት ያልተገባ አለመሆን</u>

በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ መሠረትሚች ሲሞት በህይወት የነበረ ሰው ሁል ጊዜ ሚችን ለመውረስ ችሎታ አለው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው። ሚች ሲሞት በህይወት የነበረ ሰው ሚችን ለመውረስ ማሚላት የሚገባው ሌላ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ አለ።

ይኸውም ሟችን ለመውረስ ያልተገባ አለመሆን ነው። ያለኑዛዜ ወይም በኑዛዜ ከሟች ውርስ ለመካፈል የሚመጡ ሰዎች ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኙትና በሕጉ በግለጽ የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ያልፈፀሙ መሆናቸውን በቅድሚያ መረጋገጥ ያለበት መሆኑ ተደንግጓል። ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኙ ምክንያቶች እና ድርጊቶች በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች በዝርዝር እና በግልጽ ተመልክተዋል። ከእነዚህ ህጉ በግልጽ ካስቀመጣቸው ውጭ ያሉ ድርጊቶችን እና ምክንያቶችን በመጥቀስ ዳኞች አንድን ሰው ሟችን ለመውረስ ያልተገባህ ነህ በማለት ውሣኔ ሊሰጡእንደማይችሉ ይህንን በሚመለከት የተደነገጉት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች አመልካች የሕግ ድንጋጌዎች ሣይሆኑ አሣሪ እና አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች መሆናቸውን መገንዘብና ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ሌላው በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ለወራሽነት ያልተገባ መሆን /Un worthy of succeding the deceased/ እና ከውርስ መነቀል /Disherison/ የተለያየ የሕግ ጽንሰ ሀሣቦች መሆናቸውን ነው።ለወራሽነት ያልተገባ መሆን/Un worthy of succeding the deceased/ አንድ ሰው በሕግ እንዳያደርገው የተከለከለውን ድርጊት ፈጽሞ በመገኘቱ በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ከሟች ውርስ እንዳይካፈል የወራሽነት መብቱን የሚያሣጣበት የሕግ መርህ ነው።

ከውርስ መነቀል / Disherison/ ግን በውርስ ሕግ ሟችን ለመውረስ ሙሉ ችሎታ ያለው ሰው ሟች ከውርሱ እንደማይካፈል በማሰብ ባደረገው የኑዛዜ ቃል መሠረት ለሟች የኑዛዜ ቃል ዋጋ በመስጠትና በማስፈፀም ወራሽ የሆነው ሰው ከሟች ውርስ ውጭ እንዲሆን የማደረግበትን ሁኔታ የማያመለክት የሕግ ጽንሰ ሀሣብ ነው። ስለዚህ ሟችን ለመውረስ ያልተገባ መሆን ከውርስ ሕግ ድንጋጌዎች የሚመነጭና ለአፈጻጸም መሠረቱ የሕጉ ድንጋጌ ሲሆን የውርስ መነቀል ምንጩ ሟች ያደረገው የኑዛዜ ቃል ነው። ስለዚህ ሁለቱ የተለያዩ የሕግ ጽንሰ ሀሣቦች መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል። አንድ ሰው ከሟች ኑዛዜ ከውርስ የሚነቀልበትን ዝርዝር ሁኔታ በኑዛዜ ስለሚደረግ ውርስ የሚለውን ክፍል በምናይበት ጊዜ በሰፊው የምንመለከተው ይሆናል። በፍትሐብሔር ሕጋችን ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኙ ምክንያቶች በሁለት ክፍሎች የተመደቡ ናቸው። የመጀመሪያው ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኙ የወንጀል ድርጊቶችን ፈጽሞ በፍርድ ጥፋተኛ መባለና መቅጣት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሕጉ በግልጽ የተመለከቱትን ሌሎች ተግባሮች መፈፀም ናቸው፡

3.3.1 ወንጀል ፈጽሞ መቀጣት

የውርስ ሕግ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንድ ሰው እንዳያደርግ የከለከለውን በመተላለፍ በፈጸማቸው የወንጀል ድርጊቶች ምክንያት በሟች ውርስ በተካፋይነት ከመቅረብ የሚገድቡትን በዝርዝር አስቀምጧል። ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 ድንጋጌዎች ለመረዳት እደምንችለው ለወራሽነት ከመቅረብ የሚገድቡ የወንጀል ድርጊቶች ሆነ ተብለው የተፈፀሙት ብቻ ናቸው። በቸልተኝነት የተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው አያሰኙም።ሆነ ተብለው ከተፈፀሙት የወንጀል ድርጊቶች ውስጥ ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኙን ሟችን ሆነ ብሎ መግደሉ ወይም ለመግደል መሞከሩ በፍርድ ተረገግጦበት መቀጣት፣ በቀጥታ የስጋ ዝምድና አቆጣጠር ሥር ያሉ የሟችን ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች፣ ወይም ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች አንዳቸውን ሆነ ብሎ መግደሉ ወይም ለመግደል መሞከሩ ተረጋግጦበት የተቀጣ፣ የሟችን ባል ወይም ሚስት ሆን ብሎ መግደሉ ወይም ለመግደል መሞከሩ ተረጋግጦበት መቀጣት፣ ሟችን ወይም የሟችን ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ወይም ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹን የሟችን ባል ወይም ሚስት ከአስር ዓመት በላይ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ፍርድ በሚያስቀጣ ወንጀል በሀሰት የከሰሰና በሀሰት ክስ ማቅረቡ በፍርድ ተረጋግጦበት የተቀጣ፡. ሟችን ወይም የሟችን ተወላጆች እነደዚሁም ወደላይ በሚቆጠሩ የሟች ወላጆች ወይም የሟች ባል ወይም ሚስት ከአስር ዓመት ጽኑ አስራት በላይ ወይም በሞት ፍርድ የሚያስቀጣ ወንጀል ተከስሰው ቀርቦ የሀሰት የምስክርነት ቃል የሰጠና የሀሰት የምስክርነት ቃል መስጠቱ ተረጋግጦበት የተቀጣ ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው እንደሚባል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 ድንጋጌዎች ያሣያሉ።

ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው የሟችን ወደ ጐን የሚቆጠሩ የስጋ ዘመዶች ለምሣሌ እህት፣ ወንድም፣ አክስና አጐት ሆነ ብሎ መግደሉ ወይም ለመግደል መሞከሩ ተረጋግጦበት የተቀጣ ወይም የሟችን የጋብቻ ዘመዶች ሆነ ብሎ በመግደሉ ወይም ለመግደል በመሞከሩ የተቀጣ ሟችን የመውረስ ችሎታ ያለው መሆኑንና ለመውረስ ያልተገባ ነው እንደማይባል ነው።ከዚህ በተጨማሪ ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ ወይም በሞት ፍርድ የሚያስቀጣ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት በሟች የጐን የስጋ ዘመዶች ወይም የጋብቻ ዘመዶች ላይ የሀሰት ክስ ቢያቀርብ ወይም በተከሰሰበት ጉዳይ ቀርቦ የሀሰት የምስክርነት ቃል መስጠቱ ተረጋግጦ ቢቀጣ ሟችን ከመውረስ የሚገደብ አለመሆኑን ነው።እንደዚሁም ሟችን ተወላጆቹን ወይም ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹን ወይም የሟችን ባል ወይም ሚስት በሀሰት የከሰሰው ወይም በተከሰሰበት ጉዳይ የሀሰት

የምስክርነት ቃል የሰጠው ከአስር ዓመት በሚያንስ ጽኑ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ጉዳይ እንደሆነ የሀሰት ክስ ማቅረቡ ወይም በሀሰት መመስከሩ በፍርድ ተረጋግጦ ቢቀጣም እንኳን ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው ተብሎ ከሟች ውርስ ከመካፈል የሕጉ ድንጋጌ የሚከለክለው አይደለም።

ከዚህ ጋር መታየት ያለበት ፍሬ ጉዳይ ከላይ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ አምስት የተዘረዘሩትን የወንጀል ድርጊቶችን ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኙት ግለሰቡ የወንጀሉን ድርጊት የፈፀመው ሟች ከመሞቱ በፊት የሆነ እንደሆነ ነው። ሟች ከሞተ በኋላ ከላይ የዘረዘርናቸውን ድርጊቶች የፈፀመ ሰው ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው እንደማይባል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 839 ድንጋጌዎች ያመለክታሉ። ለዚህም መሠረታዊ ምክንያቱ ለሟች ወራሽ የሆነ ሰው ሟችን የመውረስ ችሎታ አለው ወይስ የለውም የሚለው ጥያቄ መጠየቅ ያለበት የሟች ውርስ በተከፈተ ጊዜ ነው። የሟች ውርስ የሚከፈተው ከዚህ ዓለም ህይወቱ ባለፈችበት ቅጽበት መሆኑን አይተናል። የሟች ውርስ ሲከፈት የተዘረዘሩትን የወንጀል ድርጊቶች ቢፈጽም የመውረስ ችሎታውን የሚያጣበት ሁኔታ እንደሌለ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 839 ድንጋጌዎች ከሌሎች የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል።

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 ድንጋጌዎች በአቀራረጽና በአፈጻጸማቸው ምን አይነት ችግር እና ክፍተት ይታይባቸዋል የሚለውን ነጥብ ስንመለከት በመጀመሪያ የድንጋጌው ርእስ '' ወንጀሎች ወይም ቅጣቶች'' የሚል ሲሆን፣ በይዘቱ ግን አንድ ሰው ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚባለው ድርጊቱን በመፈፀሙ ብቻ ሣይሆን በድርጊቱ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኝነቱ ፍርድ ቤት ተረጋግጦበት የተቀጣ መሆኑ አስፈላጊ መሆኑን የሚደነግግ ነው። በመሆኑም በርእሱ እና በይዘቱ መካከል የመልእክት አለመጣጣም ያለ መሆኑን እንመለከታለን።በሁለተኛ ደረጃ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጠር 838 የሟች የወራሾች አንድን ሰው ከላይ የዘረዘርናቸውን የወንጀል ድርጊቶች በሟች በተወላጆቹ ወይም ወደ ላይ በሚቆጠሩ ወላጆቹ በሟች ባል ወይም ሚስት ላይ የፈፀመ ስለሆነ ለመውረስ ያልተገባ ነው ብለው ለመከራከርና በክርክሩ ለመርታት ይዘው መቅረብ ያለባቸውን የማስረጃ አይነት ወስኖታል። በሟች በተወላጆቹ ወይም ወደ ላይ በሚቆጠሩ ወላጆቹ በሟች ባል ወይም ሚስት ላይ በሕጉ የተገለጹትን ወንጀሎች መፈፀሙ በፍርድ ተረጋግጦበት በወንጀል ሥራው የተቀጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ ጉዳዩን ያየው የወንጀል ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ በማስረጃነት መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል።

ይህ ደግሞ የአፈጻጸም ችግር ያስከተለ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም:: ምክንያቱም ግለሰቡ የወንጀሉን ድርጊት ለመፈፀሙ አጥጋቢ ማስረጃ እያለ ከወንጀሉ ቅጣትና ከፍርድ የሚያመልጥባቸው እና የወንጀሉ ክርክር ከፍርድ በፊት የሚቆረጥባቸው ሁኔታዎች በርካታ በመሆናቸው ነው:: ከነዚህ ምክንያቱች ጥቂቶቹን ለመጠቆም:.

ሀ) የተያዘው የወንጀል ክርክር ፍርድ ከማግኘቱ በፊት ተከሣሹ ከሞተ የወንጀሉ ክርክር ባለበት ሁኔታ ተቋርጦ መዝገቡ እንደሚዘጋ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 223 ይደነግጋል:: ይህንን ድንጋጌ መነሻ በማድረግ ሁኔታዎችን በምሣሌ ለማየት ብንሞክር:. አቶ ወንድወሰን መኪና የምገዛበት ገንዘብ ከለከልከኝ በሚል ቂም በመያዝ ሆን ብሎ አስቦና ተዘጋጅቶ አባቱን አቶ ገ/እግዛብሔርን ገደለ:: ወንድወሰን ይህንን የፈፀመው በቂ የሰው ማስረጃ ባለበትና በቴክኒክ ምርመራም ሟች ገ/እግዛብሔር የሞቱት ከወንድወሰን እጅ በኤግዚቪት በተያዘው ሽጉጥ በተተኮሰ ጥይት መሆኑ ተረጋግጧል::

i/ ወንድወሰን ሟችን ከገደለ በኋላ ወደ ፍርድ ከመቅረቡ በፊት እራሱን ቢገድል ወይም በተፈጥሮ ሁኔታ ቢሞት ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው ይባላልን ወንድወሰን የአቶ ገ/እግዛብሔር ውርስ ሲከፈት በህይወት ነበረ:: ሟችን ወርሶ ነው የሞተው ወይስ አይደለም የወንድወሰን ወራሾች የእሱን የወራሽነት መብት ተጠቅመው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 833 መሠረት በአቶ ገ/እግዛብሔር ውርስ እንዳይካፈሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 ድንጋጌዎች ይገድባሉ ወይስ አይገደቡም::

/ ii/ ወንድወሰን ክስ ቀርቦበት ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ አባቱን በቂም በቀል መግደሉን በዝርዝር አምኖ ጥፋተኛነቱን ካረጋገጠ በኋላ የችሎቱ የመነሻ ሰዓት በመድረሱ ለብይን ቀጠሮ እንደተሰጠው እራሱን ቢገድል ወይም ሌላ ሰው ቢገድለው ወይም በህመም ምክንያት ቢሞት ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው ይባላል ወይስ አይባልም?

iii/ ወንድወሰን ክስ ከቀረበበትና የከሣሽ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ብይን ሰጥቶ እሱም የመከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለት በጽሁፍ ማረጋገጫ ከሰጠ በኋላ ቢሞት የወንጀሉ ክርክር ስለሚቋረጥ በውርሱ ክርክር ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ ምንድን ነው?

/ iv/ የከሣሽና የወንድወሰን ማስረጃ ከተሰማና የመፋረጃ ሀሣባቸውን ካቀረቡ በኋላ ፍርድ ቤቱ ወንድወሰን በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ነው ወይም አይደለም የሚለውን ፍርድ ለመስጠት ቀነ ቀጠሮ እንደሰጠ ወንድወሰን ቢሞት የወንጀሉን ጉዳይ የያዘው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ትእዛዝ ቢኖር ክርክሩን አቋርጦ መዝገቡን መዝጋት እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 214 ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም ከላይ ባየናቸው ሁኔታዎች ወንድወሰን ሆነ ብሎ አባቱን ለመግደሉ በቂ ማስረጃ አለ፡፡ ከፍርድ በፊት እሱ በማናቸውም መልኩ ከሞተ የወንጀሉ ክርክር ይቋረጣል፡፡ የሟች ሌሎች ወራሾች ይህንን የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ እያላቸው ወንድወሰን ከፍርድ በፊት በመሞቱና የወንጀሉ ክርክር በዚህ ምክንያት በመቆሙ የወንጀል ችሎት የሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ በማስረጃነት ለማቅረብ ስላልቻሉ ብቻ ወንድወሰን የሟች አባቱን ለመውረስ ያልተገባ አይባልም በማለት የወንድወሰን ወራሾች የእሱን የመውረስ መብት ተጠቅመው በአቶ ገ/እግዛብሔር ውርስ እንዲካፈሉ ሕግ አውጭው የፈቀደበት ምክንያት ምንድን ነው?

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 በማስረጃነት የሚጠይቀው ግለሰቡ በወንጀል የተቀጣበት የፍርድ ቤት ውሣኔ ነው፡፡ ሟች ከፍርድ በፊት መሞቱ የወንጀሉን ክርክር ለዘለቄታው የሚያቋርጥ ምክንያት ሲሆን ሌሎች የወንጀሉን ክርክር ለጊዜው ለማቋረጥ ምክንያት የሚሆኑ ሁኔታዎችም አሉ፡፡ እነርሱም

ሀ/ ተከሣሹ ሊያዝ እና ለፍርድ ሊቀርብ አለመቻሉ ወይም ተይዞ ለፍርድ ከቀረበ በኋላ ያመለጠ እንደሆነ ተከሣሹ በሌለበት የወንጀሉ ክርክር ሊታይ የሚችለው የተከሰሰበት ወንጀል ከአስራ ሁለት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ የሆነ እንደሆነ መሆኑን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 161/2/ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በሀሰት በሟች ላይ ወይም በተወላጆቹ ወደ ላይ በሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም ባል ወይም ሚስት ላይ ክስ ያቀረበ ሰው በሀሰት ክስ ማቅረብ የመጨረሻ ቅጣት አምስት ዓመት ጽኑ እስራት መሆኑ በአዲሱ የወንጀል ህግ አንቀፅ 452 ተደንግጓል፡፡ በእነዚህ ሰዎች ላይ የሀሰት ምስክርነት በመስጠቱ ቢወነጀል ህጉ አንቀፅ 453 (ሀ) የተከሰሰ ሰው እና ከላይ ከዘረዘርናቸው የሟች ዘመዶች ወይም ሟችን በደም ፍላት በመነሣሣት በመግደሉ የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 541 በመተላለፍ የተከሰሰ ሰው በቁጥጥር ስር ካልዋለ ክርክሩ በሌለበት ሊታይ የማይችል በመሆኑ ከሕግ በመሰወሩና በሌለበት የጥፋተኝነት ውሣኔ እንዳይሰጥ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ቅጥር 162(2) ስለሚገድብ በዚህ

ምክንያት ጥፋተኛ የተባለበት ማስረጃ ሊቀርብለት ስለማይችል ብቻ በሚች ውርስ በወኪሉ አማካኝነት እንዲካፈል እና ሚችን ለመውረስ ያልተገባ አይደለም ማለት ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?

ለ/ የወንጀሉ ክርክር በሌሎች የሥነ ስርዓት ምክንያቶች እና ክርክር ወቅት በሚታዩ ግድፈቶች ይቋረጣል። ለምሣሌ የምስክሮች አለመቅረብ ክስ ተሻሽሎና ተስተካክሎ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ተሻሽሎና ተስተካክሎ ባለመቅረቡ ተከሣሹ ለጊዜው ከእስር እንዲለቀቅና ክርክሩ ለጊዜው እንዲቋረጥ፣ የሚደረግበት ሁኔታ አለ። በእነዚህ ምክንያቶች የጥፋተኝነት ውሣኔ ስላልቀረበበት ብቻ ሚችን ለመውረስ የተገባ ነው ተብሎ በሚች ውርስ እንዲካፈል መፈቀድ አለበት ወይ ?ህግ አውጭው አንድን በኑዛዜ ወይም ያለ ኑዛዜ የሚች ወራሽ ሆኖ የቀረበን ሰው በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ሚችን ለመውረስ ያልተገባህ ነህ ለማለት በወንጀሉ የተቀጣበት ማስረጃ መቅረቡ የግድ አስፈላጊ ነው በማለት በፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 838 የደነገገው አንድ ሰው በሕጉ የተቀመጡትን የወንጀል ድርጊቶች አንዱን ስለመፈፀሙ በበቂ ሁኔታ ከተገቢው ጥርጣሬ ውጭ በማስረጃ ሣይረጋገጥበት የወራሽነት መብቱን አላግባብ እንዳያጣ የወራሹን መብትና ጥቅም ለመጠበቅ በማሰብ ነው።

ሆኖም የውርስ ክርክር አንድ ሰው ሚችን ለመውረስ መብት አለው የለውም፣ ሚችን ለመውረስ መብት አለው ከተባለው ድርሻው ምን ያህል ነው የሚሉትን ጭብጦች ለማስወሰን የሚቀርብ የፍትሐብሔር ጉዳይ ነው። ይህ ከሆነ ሕግ አውጭው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 838 በተዘረዘሩት ወንጀሎች አንድን ወንጀል በመፈፀሙ የተከሰሰ ሰው ወንጀሉን ስለመፈፀሙ የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ እያለ በፍርድ ጥፋተኛ ከመባሉ በፊት የወንጀሉ ክርክር የሚቋረጥባቸው ብዙ ምክንያቶች ያሉ መሆኑን በማሰብ የሚች ሌሎች ወራሾች እነዚህን በቂ እና አሣማኝ ማስረጃዎች በፍትሐብሔሩ ችሎት ማስረጃ አድርገው በማቅረብ የሚሟገቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነበረበት። የፍትሐብሔሩን ክርክር በወንጀል ችሎት በሚሰጠው ፍርድ ውጤት ጥገኛ ማድረጉ የወንጀሉ ክርክር ከላይ ባየናቸው የሕግና የፍሬ ጉዳይ ምክንያቶች በሚቋረጥበት ወቅት በሕጉ የተከለከለውን ድርጊት የፈፀሙ ሰዎች የሚች ወራሽ ሆነው እንዲካፈሉ የሚያደርግ በመሆኑና ይህም ሚዛናዊ ባለመሆኑና ከርትእ እና የፀሀ ልቦና ፍርድ ጋር የሚቃረን ስለሚሆን ይህ የሕግ ድንጋጌ መሻሻል ካለባቸው ድንጋጌዎች ውስጥ አንደኛው ነው የሚል አመለካከት አለ? ዕርስዎስ ምን ይላሉ?

በአጠቃላይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 ድንጋጌዎች መሠረት አንድ ሰው የተዘረዘሩትን የወንጀል ድርጊቶች መፈጸሙ ብቻውን ሚችን ለመውረስ ያልተገባ ነው አያሰኘውም። ሚችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚባለው በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት በፍርድ ጥፋተኝነቱ ከተረጋገጠ ብቻ ነው። በመሆኑም የሕጉ አቀራረጽ እና ይዘት መስተካከል አለበት በማለት ለመተቸት ብችልም ሕጉን የማሻሻል ስልጣን ያለው አካል እስኪያሻሽለው ጊዜ ድረስ የህጉን ድንጋጌ ማክበር እና መከተል እንደዚሁም በተግባር ላይ ማዋል እንደሚጠበቅብን መዘንጋት አያስፈልግም። በመሆኑም አንድን ግለሰብ ሚችን ለመውረስ ያልተገባ ነው ብለው ለመከራከር የሚቀርቡ ወገኖች ግለሰቡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 በተዘረዘሩት የሚች የስጋ ዘመዶች ወይም ባል ወይም ሚስት ላይ በሕጉ ከተገለጹት የወንጀል ድርጊቶች አንዱን ፈጽሞ በፍርድ የተቀጣ ስለመሆኑ ማስረዳት አለባቸው።

ከዚሁ ጋር በማያያዝ የምንመለከተው ሚች ይህንን እያወቀ ማለትም የወንጀል ድርጊት መፈፀሙን እያወቀ በግልጽ ጽሁፍ ይቅርታ አድርጐለት የሆነ እንደሆነ ወይም ድርጊቱን መፈፀሙን እያወቀ ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ በኑዛዜ ስጦታ ሰጥቶት ከሆነ የወራሽነት መብቱን እንደማያጣና ሚችን ለመውረስ ያልተገባህ ነው ተብሎ ከሚች ውርስ ውጭ እንደማይሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥርግ 841 ይደነግጋል። በሚች በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ የተደረገ ይቅርታ በህግ የተከለከለውን የወራሽነት መብትና ችሎታ የሚያስገኝ መሆኑን እንመለከታለን።

3.3.2 ሌሎች ለወራሽነት ያልተገባ ነው የሚያሰኙ ምክንያቶች

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 የተዘረዘረውን የወንጀል ድርጊት ሚች ከመሞቱ በፊት መፈጸምና ይኸው በፍርድ ተረጋግጦ መቅጣት ሚችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኝ የመጀመሪያው ምክንያት መሆኑን በዝርዝር ተመልክተናል።ከዚህ በተጨማሪ የወራሽነት መብትን የሚያሣጡ ሌሎች ምክንያቶች መኖራቸውን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840 ድንጋጌዎች ለመረዳት እንችላለን። እንዚህም ሚች ኑዛዜ እንዳያደርግ ወይም ኑዛዜውን እንዳይለውጥ ወይም ሆነ ብሎ ማበላሸት እንዳይገኝ ማድረግና ማጥፋት መሆናቸው በሕጉ ድንጋጌ ተመልክቷል። በፍትሐብሔር ሕጉ ሚችን ለመውረስ የማይገባ ነው የሚያሰኙትን ሌሎች ምክንያቶች በሁለት ከፍሎ አስቀምጧቸዋል እነርሱም፡.

ሀ. ሚች ኑዛዜ እንዳያደርግ እንዳይሽር ወይም እንዳይለወጥ መከልከል

’’ የሚችን የሰውነት ሁኔታ ምክንያት በማድረግ አውራሹ ከመሞቱ በፊት በአሉት ሶስት ወር ውስጥ፣ ኑዛዜ እንዳያደረግ እንዳይለወጥ ወይም አንዳይሽር የከለከለ ሰው ’’ ሚችን የመውረስ መብቱን እንደሚያጣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840/ሀ/ ይደነግጋል። የዚህን የሕግ ድንጋጌ መልእክት ስንመረምረው በኑዛዜ ወይም ያለ ኑዛዜ የሚች ወራሽ የሆነ ሰው የሚችን ኑዛዜ የማድረግ ኑዛዜውን የመለወጥ እና የመሻር ፍፁማዊ መብት በማክበር መልካም ሥነ መግባር ማሣየት የማጠበቅባቸው መሆኑንና የሚችን መብት እንዲያከብሩ ግዴታ የተጣለባቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው።

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840/ሀ/ ድንጋጌ መሠረት ሚችን ኑዛዜ እንዳያደርግ ኑዛዜውን አንዳይለውጥ ወይም እንዳይሽር የከለከለ ሰው የወራሽነት መብቱን የሚያጣው ሁለት መሠረታዊ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው። የመጀመሪያው ሚች ኑዛዜ እንዳያደርግ እንዳይለውጥ ወይም አንዳይሽር የከለከለው ከመሞቱ በፊት ባሉት ሶስት ወር ውስጥ የሆነ እንደሆነ ነው። ወራሹ ሚችን ኑዛዜ እንዳያደርግ ኑዛዜውን እንዳይለውጥ ወይም እንዳይሽር የከለከለው ሚች ከመሞቱ በፊት ካሉት ሶስት ወራት ውጭ ማለትም ከመሞቱ ከአንድ ዓመት ወይም ከአራት ወር በፊት ከሆነ ሚችን ለመውረስ ያልተገባ ነው እንደማይባል የህጉ ድንጋጌ ያስረዳል።ሕግ አውጭው ሚች ከመሞቱ በፊት በነበሩት ሶስት ወራት ውስጥ ኑዛዜ ለማድረግ ለመለወጥ እና ለመሻር ነጻ ከነበረ ከዚያ በፊት የተደረገበት ክልከላ መሠረታዊ መብቱን በመጠቀም ኑዛዜ ከማድረግ፣ ኑዛዜውን ከመለወጥ ወይም ከመሻር የሚገድበው አይደለም በሚል ሀሣብ ክልከላው የተደረገበትን ጊዜ ትኩረት በመስጠት በሕጉ ድንጋጌ ውስጥ በግልጽ ያመለከተው መሆኑን እንረዳለን።

ሁለተኛው ደግሞ ሚችን ኑዛዜ የማድረግ የመለወጥ እና የመሻር መብቱን እንዳይጠ ቀም የከለከለው የሰውነቱን ሁኔታ ምክንያት በማድረግ እና በመጠቀም የሆነ እንደሆነ ንወዉዉዉ እዚህ ላይ በሕጉ የሚችን የሰውነት ሁኔታ ምክንያት በማድረግ የሚለው ምን አይነት ሁኔታዎችን የሚያጠቃልል ነው የሚለው ጥያቄ መነሣቱ የማይቀር ነው። ለዚህ ድንጋጌ የተለያዩ ትርጉሞችና አመለካከቶች ሲሰጡ ይስተዋላሉ። የመጀመሪያው ሚችን በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ በማስገባትና በቁጥጥር ስር በማዋል ከመሞቱ በፊት ባሉት ሶስት ወራት ውስጥ ኑዛዜ እንዳያደርግ እንዳይለውጥ ወይም እንዳይሽር በከለከለው ወራሾች ላይ የሕጉ ድንጋጌ ተፈጻሚነት አለው የሚለውና ብዙወቹ የሚስማሙበት ነው።

ሌላው የሚችን የሰውነት ሁኔታ ምክንያት በማድረግ የሚለው ድንጋጌ ሚች ባደረበት ህመም ብርታት ከአልጋ መነሣት እና መንቀሣቀስ በማይችልበት ወቅት ኑዛዜ ለማድረግ ወይም ያደረገውን ኑዛዜ ለመለወጥ ወይም ለመሻር ፈልጌ ሁኔታወቹን እንዲያመቻችለት ወራሾቹን ሲጠይቅ እንቢተኛ በመሆን ኑዛዜ እንዳያደርግ እንዳይሽር ወይም አንዳይለውጥ ከገደቡት ለወራሽነት ያልተገቡ ናቸው የሚለው አከራካሪ ሀሣብ ነው::ይህንንም ለመረዳት ምሣሌዎችን አንስተን ብንመለከት ሚች እጅ እና እግሩን ማንቀሣቀስ በማይችልበት ሁኔታ ኑዛዜ ለማድረግ ፈልጌ የዩንቨርስቲ ተማሪ የሆነውን ልጁን ኑዛዜውን ቃል በቃል እንዲጽፍለት እና ሌሎች ሴቶች ልጆቹ በምስክርነት ሰምተው እንዲፈርሙ ሲጠይቃቸው ተማሪው ልጁ ቃሉን በወረቀት ለመጻፍ እንቢተኛ ቢሆን እና ሌሎችም ምስክር ለመሆን አንፈልግም ቢሉ ከዚህ ባሻገር ሚችን ሌላ ሰው እንዳይጐበኘው በተለያየ ዘዴ እየፈጠሩ ሚች በምንም መንገድ ኑዛዜ የሚያደርግበትን ሁኔታ ቢያጣብቡ የሚችን የአካል መዳከም ምክንያት በማድረግ ኑዛዜ እንዳያደርግ እንዳይለውጥ ወይም እንዳይሽር ከልክለውታል ለማለት አይችልም ወይ የሚለው ጥያቄ ሲነሣ የተለያዩ መልሶች ይቀርባሉ::

አንደኛው ኑዛዜውን ለመጻፍ ወይም በኑዛዜ ምስክር ላለመሆን እንቢተኛ መሆናቸው የሚችን ኑዛዜ የማድረግ መብት በቀጥታ የሚገድብ ባለመሆኑ ለወራሽነት ያልተገባ አያሰኝም የሚል ሲሆን ሌላው ደግሞ፣ የሚችን የሰውነት ሁኔታ ምክንያት በማድረግ የሚለው የሕጉ ድንጋጌ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ሚች መብቱን እንዳይጠቀም በተዘዋዋሪ የሚደረገውን ማእቀብ የሚያጠቃልል ነው::ምክንያቱም የሚችን የአካል ጥንካሬ መዳከም በመጠቀም ሚች ኑዛዜ ለማድረግ ለመለወጥ ወይም ለመሻር የሌላ ሰው እርዳታ ማግኘቱ ወሳኝ እና አስፈላጊ ሆኖ እያለ እርዳታ አነዲያደርግለት በሚች የቀረበውን ጥያቄ በመቃወም እና ሚች መብቱን የሚጠቀምበትን ሁኔታ በማጣበብ ሚቹ ኑዛዜ እንዳየደርግ፣ እንዳይለወጥ ወይም እንዳይሽር በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ማዕቀብ የጣለ ሰው በሠራው ለመልካም ፀባይ እና መልካም ሥነ ምግባር ተቃራኒ የሆነ ሥራ መቀጣት እንጅ ተጠቃሚ ሊሆን አይገባውም:: ስለዚህ በማናቸውም መንገድ የሚቹን አካል መዳከም ምክንያት እና መጠቀሚያ በማድረግ ሚች ኑዛዜ ለማድረግ ለመለወጥ ወይም ለመሻር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች እንዲሰጠው ሲጠይቅ እንቢተኛ በመሆን ወይም ሁኔታዎችን እንዲያመቻችለት ሚች ያቀረበውን ጥያቄ ሆነ ብሎ የከለከለ እና ሚች ኑዛዜ ለማድረግ ለመለወጥ ወይም ለመሻር እየፈለገና እየጠየቀ በአካሉ ድክመት ብቻ ሣይፈጽመው እንዲሞት ያደረጉ ሰዎች

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840/ሀ/ መሠረት የወራሽነት መበታቸውን ያጣሉ በማለት አመለካከታቸውን ይገልጻሉ::

ከላይ እንዳየነው የሚችን ''የሰውነት ሁኔታ ምክንያት በማድረግ '' የሚለው ሀረግ እንዴት መተርጐም አለበት በሚለው ነጥብ ዙሪያ አንድ ወጥ የሆነ አመለካከት የለም:: ከኑሮ ልምድ እንደምናውቀው አብዛኛው ጊዜ ሰዎች ኑዛዜ የሚያደርጉት በህመም ምክንያት አካላቸው ሲዳከም እና የመሞቻ ጊዜዬ እየተቃረበ ነው የሚል ስጋት ሲያድርባቸው ነው:: ኑዛዜ በአብዛኛው ሰወች የአልጋ ቁራኛ ከሆኑ በኋላ የሚፈጸም በመሆኑ ሚች አካሉ በህመም በተዳከመበት እና ተንቀሳቅሶ ምንም ነገር ለማድረግ በማይችልበት ሁኔታ ኑዛዜ ለማድረግ ለመለወጥ ወይም ለመሻር ፈልጐ ምስክርና ፀሐፊ እንዲጠራለት ወይም የመጨረሻውን የኑዛዜ ቃሉን በጽሁፍ እንዲጽፍለትና እንዲያስፈርመው እየጠየቀው ወይም ወረቀትና እስክርቢቶ እንዲሰጠው እየተማፀነ እንቢተኛ የሆነ ሰው በአጠቃላይ ሚች በመንቀሳቀስ የፈለገውን ተግባር /ኑዛዜ/ ለማድረግ ለመለወጥ ወይም ለመሻር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማሟላትና ለማቅረብ የአካል ብቃት የሌለው መሆኑን በመጠቀም እና አስፈላጊ እርዳታ ባለመስጠት ሚች ኑዛዜ እንዳያደርግ እንዳይለውጥ ወይም እንዳይሽር ገደብ የጣሉና መልካም ሥነ ምግባር የጐደላቸው ሰዎች በፈፀሙት ሞራል እና ግብረአበርነት ባልዳሰሰው ድርጊታቸው በሚች ውርስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሕግ አውጭው ሀሣብና ፍላጐት ያለው አይመስለኝም::

በመሆኑም ሕግ አውጭው የሚች ወራሾች ሊፈጽሙት የሚገባቸውን እና የሚችሉትን የሚችን የመጨረሻ ቃል በማክበር እንዲፈጽሙ ለማስጠንቀቅ በተቃራኒው የሚችን የአካል መዳከም በመጠቀም ኑዛዜ ለማድረግ ለመለወጥ ወይም ለመሻር እየፈለገ እና እየጠየቀ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና መፈፀም እየቻሉ ሆነ ብለው እንቢተኛ በመሆን ኑዛዜ እንዳያደርግ እንዳይለውጥ ወይም አንዳይሽር ያደረጉ መልካም ሥነ ምግባር የጐደላቸውን የሚች ወራሾች ለመቅጣትና ሌሎችም ሊፈጽሙ የሚገባቸውን እና የሚችሉትን የሚችን መጨረሻ ፈቃድ በመፈፀም ሚች ኑዛዜ የማድረግ የመለወጥ እና የመሻር መበቱን ከአካሉ መዳከምም በመብቱ እንዲጠቀምበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያለባቸው መሆኑን ለማስጠንቀቅ በማሰብ ነው '' የሚችን የሰውነት ሁኔታ ምክንያት በማድረግ'' ኑዛዜ እንዳያደርግ እንዳይለውጥ ወይም እንዳይሽር የከለከለ የወራሽነት መብቱን ትተሚቦኃ ቸተት ል:: የዚህን ድንጋጌ የአፈጻጸም አድማስ ስፋት እና አተረጓጐም ሕግ አውጭው ሊደርስበት ካሰበው ግብ እና አላማ ጋር ለማጣጣም በተግባር ላይ ለማዋል ተማሪዎች ውይይት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

ለ. የሚችን የመጨረሻ ኑዛዜ ማበላሸት፣ ማጥፋት ወይም እንዳይገኝ ማድረግ::

በሁለተኛ ደረጃ የፍትሐብሔር ሕጉ ለወራሽነት ያልተገባ የሚያሰኝ ሌሎች ምክንያቶች ብሎ ያዘዘው የሚቹን የመጨረሻ ጉዛዜ እንዳይገኝ ማድረግና ማጥፋት ነው:: ይህንን አስመልክቶ፣''አስቦ ያለ ሚቹ ፈቃድ የሚችን የመጨረሻ ኑዛዜ ያበላሸ እንዳይገኝ ያደረገ ያጠፋ ወይም ጉዳዩን በማወቅ በሀሰት ኑዛዜ የተጠቀመ የወራሽነት መብት ያጣል'' በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840/ለ/ ይደነግጋል::ከዚህ የሕግ ድንጋጌ ቃልና መልእክት የምንረዳው ሣያውቅ በአጋጣሚ ወይም በቸልተኝነት የሚችን የመጨረሻ ኑዛዜ ያበላሸ እንዳይገኝ ያደረገ ወይም ያጠፋ ሰው ሚችን የመውረስ መብቱ የማይገፈፍ መሆኑ ነው:: ሕግ አውጭው ትኩረት የሰጠው የሚች የመጨረሻ ቃል ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው በማሰብ ሆነ ብለው ኑዛዜው በማናቸውም መልኩ በማስረጃነት እንዳይቀርብ ለማድረግ ያበላሹ እንዳይገኝ ያደረጉ ወይም ባጠፉ የሚች ወራሾች ላይ ነው::በሁለተኛ ደረጃ በሚች ሙሉ ፈቃድ እና ትእዛዝ መሠረት የሚችን የመጨረሻ ኑዛዜ ያበላሸ እንዳይገኝ ያደረገ ወይም ያጠፋ የሚች ወራሽ ድርጊቱን የፈፀመው በመች ፈቃድ መሆኑን ካስረዳ ለወራሽነት ያልተገባ ነው እንደማይባል የሕጉ ድንጋጌ ያስረዳል::

በሶስተኛ ደረጃ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ነጥብ የሚችን የመጨረሻ ኑዛዜ የሚለው ቃል ነው:: የሚች የመጨረሻ ኑዛዜ የሚባለው ሚች በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 898 እስከ 900 በተደነገገው መሠረት ያልሻረውን የኑዛዜ ቃል ማጥፋት፣ ማበላሸት ወይም እንዳይገኝ ማድረግ የወራሽነት መብትን የሚያሣጣ መሆኑን ያመለክታል:: በተቃራኒው ከላይ በተጠቀሱት የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ሚች በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሻረውን ኑዛዜ ሆነ ብሎ ያለሚች ፈቃድ ማጥፋት ማበላሸት ወይም እንዳይገኝ ማድረግ የወራሽነት መብትን የማያሣጣና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840/ለ/ የሚሸፈን አለመሆኑን ነው::ሕግ አውጭው ያለሚች ፈቃድ የሚችን የመጨረሻ ኑዛዜ ሆነ ብሎ ያጠፋ ያበላሸ ወይም እንዳይገኝ ያደረገ በሚች ውረስ እንዳይካፈል የከለከለበት ምክንያት ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ ስንመለከት በግልጽ ወይም በተናዛዡ እጅ ጽሁፍ የተደረገን ኑዛዜ ለማስረዳት የኑዛዜ ተጠቃሚው ማቅረብ የሚገባው የኑዛዜውን ጽሁፍ መሆኑንና ተጠቃሚ ለመሆን ማስረዳት እንደማይችል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897/1/ እና /2/ ይደነግጋል::

ይህም በመሆኑ የሚች ወራሾች የኑዛዜ ተጠቃሚው የወራሽነት መብቱን የሚያስረዳበትን የኑዛዜ ጽሁፍ በማበላሸት በማጥፋት ወይም እንዳይገኝ በማድረግ ከሚች ውርስ ተካፋይ ሆኖ እንዳይቀርብ የሚያደርጉትን ሸርና ደባ ከወዲሁ ለመቆጣጠ ርና ይህንን ፈጽመው የተገኙ የሚች ወራሾች በሚች ውርስ እንዳይካፈሉ በሕግ በመከልከል የሚች ወራሾች የሚችን የመጨረሻ የኑዛዜ ቃል ማክበር ያለባቸው መሆኑን በማመልከት ደንቡን ያወጣው መሆኑን እናያለን::ከዚሁ ጋር አብሮ የማነሣው ጥያቄ ያለ ሚች ፈቃድ የሚችን የመጨረሻ ኑዛዜ ለማበላሸት ለማጥፋት ወይም እንዳይገኝ ለማድርግ ሆነ ብሎ አንድ ድርጊት የፈፀመ ሰው ለምሣሌ የኑዛዜው ጽሁፍ በውሀ እንዲበሰብስ እና እንዲጠፋ በማሰብ ባሕር ውስጥ የጨመረ የሚች ወራሽ ይህንን የኑዛዜ ጽሁፍ ወዲያውኑ ከውሀው ውስጥ ሌሎች ሰዎች አውጥተው በፀሐይ በማድረቅ ፍርድ ቤት በማስረጃነት ቢያቀርቡት፣ ወይም የሚችን የመጨረሻ ኑዛዜ በእሣት በማቃጠል ላይ እያለ ሰዎች ደርሰው ቢያስጥሉትና ከእሣት የተረፈው የሚች የኑዛዜ ቃል ሙሉ ይዘቱ ፊርማውና የተጻፈበት ቀን ስላልተቃጠለ የማስረጃነት ዋጋ ቢሰጠው፣ ወይም የሚች የመጨረሻ ኑዛዜ ከቆሻሻ ጋር እንዲጣል በማሰብ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ ኮንቲነር ከጨመረው በኋላ በድንገት ሰጪዎች አግኝተውት በማሰረጃነት ቢቀርብ በአጠ ቃላይ ሆነ ብሎ የፈፀመው ድርጊት ያሰበውን ውጤት ሣያስገኝለት ቢቀር ድርጊቱን የሚችን ኑዛዜ በማጥፋት ለማበላሸት ወይም እንዳይገኝ ለማድርግ ሆነ ብሎ መፈፀሙ ፣ መሞከሩ መረጋገጡ ብቻ የመውረስ መብቱን አያሳጣውም ወይ? የሚለው ነው:: ወራሹ የአውራሹን የመጨረሻ ኑዛዜ ሆነ ብሎ ያለ ሚች ፈቃድ ከማጥፋት ከማበላሸት ወይም እንዳይገኝ ከማድረግ መታቀብ እንዳለበት የሕጉ ድንጋጌ ያሣያል:: ይህ ከሆነ ሆነ ብሎ ያለሚች ፈቃድ የሚችን የመጨረሻ ኑዛዜ ለማጥፋት፣ ማበላሸት ወይም እንዳይገኝ ለማድረግ ግዙፍ ተግባር የፈፀመ የሚች ወራሽ የፈፀመው ተግባር በተለያዩ ምክንያቶች ያሰበውን ውጤት ባያስገኝለትም እንኳን በሕጉ የተከለከለ ድርጊት የፈፀመ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840/ለ/ መሠረት ሚችን ለመውረስ ያልተገባ ሊባል እንደሚችል የሕጉን ድንጋጌ መንፈስና ዓላማ እንደዚሁም ሕግ አውጭው ሊደርስበት ያሰበውን ግብ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል::

ሌላው በፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 840/ለ/ መሠረት ለወራሽነት ያልተገባ ነው የሚያሰኘው ምክንያት ጉዳዩን በማወቅ በሀሰት ኑዛዜ መጠቀም ነው:: ከዚህ ድንጋጌ ኑዛዜው በሀሰት የተዘጋጀ መሆኑን ሣያውቅ ሌሎች ሰዎች እውነተኛ ኑዛዜ አስመስለው የሰጡትን የኑዛዜ ቃል በማያያዝ በኑዛዜ ወራሽነት በሚች ውርስ ለመካፈል የቀረበ ሰው የሀሰት ኑዛዜ ይዞ መቅረቡ ቢረጋገጥም እንኳን ሚችን በቀጥታ ወይም በተተኪነት ያለ

ኑዛዜ ከመውረስ ወይም ሟች በተወለት እውነተኛ ኑዛዜ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ከማግኘት የሚያግደው መሆኑን ነው::እዚህ ለይ የሚነሣው ጥያቄ "በሀሰት ኑዛዜ የተጠ ቀመ የሚለው ሀረግ" እንዴት መተርጐም አለበት የሚለው ነው:: በሀሰት ኑዛዜ የተጠ ቀመ የሚለው በሟች ውርስ ተካፋይ ሆኖ ንብረት የወሰደን ወይም በሀሰት ኑዛዜ በሟች ውርስ ንብርት ክፍል ውስጥ ጥቅም ያገኘን ሰው ብቻ የሚመለከት ነው የሚል ሀሣብ ያላቸው ሰዎች አሉ::ሌሎች ደግሞ ንብረት ከመካፈሉና በኑዛዜው ጥቅም ከማግኘቱ በፊት የኑዛዜ ወራሽ ነኝ ብሎ በሀሰት የተዘጋጀውን ኑዛዜ ለውርሱ አጣሪ ወይም ለፍርድ

ቤት እንዳቀረበ ኑዛዜው የሀሰት መሆኑ የተረጋገጠበት ሰው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840/ለ/ መሠረት የወራሽነት መብቱን ያጣል በማለት ይከራከራሉ::የሕግ አውጭውን ሀሣብ እና ሊደርስበት ያሰበውን ግብ ለመረዳት የአማርኛ እና የእንግሊዝኛውን ቅጂ አጣምሮ ማየቱ ጠቃሚ ነው:: በዚህ ጉዳይ የእንግሊዝኛውን የፍትሐብሔር ሕግ ቅጅ ስንመለከት::

'' ውሀጸ ሰጸ ጵቨጵረ ሀቷሰ ፀነተጵነተፀጸነቷለለየ ደጵሰተረጸየጵደ ቸቷጭሰጵደ ተጸ ደፀሰቷፐፐጵቷረ ጸረ ቷለተጵረጵደ ተሀጵ ለቷሰተ

ወፀለለ ጸፈ ተሀጵ ደጵቸጵቷሰጵደ ወፀተሀ ጸጭተ ተሀጵ ቸጸነሰጵነተ ጸፈ ተሀጵ ለቷተተጵረ ጸረ ሀቷሰ ቷቨቷፀለጵደ ሀፀመሰጵለፈ ጸፈ ቷፈቷለሰጵ ወፀለለ ከነጸወፀነገ ፀተ ተጸ በጵ ሰጭቸሀኸ ሰሀቷለለ ለጸሰጵ ሀፀሰ ቸቷፐቷቸፀተየ ተጸ ሰጭቸቸጵጵደ ተሀጵ ደጵቸጵቷሰጵደ ቷሰ ጭነ ወጺረተሀየ'' የሚል ሆኖ እናገኘዋለን:: በእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ ኋቷቨቷፀለጵደ'' የሚለው ቃል ማንኛቸውንም አጋጣሚ ለመጠ ቀም መሞከር ወይም ተጠቃሚ ለመሆን መቅረብን እንጅ ጥቅም ማግኘትን ብቻ የሚይዝ እንዳልሆነ ለመረዳት ይቻላል::ይህ ከሆነ በሀሰት አዘጋጅቶ ባቀረበው ኑዛዜ ጥቅም ለማግኘት ማቅረቡ ብቻ ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው ሊያሰኘው እንደሚችል ከአንግሊዝኛው ቅጅ በግልጽ ለመረዳት ስለሚቻል ሆነ ብሎ የሀሰት ኑዛዜ በማዘጋጀት ሟችን ለመውረስ የቀረበ ሰው በኑዛዜው መሠረት ንብረት ሣይሰጠው በፊት ያቀረበው ኑዛዜ የሀሰት መሆኑ ከተነቃበትና ከተረጋገጠበት ሟችን በቀጥታ ወይም በተተኪነት ለመውረስ ወይም ሟች በተወለት እውነተኛ ኑዛዜ የተመለከተውን ጥቅም የማግኘት መብቱን እንደሚያጣ ለመረዳት አንችላለን::

ስለዚህ "በሀሰት ኑዛዜ የተጠቀመ'' የሚለው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840/ለ/ ድንጋጌ ቃል ከእንግሊዘኛው ቅጅ መልእክት ጋር በሚጣጣም መልኩ በሰፊው መተርጐም

ያለበት መሆኑን አንደኛው የአተረጓጐም መንገድ ሲሆን በዚህ አተረጓጐም መሠረት የሀሰት ኑዛዜ ሆነ ብሎ ለውርስ አጣሪ ወይም ለፍርድ ቤት ያቀረበ ሰው ንብረት ከመካፈሉ በፊት ይኸው ድርጊቱ ከተረጋገጠ ያለኑዛዜ ወይም ሚች በተወው እውነተኛ ኑዛዜ መሠረት ሚችን ለመውረስ ያልተገባ ነው ሊባል ይችላል። በሌላ በኩል በኑዛዜው ተጠቅሞ ሐብት ካገኘ ብቻ ነው የሚከለከለው የሚሉ ወገኖች አሉ። ጉዳዩ ትርጉም ክፍትና አከራካሪ ነው።

3.3.3 በሚች ስለ ሚደረግ ይቅርታ

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 የተዘረዘሩተን ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦበት በፍርድ የተቀጣ ወይም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840 የተመለከቱትን ተግባራት በመፈፀሙ የውርስ ሕግ ሚችን ለመውረስ አይገባውም በማለት የወራሽነት መብቱን ያሳጣው ሰው በአንድ ምክንያት ብቻ የወራሽነት መብቱ እንደሚረጋለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 841 ድንጋጌዎች ያመለክታሉ።ይኸው የወራሽነት መብቱን እንደያዘ እንዲቆይ የሚያደርገው ብቸኛው ምክንያትም ሚች በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ ይቅርታ አድርጐለት እንደሆነ ነው። አዚህ ላይ አንድ በጥልቀት ልንመለከተው የሚገባን ነጥብ አለ። ይኸውም በፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 840/ለ/ በተደነገገው መሠረት የሀሰት ኑዛዜ በማዘጋጀት ወራሽ ለመሆን በመጠየቁና በወራሽነት በማቅረቡ ሆነ ብሎ በሀሰት ኑዛዜ ከሚች ውርስ ለማካፈል መቅረቡ ተረጋግጦበት ሚችን የመውረስ መብት የለውም የተባለን ወራሽ ሚች ይቅርታ ሊያደርግለት የማይችል መሆኑ ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው በኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ ወራሽ ለመሆን የሚጠይቀው ከሚች መሞት በፊት ሣይሆን ሚች ከሞተና የሚች ውርስ ከተከፈተ በኋላ ነው። በመሆኑም በሚች ውርስ የሀሰት ኑዛዜ ይዞ በመቅረብ የውረስ ሕግ ሚችን የመውረስ መብት የለውም ያለው ሰው ሚች የሀሰት ኑዛዜ ማዘጋጀቴን እያወቀ ይቅርታ አድርጐልኛል በማለት ክርክር ቢያቀርብ በሕግ ፊት ዋጋ የሚሰጠው አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።ከዚህ ውጭ ያሉትን አና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 ወይም 840 የተዘረዘሩትን ድርጊቶች መፈፀሙን እያወቀ ሚች በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ ይቅርታ ያደረገ እንደሆነ የወራሽነት መብቱ እንደሚጠበቅለትና እንደሚረጋለት ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 841 ድንጋጌዎች እንረዳለን።ሚች በግልጽ ይቅርታ አደረገ የሚባለው ወራሹ የፈፀመውን ድርጊት ከጠቆመ በኋላ ይህንን ወራሽነት ያልተገባ ነው የሚያሰኝ ድርጊት ቢፈጽምም ይቅርታ ያደረግሁ ስለሆነ በውርሴ ይካፈል በማለት በቃል ሣይሆን በጽሁፍ ሲያሣውቅ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 841/1/ ይደነግጋል። ሚች በተዘዋዋሪ ይቅርታ አድርጓል የሚባለው ሰውየው /ሴትዮዋ/ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 ወይም 840

ከተመለከቱት ድርጊቶች አንዷን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን መፈፀሙን እያወቀ የኑዛዜ ስጦታ ያደረገለት አነደሆነ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 841/2/ ያስረዳል::

እዚህ ላይ መጠንቀቅ የሚገባን ነገር ቢኖር ሟች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 841/2/ መሠረት በተዘዋዋሪ ይቅርታ አድርጓል የምንለው ሁለት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ መሆኑን ነው:: ይኸውም ሟች የኑዛዜ ስጦታውን ያደረገው ሰውየው/ሴትዮዋ/ ለወራሽነት ያልተገባ ነው የሚያሰኛቸውን ድረጊቶች ከፈፀሙ በኋላ የሆነ እንደሆነ እንደዚሁም ለወራሽነት ያልተገባ የሚያሰኝ ድርጊት መፈፀማቸውን እያወቀ የሆነ እንደሆነ ነው::ሟች የኑዛዜ ስጦታ ያደረገው ለወራሽነት ያልተገባ የሚያደርገውን ድርጊት ከመፈፀማቸው በፊት ወይም ለወራሽነት ያልተገባ የማያሰኝ ድርጊት መፈፀማቸውን ሣያውቅና እውቀቱ ሣይኖረው እንደሆነ በተዘዋዋሪ ይቅርታ እንዳደረገ እንደማይቆጠር ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 841/2/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል::በመሆኑም ስለ ይቅርታ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በተግባር ላይ ከምናውልበት ወቅት ከላይ ያነሣናቸውን ጠንቃቄዎች ማድረግ አስፈላጊ ነው::

በአጠቃላይ ሟችን ለመውረስ የሟች ውርስ ሲከፈት በህይወት መኖር እና ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው አለመባል የኢትዮጵያ ውርስ ሕግ ያስቀመጣቸው መሠረታዊ ሁኔታዎች መሆናቸውን እና በልዩ ሁኔታ ከሟች ውርስ ሟች ሲሞት ያልነበሩ ሰዎች ተካፋይ የሚሆኑበት ድንጋጌዎች ያሉ መሆኑን ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው በማለት የውርስ ሕግ የገደበው ሰው ሟች በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ በሚያደርግለት የቅርታ የወራሽነት መብቱ ሊረጋለት እንደሚችል መረዳት እና ዝርዝር ጉዳዮችን በጥልቀት ማየት ያስፈልጋል::

ሆኖም ፍርድ ቤቶች ሟች በኑዛዜ፣ ከወራሾቹ አንዱን ከወረሱ የሚነቅልበትንና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 837 እስከ ፍትሐብሔር 839 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ጋር በማደበለቅ፣ ለወራሽነት ያልተገባ መሆን፣ እና በሟች ኑዛዜ የሟች ወራሾች፣ ከውርስ የሚነቅልበትን፣ ስርዓት ሣይለዩ ውሣኔ ሲሰጡ ይታያሉ:: በዚህ በኩል ያለውን ችግር ለመረዳት በመጀመሪያ በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በኩል ታይቶ ከተወሰነ በኋላ የምዕራብ ጐጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 05934 ህዳር 22 ቀን 1996 ዓ.ም በይግባኝ አይቶ የሰጠውን ውሣኔ በአጭሩ ማየቱ ጠቃሚ ነው:: የጉዳዩ መነሻ ሟች አቶ ድረስ ንግሩ ሚያዝያ 27 ቀን 1989 ዓ.ም ያደረጉት በግልጽ

የተደረገ ኑዛዜ ሲሆን በኑዛዜ ሰነድ ሚች በርካታ ጉዳዮችን የሚመለከት ኑዛዜ ካደረጉ በኋላ፣ ካሣ ድረስ የተባለው ልጅ ግን ከምሰጠው ምክርና መመሪያ ውጭ አንድም ቀን ብሎ ትዕዛዜን የማይቀበል በድፍረት ብዙ ችግርና በደል ያደረሰብኝ በመሆኑ ከማንኛውም ሀብቴና ንብረቴ እንዳይደርስ ከላይ በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 909 በፊደል፣ ሐ፣ ሠረኛዋለሁ የሚል ኑዛዜ በሕጉ መሠረት ፎርማሊቲውን አሟልተው ያደርጋሉ፡፡

በሚች ዙዛዜ ከውርስ እንዳይደርስ የተባለው ካሣ ድረስ ሚች ከሞቱ በኋላ የሚች አባቴ ልጅና ወራሽ ሆኜ እያለሁ የሚችን ውርስ ንብርት አላካፍለኝ ስላለች ፍርድ ቤቱ ወራሽነቴን ያረጋግጥልኝ በማለት ለባሕርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት ማመለከቻ ያቀረበች ሲሆን፣ ወሐሮ ወረቀት ዓለሙ አመልካቹን ሚች በኑዛዜ ከውርሱ የነቀለው መሆኑን ገልጻ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘገቶ እንዲያሰናብተው ትከራከራለች፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር የሰማው የወረዳው ፍርድ ቤት፣ ሚች አቶ ድረስ ንግሩ ማያዝያ 27 ቀን 1989 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ልጃቸው አቶ ካሣ ድረሰን ለመንቀል የሰጡት ምክንያት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 ከተገለጹት ተግባራት አንዱን የማይሸፍን በመሆኑ ሚች ልጅን ከውርስ በኑዛዜ መንቀል የሚችለው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 የተመለከቱትን ድርጊቶች ሲፈጽም መሆኑን በመተንተን ሚች ያደረገውን ኑዛዜ ውድቅ አድርጐ አቶ ካሣ ድረስ የሚች ድረስ ንግሩ ወራሽ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 አንድ ሰው ለወራሽነት ያልተገባ ተብሎ ከሚች ውርስ በሕግ የሚከለከልበት የሕግ ድንጋጌ ሲሆን ወራሽን በተለይም ወደታች የሚቆጠር ተወላጅን ከውርስ ለመንቀል መታየትና መመዘን ያለባቸው የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 937 እና 938 -1? ናቸው፡፡ ስለዚህ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ይሻርልኝ በማለት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ብታቀርብም ከፍተኛው ፍርድ ቤት ወደ ይግባኙ ለማስገባት የሚችል በቂ ምክንያት የለም በማለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ይግባኙን በመሠረዝ ይግባኝ ባይን አስናብቷታል፡፡ ይኸም ጉዳይ ሚች አቶ ካሣን ለመንቀል የሰጠው ምክንያት በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ እንደመዝን የፍትሐብሐር ሕግ ቁጥር 938 -2? በፍርድ ቤቱ የሰጠው ስልጣን አለግባብ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 838 ጋር

በማጣመር መመዘኑ፣ ሚችን ለመውረስ ያልተገባ መሆን፣ የሚለው ሀሣብና፣ ከሚች ውርስ በሚች ኑዛዜ ስለመነቀል፣ የሚለው ጽንሰ ሀሣብ ለብቻ ለያይቶ ማየትና ሕጉን መተርጐም እንደሚገባ ያመለክታል።

የሙከራ ጥያቄዎች

1.በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ለመውረስ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ጉዳዬች ምንድን ናቸው?

2.ለወራሽነት ያልተገባ መሆን እና በውርስ መነቀል በሚሉት ፅንሰ ኃሣቦች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

3. የውጭ ዜግነት ያላቸው ሰዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በኢትዮጵያዊ ውርስ ተካፋይ እንደሆኑ መጋበዙ፣ ተገቢ ነው ብለው ያስባሉ?

4. በውርስ መከፈትና በውርስ ማጣራት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

5. የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 ርእስና በይዘቱ አለመጣጣም አለበት ብለው ያስባሉ

6. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 የፍትሐብሔሩን ጉዳይ በወንጀል ችሎት በሚሰጠው የቅጣት ውሣኔ ላይ ጥገኛ እንዳይሆን ማድረጉ ምን አይነት ጉዳት ያስከትላል ብለው ያስባሉ?

7. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840-ለ? ድንጋጌ የአማርኛው የእንግሊዘኛው ቅጅ የትኛው በተሻለ ሁኔታ ህግ አውጭው ሊደርሰበት ያሰበውን ግብና አላማ ይገልፃሉ ብለው ያስባሉሕ ለምን?

8. ሚች በተዘዋዋሪ መንገድ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 841 መሰረት ይቅርታ አድርጓል ለማለት ምን ምን ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው?

ምዕራፍ አራት

ሳይናዘዝ የሞተ ሰው የውርስ ሥርዓት አፈጻጸም

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ በሕይወት ዘመኑ ኑዛዜ ሳይተው የሞተ ሰው የውርስ ሥርዓት አስተዳደር እንዴት መሆን እንዳለበት በፍትሐብሔር ሕጉ የተደነገጉትን መሠረታዊ መርሆች ማሳየት፣

ሣይናዘዝ የሞተ ሰው የውርስ ሥርዓት በሚፈፀምበት ጊዜ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉ የሥጋ ዘመዶቹ እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉና፣ በውርስ ሂደት ያላቸውን ቅደም ተከተል፣ እና ሊያገኙ የሚገባው ድርሻ መጠን ምን ሊሆን እንደሚችል በአጭሩ ማሣየት ነው::

4.1. ጠቅላላ መግቢያ

በጠቅላላው ስለ ውርስ ሥናወራ ሟች ከሞተ በኋላ የውርስ ሥርዓት የሚፈፀመው ቢያንስ በሦሥት ዓይነት መንገድ ሊሆን እንደሚችል በፍትሐብሔር ሕጉ ተደንግጓል:: ይኸውም :.

ሟች በሕይወት ዘመኑ ስለ ውርስ ሥርዓትና ስለ ወራሾቹ የተወው ኑዛዜ ካለ፣ በሟች ኑዛዜ መሠረት / Testate Succession/ **ሟች በሕይወት ዘመኑ በሞት በተለየበት ጊዜ ውርሱ ምን መሆን እንዳለበት የተወው ኑዛዜ ከሌለ ያለኑዛዜ በሚፈፀም የውርስ ሥርዓት** / Intestate Succession/ **ሟች በከፊል ኑዛዜ ከተወና ከፊል ንብረቱ እንዴት መከፋፈል እንዳለበት የተወው ኑዛዜ ከሌለ፣ ውርስ በከፊል በኑዛዜና በከፊል ያለ ኑዛዜ ሊፈፀም እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ** 829 **ተደንግጓል::**

በመሠረታዊ መርህነት የኢትዮጵያ ሕግ፣ ሟች በሕይወት ዘመኑ የተወው ኑዛዜ ካለ የሟች የውርስ ሥርዓት በሟች የኑዛዜ ቃል መሠረት መፈፀም እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን ሟች በኑዛዜ ያላደላደላቸው ንብረቶች በሙሉ ለሥጋ ዘመዶቹ በውርስ ሕግ መሠረት ሊተላለፍ እንደሚችሉ ተመልክቷል:: በመሆኑም ሟች ንብረቱን በሙሉ በኑዛዜ አደላድሎ ከሞተና ያለኑዛዜ የሚተላለፍ ምንም ዓይነት ንብረት ከሌለው በውርስ ሕግ መሠረት ያለኑዛዜ ውርስ ለመፈፀም አይችልም:: ሟች ስለ ውርስ ሥርዓት አፈጻጸምና ስለ ወራሾቹ የተወው በሕግ ውጤት ያለው ኑዛዜ በሌለበት ሁኔታ ውርሱ ያለኑዛዜ ይፈፀማል:: ውርሱ ያለኑዛዜ በሚፈፀምበት ወቅት እንዴት

እንደሚፈፀምና እነማን የቀዳሚ ወራሽነት መብት እንዳላቸው፣ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ይወስናሉ።

ከዚህ አንጻር ሲታይ የአንድ ሰው ውርስ ያለኑዛዜ በሚፈፀምበት ወቅት፣ ሦሥት ዓይነት የአወራረስ ሥርዓቶች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ፣ ስለውርስ ስርዓት የተጻፉ ፅሁፎች ያሣያሉ። የመጀመሪያው የተለመ ተፈጥሮዓዊ አወራረስ / Natural Succession/ የሚለው ነው። የተፈጥሮ አወራረስ ሥርዓት የምንለው ውርሱ የሚፈፀመው በሁለት የተፈጥሮ ሰዎች መካከል የሆነ እንደሆነ ነው። ይኸም ማለት የሟች ወራሾች የሥጋ ዘመዶቹ የሆኑ የተፈጥሮ ሰዎች የሆኑ እንደሆነ ውርሱ የተለመደ ወይም Natural Succession፣ ይባላል። የፍትሐብሔር ሕጋችን በአብዛኛው ያለ ኑዛዜ የሚደረግ ውርስ፣ የተለምዶ የውርስ ሥርዓትን / Natural Succession/ እንዲከተል የሚያደርጉ በርካታ የሕግ ድንጋጌዎችን ይዞ እናገኘዋለን። እነዚህ የሕግ ድንጋጌዎችም የሟችን ቀጥታ ወራሾች ወይም በሟች ውርስ በተተኪነት ሊካፈሉ የሚችሉትን እነማን እንደሆኑ በሰፊው በመዘርዘር፣ የሟች የውርስ ሥርዓት ተፈጥሯዊ የሆነው የሥጋ ዝምድና መሠረት በማድረግ እንዲከናወን ሰፊ በር የሚከፍት ነው።

ሁለተኛው የአወራረስ ሥርዓት ያልተለመደ አወራረስ ወይም Irregural Succession የሚባለው ነው። ያልተለመደ የውርስ ሥርዓት የምንለው ሟች በሕይወት ዘመኑ የተወው፣ ኑዛዜ ከሌለና በውርስ ሕግ መሠረት ወራሽ ሊሆን የሚችል የሥጋ ዘመድ ከሌለው፣ የሟች ወራሽ የአገሪቱ መንግሥት ወይም፣ በሕግ በግልፅ የተጠቀሰ የበጐ አድራጐት ድርጅት እንደሆን፣ የአንዲት አገር ሕግ የሚፈቅድ ሲሆንና ውርሱም በዚሁ መሠረት የሚፈፀም ሆኖ ሲገኝ ነው።የእኛ ሕግ ኑዛዜ ሣይፈጽም የሞተ ሰው በዘመዶቹ እንዲወረስ ሰፊ እድል የሚሰጥ ቢሆንም፣ ሟች በውርስ ሕግ መሠረት ሊወርሰው የሚችለው ዘመድ ከሌለው የሟች ሐብት በወራሽነት ለመንግሥት ሊተላለፍ እንደሚገባው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 852 በግልፅ ይደነግጋል። በመሆኑም ሟች በሕይወት ዘመኑ ኑዛዜ ካልተወና፣ በውርስ ሕግ መሠረት ለመውረስ የሚችል ዘመድ የሌለው እንደሆነ መንግሥት የሟች ወራሽ ሆኖ እንደሚቀርብና የሟችን ንብረት እንደሚረከብ፣ በዚህ ዓይነት መንገድ የአንድ ሰው የውርስ ሥርዓት ሲፈፀም ያልተለመደ የአወራረስ ሥርዓት ወይም Irregular Succession በሚባል እንደሚጠራ፣ ግንዛቤ መያዝ አለበት።

ሶሥተኛው የውርስ ሥርዓት ክፍት የውርስ ሁኔታ ወይም vacant Suceession የሚባለው ነው። የአንድ ሰው ውርስ ክፍት (Vacant) ነው የሚባለው ሟች ኑዛዜ ካልተወና፣ በውርስ ሕግ መሠረት ወራሽ ሊሆን የሚችል ዘመድ ከሌለው እንደዚሁም፣ የአገሪቱ የውርስ ሕግ ሟች ወራሽ ዘመድ በሌለው ጊዜ ንብረቱ ለማን መተላለፍ እንደሚገባው ሣይደነግግ ክፍት አድርጐ የተወው እንደሆነ ነው። በእኛ አገር ሟች ወራሽ ዘመድ በሌለው ጊዜ መንግሥት በወራሽነት፣ እንደሚቀርብ ግልፅ የሕግ ድንጋጌ በመኖሩ የሟች ውርስ ወራሽ አልባ ወይም (Vcant Succession) የሚሆንበት አጋጣሚ የለም። ሆኖም የአንዲት አገር ሕግ ሟች ወራሽ ዘመድ በሌለው ጊዜ የሟች ንብረት ለማን መተላለፍ እንደሚገባው የሚደነግግ ካልሆነ የሟች ውርስ ወራሽ አልባ ይሆናል ንብረቱም ለብክነት የሚዳረግ ይሆናል። በመሆኑም የውርስ ሕግ በሚረቀቅበትም ጊዜ ሆነ ሕጉ በሚሻሻልበት ወቅት የሟች ውርስ ወራሽ አልባ ሆኖ እንዳይቀር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

4.2 ያለ ኑዛዜ በሚፈጸም ውርስ ሊካፈሉ የሚችሉ የሥጋ ዘመዶች፣

ከላይ እንደተገለፀው አንድ ሰው፣ ስለ ውርሱ አፈጻጸም የተወው ኑዛዜ ከሌለ የሟች ውርስ ይህንኑ ሁኔታ በሚገዛው በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሠርት ሊፈፀም እንደሚችል፣ ለመረዳት ይችላል። በዚህ መሠረት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት አንድ ሰው የኑዛዜ ወራሽ የሌለው እንደሆነና ውርሱ ያለ ኑዛዜ የሚፈፀም ከሆነ በመጀመሪያ ለመጀመሪያ ደረጃ ወራሾቹ ወይም ለእነርሱ ተተኪዎች፣ በመጀመሪያ ደረጃ ወራሽነት የሚጠሩት የሥጋ ዘመዶች ወይም የእነርሱ ተተኪዎች የሌሉ እንደሆነ ለሁለተኛ ደረጃ ለሚጠሩ ወራሾቹ ወይም ለእነርሱ ተተኪዎች፣ የሁለተኛ ደረጃ ወራሽነት የሚጠሩ የሥጋ ዘመዶቹ ወይም የእነርሱ ተተኪዎች የሌሉ እንደሆነ በሦሥተኛ ደረጃ ለሚጠሩ ወራሾች ወይም ለእነርሱ ተተኪዎች፣ በሶስተኛ ደረጃ በወራሽነት የሚጠሩ የሥጋ ዘመዶች ወይም የእነርሱ ተተኪዎች የሌሉ እንደሆነ በአራተኛ ደረጃ ለሚጠሩ የሟች ወራሾች ወይም የእነርሱ ተተኪዎች፣ በአራተኛ ደረጃ በወራሽነት የሚጠሩ የሟች የሥጋ ዘመዶች ወይም የእነርሱ ተተኪዎች የሌሉ እንደሆነ የሟች ውርስ ለመንግሥት መተላለፍ እንደሚገባው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፣ የውርስ ሕግ ደንቦቹ ሳይናዘዝ የሞተ ሰው ወራሾች በሁለት ዓይነት መንገድ ከፍለው ያስቀምጣሉ። የመጀመሪያው በቀጥታ ከሟች ውርስ ተካፋይ ሊሆኑ የሚችሉ የሟች የሥጋ ዘመዶች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ ሟችን በቀጥታ የሚወርሱ የሥጋ ዘመዶቹ በሌሉ ጊዜ ሟችን በቀጥታ ሊወርሱ የሚችሉትን የሥጋ ዘመዶች በመተካት የሚወርሱ የሥጋ ዘመዶቹን

ነው፡፡ በመሆኑም የሚች የሥጋ ዘመዶች በሚች ውርስ ሊካፈሉ የሚችሉት በቀጥታ ወራሽነት ወይም በተተኪነት ሊሆን እንደሚችል የሕጉ ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ እነዚህ በአጠቃላይ በሕጉ የተመለከቱት የሚች ወራሾች እና የውርስ ሥርዓት አፈጻጸም ያስቀመጣቸው ሲሆን ሕጉ የሚችን ወራሾች በቅደም ተከተል አስቀምጧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የሚጠሩት ወራሾቹ በመጀመር እስከ አራተኛ ደረጃ ውርስ የሚጠ ሩትን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ሚች ኑዛዜ ባልተወበት ወቭም ትዛዜው ውጎ፤ አልባ በሆነበፔ ሁኔታ ውርስ እንደየደረጃቸው ለሥጋ ዘመዶቹ እንዲተላለፍ ይፈቅዳል፡፡ ሆኖም በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ መሠረት የሚች ባል ወይም ሚስት ወይም የሚች የጋብቻ ዘመዶች በሚች ውርስ ለወራሽነት እንዲካፈሉ አይጠ ሩም፡፡ የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ የደም ትስስርን መሠረት ያደረገ መሠረታዊ መርህ ይከተላል፡፡ ሌሎች አገሮች የጋብቻ ትስስርን በተለይም ሚስት ባሏን ወይም ባል ሚስቱን የሚወርስበትን ሁኔታ ይፈቅዳሉ፡፡ በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ መሠረት ግን የሚች ያለ ኑዛዜ ወራሾች ሆነው ሊቀርቡ የሚችሉት የሚች የስጋ ዘመዶች ብቻ መሆናቸውን በግልጽ ያስቀምጣል

ሀ. የሚች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች

የሚች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች የሚቹ ልጆች እንዲሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842/1/ ይደነግጋል፡፡ የሚች ልጆች ስንል ሚች በሕጋዊ ጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ የወለዳቸው ልጆች የሚች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች እንደሚሆኑና፣ የሚች ልጆች እስካሉ ድረስ በሚች የኑዛዜ ቃል ካልሆነ በስተቀር እናትና አባቱም ሆነ ሌሎች ዘመዶቹ በሚች ውርስ እንዲካፈሉ ሕጉ መብት የማይሰጣቸው መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡

ከዚሁ ጋር አብሮ መነሳት ያለበት ነገር የሚች ልጆች ከሚች ውርስ የሚደርሳቸው ድርሻ እኩል /ትክክል/ መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842/2/ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ይኸም ማለት ሚች አራት ልጆች ካሉት የሚች የውርስ ንብረት ልጆቹ ለአራት እኩል ከፍለው እያንዳንዱ ልጅ ከሚች መካከል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 913 መሠረት በግልፅ በልዩ ሁኔታ የተደረገ፣ የኑዛዜ ቃል ከሌለ በስተቀር በሚች ልጆች መካከል የድርሻ መበላለጥ እንደሌለ በሕጉ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በመሠረታዊ መርህ ደረጃ የሚች ልጆች ከሚች ውርስ እኩል የሆነ ድርሻ እንደሚወስዱ መታወቅ አለበት፡፡ ሕጉ የሚች አንደኛ ደረጃ ወራሾች መሆናቸውን ብቻ በመደንገግ አያበቃም፡፡ የውርስ ሕጋችን በሚች ውርስ በመጀመሪያ ደረጃ ሊጠሩት የሚችሉ ልጆቹ ወይም ከልጆቹ

አንዱ የሞተ እንደሆነ የሚች ውርስ ለማን ይተላለፋል ለሚለው ጥያቄም በቂ ምላሽ ሰጥቷል። ይኸንንም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842/3/ የሚች ልጆች ወይም ከልጆቹ አንዱ የሞተ እንደሆነና ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ትተው እንደሆነ በእነርሱ ምትክ ሆነው እንደሚወርሱ በግልፅ ይደነግጋል።

እዚህ ላይ መታየት የሚገባው ነጥብ እስከ ስንተኛ ደረጃ ያሉ የሚች ተወላጆች ናቸው በሚች ውርስ ላይ በተተኪነት ተካፋይ የሚሆኑት የሚለው ነው። ይህንን ጥያቄ ለመመለስ በፍትሐብሔር ሕጉ ሁለተኛ መፅሐፍ መግቢያ ላይ ስለ ሥጋ ዝምድናና ስለ ጋብቻ ዝምድና የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ወይም ሌሎች በቅርብ የወጡ የቤተዘመድ ሕጐችን በማየት መልስ መስጠት ያስፈልጋል።በበኩሌ በፍትሐብሔር ሕጉ ከተቀመጠው ውጭ ሥለ ሥጋ ዝምድናና ስለጋብቻ ዝምድና በተሟላ ሁኔታ የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ አላገኘሁም። የፌዴራሉ መንግሥት ያወጣው የቤተሰብ ሕግ የዝምድና ደረጃቸው ፣ በጐንዬሽ የሆነ የሥጋ ዘመዶች የዝምድና ደረጃ ከሶስት ደረጃ በላይ ከሆነ መጋባት እንደማይከለከሉ፣ የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ የያዘ ሲሆን ይኸው ሕግ በቀጥታ የሥጋ ዝምድና ውጤት የሚኖረው እስከ ስንተኛ ደረጃ እንደሆነ በግልፅ አያስቀምጥም።

በመሆኑም በውርስ ጉዳይ በፍትሐብሔር ሕጉ የሥጋ የዝምድና ደረጃ እስከ ሰባተኛ ትውልድ ድረስ ውጤት እንደሚኖረው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 551 በግልፅ የሚደነግግ በመሆኑ፣ ሚች እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ የሚቆጠሩ ተወላጆች ካሉት ሚችም የልጅ ልጆች፣ የልጅ ልጅ ልጅ. ወዘተ ካሉት እነዚህ ተወላጆች በሚች ውርስ በተተኪነት የመውረስ መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። በመሆኑም የሚች ውርስ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ወራሾቹ ሊሸጋገር የሚችለው የሚች ልጆች ወይም እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ የሚቆጠር ተወላጆች የሌሉት እንደሆነ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በሁለተኛ ደረጃ መታየት ያለበት ነጥብ፣ በተተኪ ወራሽነትና የሚች የወራሽነት መብት ከሚች ወራሽ መተላለፍ የተለያዩ ፅንሰ ኃሣቦት መሆናቸውን ነው። በምዕራፍ ሁለት ላይ በዝርዝር እንዳስቀመጥነው፣ የሚች ውርስ የሚከፈተው ሚች ሕይወት ባለፈበት ቅፅበት ነው። ይኸም ማለት ከሚች በሴኮንድም ሆነ በደቂቃዎች እድሜ ዘግይቶ የሞተ ሰው፣ ለወራሽነት ያልተገባ ነህ የሚያሰኝ ወንጀል ፈፅሞ ካልተቀጣ በስተቀር ሚችን ወርሶ እንደሞተ ይቆጠራል። በመሆኑም የሚች ወራሽ የሆነ ሰው የሚች ውርስ ከተከፈተ በኋላ የሞተ እንደሆነ እርሱ ያረጋገጠው የወራሽነት መብት ለእርሱ ወራሾች እንደሚተላለፍ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 833 ይደነግጋል። በዚህ

ዓይነት ሁኔታ በሚች ውርስ ተካፋይ የሚሆኑ ሰዎች በውርሱ ተካፋይ የሚሆኑት የሚች ወራሽ አረጋግጦት የሄደውን የወራሽነት መብት እንጅ የሚችን ወራሽ በመተካት አይደለም::

የሚች ተተኪ ወራሾች የሚባሉት የሚች ውርስ ሲከፈት በሕይወት ቢኖር ኖሮ በሚች ውርስ በወራሽነት ለመካፈል የሚችል አንድ ሰው፣ ከሚች በፊት በመሞቱ ምክንያት ሚችን የመውረስ ችሎታ ሲያጣ፣ የእርሱ ተወላጆች እርሱን ተክተው በወራሽነት እንዲካፈሉ የውርስ ሕግ የሚፈቅድላቸው ሆኖ ሲገኝ ነው::በሶስተኛ ደረጃ መነሳት ያለበት ነጥብ የሚች ተተኪ ወራሾች ከውርሱ የሚደርሳቸው ድርሻ ትክክል ወይም እኩል አለመሆኑን ነው:: የሚች ተተኪ ወራሾች ከውርሱ ንብረት የሚወስዱት ድርሻ እነርሱ የተኩት ሰው ሊያገኝ የሚችለውን ያህል ብቻ ነው ::

ለምሳሌ አቶ አበበ ሳህሉ የተባሉ ሰው በሕይወት ዘመናቸው ወንድይፍራው አበበ እና አልማዝ አበበ የተባሉ ልጆች ቢወልዱና ወንድፍራው አበበ አራት ልጆች ከወለደ በኋላ ከአባቱ ከአቶ አበበ ሣህሉ በፊት ቢሞት አልማዝ አበበ ደግሞ አንዲት ልጅ ከወለደች በኋላ ከአባቷ ከአቶ አበበ ሣህሉ በፊት ብትሞት ፣ሚች አበበ ሣህሉ ከዚህዓለም በሞት በሚለዩበት ጊዜ ከወንድ ልጃቸው አራት የልጅ ልጆች ከሴት ልጃቸው አንዲት የልጅ ልጅ በድምሩ በውርሳቸው ተካፋይ የሚሆኑ አምሥት ተወላጆች አሏቸው:: ሆኖም የሚች ውርስ በሚከፋፈልበት ጊዜ፣ ሁሉም ተወላጆች የሚችን ንብረት ለአምሥት እኩል ተከፋፍለው እያንዳንዳቸው ከሚች ውርስ ንብረት አንድ አምስተኛውን መውሰድ አይችሉም:: የሚች ወንድፍራው አበበ ልጆች ከሚች ውርስ አባታቸው አቶ ወንድፍራው ቢኖር የሚደርሰውን ድርሻ ማለትም የውርሱን ግማሽ ንብረት በመውሰድ ለአራት የሚካፈሉ ሲሆን፣ የአልማዝ አበበ ልጅ ደግሞ በእናቷ ተተክታ እናቷ ከውርሱ ልታገኝ የምትችለውን ግማሽ ሐብት ብቻዋን ትወስዳለች::

እንደዚሁም ከላይ ያነሣነውን ስለ ወራሽነት መብት መተላለፍ እና የተተኪነት ዕንሰ ኃሣብ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የሚከተለውን ምሣሌ ማየት ይቻላል::አቶ አበበ ዓለሙ የተባለ ሰው ደበበ እና ተስፋየ የሚባሉ ልጆች ነበሩት:: ደበበ አባቱ ከመሞቱ ከአንድ ዓመት በፊት ጉዳይ ዓጭጭና ሰለሞን ዓጭጭ የተባሉ ልጆችን ወልዶ ሞተ:: ተስፋየ ደግሞ አባቱ ከሞተ ከሁለት ቀን በኋላ የሞተ ሲሆን ልጅ ወይም የልጅ ልጅ የለውም:: የደበበ ልጆች በሚች አበበ ውርስ አባታቸውን ተክተው በወራሽነት የሚጠሩ ሲሆን፣ ተስፋየ ደግሞ የወራሽነት መብቱን አረጋግጦ ስለሞተ የእሱ ወራሾች አለሙና ዓለሚቱ የተስፋየን የወራሽነት መብት በመጠቀም፣ የእሱን ድርሻ ከአበበ ውርስ ላይ ይወስዳሉ::

ተስፋየ ከአበበ ቀድሞ ቢሞት ኖሮ ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ስለሌለው እሱን ተክቶ በአበበ ውርስ የሚካፈል ሰው አይኖርም። በመሆኑም የአበበ ንብረት በሙሉ ደበበን ተክተው በውርሱ ለሚቀርቡት ለጉዳይና ለሰለሞን ይሰጥ ነበር። ስለዚህ ተተኪነት እና የወራሽነት መብት ማስተላለፍ ፅንሰ ኃሣብም ሆነ በውጤት ደረጃ የተለያየ ውጤት ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ሌላው መታየት ያለበት ሚች የጉድፍቻ ልጅ እንደ ሚች የሥጋ ልጅ ተቆጥሮ በሚች ውርስ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሆኖ እንደሚጠራና ከውርሱ የሚደርሰውን ድርሻ ከሚች ልጆች ጋር ትክክል እንደሚሆን መገንዘብና፣ከ ሚች ሌሎች ልጆች ወይም ተወላጆች ከሌሉት ጠቅላላ የውርሱን ንብረት እንደሚወስድ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 557 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842 ድንጋጌ ለመረዳት የሚቻል መሆኑን ነው።በአጠቃላይ ሚች በሕይወት ዘመኑ በሕግ ውጤት ያለው ኑዛዜ ያልተወ እንደሆነ የሚች ተወላጆች፣ ወይም የጉድፍቻ ልጆች ወይም ተተኪዎች የእነርሱ በወራሽነት ሊካፈሉ እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ያስቀምጣሉ። ስለዚህ የሕጉን ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት እንደዚሁም አተረጓጐም ትኩረት በመስጠት በማጥናት ተግባራዊ ካልተደረጉ በአፈጻጸም ወቅት የሚከሰተው ችግር በቀላሉ የሚስተካከል አይደለም። ሰዎችንም ለአላስፈላጊ መጉላላት እና መንከራተት የሚዳርግ ይሆናል። ይህንንም ለማሣየት ከዚህ ባሚጸተለውት ፡ ቭ በልዕራፍ መጨረሻ ላይ የቀረበውን የፍርድ ቤት ውሣኔ በአፅንኦት እንዲከታተሉት ይመክራሉ።

የተተኪነት ወራሽ ስለመሆን በተመለከተ ለሰዎች አሁንም የመከራከሪያ ነጥብ እንደሆነ የደቡብ ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 04033 ታህሣሥ 27 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማየት ለመረዳት ይቻላል። የክርክሩ መነሻ መመህር ሞገስ አለነ በጠበቃ እያታገዙ ያረቡት ማመለከቻ ሲሆን ይዘቱም ወላጅ እናቴ ወሐሮ እማዋይ አለመኔ 1966 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይታለች። የእናቴ እናት የሆነችው ወሐሮ ሁሉአገር ውበቴ ደግሞ በ1989 ዓ.ም ከዚህ ዓአለም በሞት ተለይተዋል። አያቴ ወሐሮ ሁሉአገር ውበቴ በወረታ ከተማ የሠራችው መኖሪያ ቤት ያላት ሲሆንቤቱን የእናቴ እህት የሆነችው ወሐሮ አሰፉ አዳነ ከባለቤታቸው ከዶክተር ሞገስ አለነ ጋር በመሆን በውርስ የወሰዱት ስለሆነ እኔ አያቴን በእናቴ በወሐሮ እማዋይ አለምኔ ምትክ በመሆን ወራሽ ስለሆንኩኝ የቤቱ ግምት ርማሹ ይገባኛል በማለተ ክስ ያቀረባል። በዚህ ጉዳይ አንደኛ ተከሣሽ የሆነውንና የወሐሮ አሰፉ አዳነ ባለቤት የሆኑት ዶሐር ሞገስ ጥሩነህ በጠበቃቸው አማካኝነት ባቀረቡት

መልስ ሟችን ለመውረስ በመጀመሪያ የሟች ውርስ ሲከፈል በሕይወት መሃር አስፈላጊ ነው፡፡ የእሱ አናት ወሐሮ ሁለአገር ውበቱ ከመሞታቸው ከሃያ ሶስት አመት በፊት ቀድማ የሞተች ስለሆነ የከሣሽ እናት ሟች ወሐሮ ሁሉአገርን ወርሣ አልሞተችም፡፡ በመሆኑመ የከሣሽ እናት የፍተሐብሐር ሕግ ቁጥር 830 በሚደነግገው መሠረት ወሐሮ እማዋይ ከወሐሮ ሁሉአገር በፊት ስለሞተችና በፍትሐብሐር ሕግ ቁጥር 832 መሠረት ወራሽነቷን አረጋግጣ ሰላልሞተች ከሣሽ ወራሽ መሆን አይችሉም በማለት የተከራከረ ሲሆን ሁለተኛዋ ተከሣሽና ከሣሽ ወራሽ መሆን አይችሉም በማለት የተከራከረ ሲሆን ሁለተኛዋ ተከሣሽና የከሣሽ አክስት የሆነችው ወሐሮ አሠፉ አዳነ ከሣሹ ከሟች አያቱ ውርስ የእናቱን ድርሻ ሊወስድ ይገባዋል በማለት ክሱን አምና ተከራክራለች፡፡

ፍርድ ቤቱም ከሣሽ በወሐሮ ሁሉአገር ውበቱ ውርስ ጉዳይ ክስ ለመመስረት የሚያስችለው መብት አለው ወይስ የለውመ የሚለውን ጭብጥ ካወጣ በኋላ በሰጠው ውሣኔ፣ በክርክሩ ሂደት እንደተዳነው የከሣሽ አያት ወሐሮ ሁሉአገር ውበቱ መሆናቸው አልተካደም፡፡ የከሣሽ እናት ደግሞ ወሐሮ እማዋይ አለምኔ መሆናቸው የከሣሽ አየት በቸኛ ወራሾች ደናሞ የከሣሽ እናትና ሁለተኛ ተከሣሽ መሆናቸው በግራ ቀኙ የተካድ ነጥቦች አይደሉም፡፡ ከዚህ በመነማት የከሣሽን መብት ስንመለከት ከሣሽ ያቀረበው ጥያቄ የምትክ ወራሽነት ነው፡፡ አንደኛ ተከሣሽ አጥብቆ ያነሣው የመከራከሪያ ነጥብ ይህንኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ በፍትሐብሐር ሕግ ቁጥር 842 -3? ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ከሟች ልጆች የሚወርሰው ንብርት ባለ ጊዜና እሱ አስቀድሞ የሞተ እንደሆነ በእሱ እግር ተተክተው ተወላጆች መውረስ እንዲችሉ የተደነገገ መሆን ነው፡፡ አንደኛ ተከሣሽ እዚህ ላይ ያቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ የከሣሽ እና ከከሣሽ አያት ቀድማ የሞተች ስለሆነ አልወረሰችም፡፡ ምክንያቱም ለመውረስ በፍትሐብሐር ሕግ ቁጥት 830 መሠረት መጀመሪየ ሟች ሲሞት በህይወት መኖር አለበት፡፡ እናቱ ሣትወርስ ከሞተች ደገሞ ተከሣሽ እናቱ የሌላትን መብት ስለማይወርስ ክስ የማቅረብ ስልጣን የለውመ የሚል ነው፡፡ በእርግጥ ነው በፍትሐብሐር ሕግ ቁጥር 830 ላይ አንድ ሰው ለመውረስ ተወራሹ ሲሞት በህይወት መገኘት አለበት፡፡ ወደ ፍትሐብሐር ሕግ ቁጥር 842 -3? ስንመጣ ደግሞ አንድ የሟች ልጅ ሟችን ተክቶ መውረስ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ እንደዚህ የሉ እርስ በርሣቸው የሚቃረኑ የሚመስሉ ትርጉም በምናስታርቅበት ጊዜ ደገሞ ሁለቱን

ድንጋጌዎች ስራ ላይ እንዲውሉ -_____? እንደሆነ አድርጐ መተርጐም ያስፈልጋል፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 መሠረት ተወራሹ ሲሞት ወራሽ በህይወት ከሌለ መውረስ አይችልም ካልን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842 -3? ስራ ላይ የሌለው አንቀጽ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842-3? መተርጐም የሚገበው በአንደኛው ተከሣሽ አተረጓጐም ማይሆን መጀመሪያ ሣይወርሱ የሞቱና እርሱ ደገሞ ወራሽ ልጆች ትተው ላለፉ ተወራሾች ነው፡፡ በዚህ አተረጓጐም መሠረት ከሣሽ እሃቱን ተክቶ የአየቱን ንብረት የመውረስ መብት ስላለው ክስ ማቀረብ ይችላል፡፡ ሁለተኛዋ ተከሣሽና የሚች ወሐረ ሁለአገር ልጅ ይህንን አልካደችም ስለሆነም አንደኛው ተከሣሽ በዚህ ረገድ ያቀረበው መከራከሪያ ነጥብ የህግ ድጋፍ የለውም፣ በማለት ሌሎች ነጥቦችንም አንስቶ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

እዚህ ላይ የሚታየው ማችን ለመውረስ በህይወት መሃር አስፈላጊ ሲሆን ወደታች የሚቆጠር ተወላጆች ያሏቸው ሰወች ሚች ሲሞት በህይወት ባይኖሩም ተወላጆቻቸው እነርሱን በመተካት በሚች ውርስ የሚካፈሉበት የውርስ ስርዓት በአገራችን ሕግ የተፈቀደ ነው፡፡ ምክንያቱም አሁን ያለን የውርስ ሰርዓት ሚች ኑሣዜ ከሌለው ውርሱ የእሱ የቅርብ የስጋ ዘመድ የሆነው እንዲያገኝ የሚፈቅድ ነው፡፡ ስለዚህ የሚች ውርስ ሲከፈት በህይወት መኖር ሚችን ለመውረስ አስፈላጊ መሆን በመርህ ደረጃ ቢቀመጥም በህይወት ቢኖር ኖሮ በሚች ውርስ የመካፈል እድል የነበረው ሰው ተወላጆች እሱን ተክተው በሚች ውርስ የሚካፈሉበት የውርስ -ርጽፐረጽሰጽነተድተፀሸጽ ስጭቸቸጽሰሰፀጸነ? ስርዓት በልዩ ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ይህንን መገንዘብና ሁሉንም የሕግ ድንጋጌዎች ተግባር ላይ ማዋል ልንከተለው የሚገባን የሕግ አተረጓጐም ዘዴ ነው፡፡

ለ. በሁለተኛ ደረጃ የሚጠሩ የሚች ወራሾች

ከላይ እንደተገለፀው ሚች ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች የጉዲፈቻ ልጅና ተወላጆች የሌለው እንደሆነ፣ የሚች እናት እና አባት የሚች ወራሾች ይሆናሉ፡፡ በውርሱም የሚች እናት እና አባት የሚችን እናት እና አባት ከእሱ ቀድመው ከሞቱ የእነርሱ ተወላጆች ማለትም ወንድሞቹና እህቶቹ ወይም የወንድሞቹ እና የእህቶቹ ተወላጆች እናትና አባቱን በመተካት በሚች ውርስ እንደሚካፈሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 843 እና 844 የሚደነግጉ ሲሆን ከሚች እናት እና አባት በአንዱ መስመር ወራሽ ቢታጣ

የሚች ውርስ ወደ ሌላው መስመር በሙሉ ሊተላለፍ እንደሚችል ከላይ የጠቀስናቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡ ሁኔታውን በምሣሌ ለማስረዳት ሚች አበበ ተስፋዬ ወራሽ የሚሆኑ ተወላጆች የሌሉት ከሆነ እናትና አባቱ በሁለተኛ ደረጃ ወራሽነት በውርሱ ላይ ይካፈላሉ፡፡ እነርሱ ከሌሉ ወንድሞቹ ወይም እህቶቹ በተተኪነት በእርሱ ውርስ ይካፈላሉ፡፡ ከእናቱ ሚችን ብቻ የወለዱ ቢሆንና አባቱ ከሌላ ሴት አንድ ልጅ ቢወልዱ በእናቱ መስመር ተተኪ ስለሌለ ውርሱ ወደ አባቱ ልጅ ተጠቃልሎ ይሄዳል ለማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ አከራካሪ የሚሆነው የጉድፍቻ ልጅ የሆነ ሰው በሞት ቢለይና ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ባይኖሩት ወራሾቹ እነማን ይሆናሉ የሚለው ጥያቄ ነው፡፡የጉድፍቻ ልጅ በማናቸውም አስተያየት እንደ ጉድፍቻ አድራጊው ልጅ እንደሚቆጠር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 557 በአንድ በኩል የሚደነግግ ሲሆን በሌላ በኩል የጉድፍቻ ልጅ ከጥንት ቤተዘመዶቹ ወይም የስጋ ወላጆቹና ዘመዶቹ ጋር ያለውን የዝምድና መተሣሠር እንደያዘ እንደሚኖር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 559/1/ ይደነግጋል፡፡ ይኸም በመሆኑ የጉድፍቻ ልጅ በሁለት አይነት መንገድ የሚያገኛቸው ወላጆች አሉ፡፡ ይኸውም በጉድፍቻ ውል መሠረት ያገኛቸው ወላጆች እና በደም የሚተሣሰሩት የሥጋ እናትና አባቶቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የጉድፍቻ ልጅ ሲሞት ወደታች የትሸቀጠሩ ተወላጆች ባይኖሩት የሚች ወላጆች ስለሆነ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 843 መሠረት ወራሾች ነን ብለው የስጋ ወላጅ እናትና አባቱና የጉድፍቻ ወላጆች የሆኑት እናትና አባቱ ይቀርባሉ፡፡ በማናቸውም ሁኔታ ከጉድፍቻ ቤተዘመድ እና ከጥንት ቤተዘመድ መካከል ምርጫ ማድረግ አሰፈላጊ በሆነ ጊዜ የጉደፍቻ ቤተዘመድ ቅድሚያ እንደሚያገኝ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 559 የሚደነግግ ቢሆንም ይኸ የሕግ ድንጋጌ በውርስ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም የሚለው ነጥብ በራሱ አከራካሪ ነው፡፡ ምንያቱም የስጋ ዘመዶቹንም ሆነ የጉድፍቻ ዘመዶቹን ወራሽ አድርጐ የሚችን ሀብት ግማሹን ለስጋ ዘመዶቹ ግማሹን ደግሞ ለጉድፍቻ ዘመዶቹ ማከፋፈል ስለሚቻል በውርስ ጊዜ ከሁለቱ መካከል ዓቃባቃ ምርጫ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ሕጉ በጉድፍቻ ቤተዘመድ ቅድሚያ እንዳሰጥ የሚደነግገው ሁለቱንም በእኩል ለማሣተፍ በማይችሉበት ሁኔታ አንዳቸውን መምረጥ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው በማለት የሚከራከሩ ያሉ ሲሆን በሌላ በኩል ሚች ተወላጅ ከሌለው ወራሾች የሚሆኑት ወላጆቹ ናቸው የሚለውን ቅግ ለማስፈጸም ከጥንት ቤተዘመዶቹና ከጉድፍቻ ዘመዶቹ መምረጥ አስፈላጊ ስለሆነ ወራሽ መሆን ያለባቸው የጉድፍቻ ዘመዶቹ ናቸው በማለት

የሚከራከሩ ስላሉ ተማሪዎች ከሁለቱ አተረጓጐም ሚዛናዊ ነው ብለው የሚያስቡትን በውይይት እንዲያዳበሩ ይጠበቃል።

ሐ. በሶስተኛ ደረጃ የሚጠሩ የሚች ወራሾች

የሚች ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆቹ ወይም የሚች እናትና አባት ወይም የእነርሱ ተተኪዎች የሆኑ ወንድሞቹና እህቶቹ ወይም የእነርሱ ተወላጆች የሌሉ እንደሆነ፣ አያቶቹ የሚች ወራሾች ይሆናሉ። የሚች አያቶች የሌሉ ከሆነ የእነርሱ ተወላጆች ማለትም አጐቶቹና አክስቶቹ ወይም የእነርሱ ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆች የሚች ተተኪ ወራሾች እንደሚሆኑና የሚች ንብረትም ግማሹ ለአባት መስመር ግማሹ ለእናት መስመር ሊተላለፍ እንደሚችል በአንዱ መስመር ወራሽ ከታጣ የሚች ንብረት በሙሉ ለሌላው መስመር ሊተላለፍ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 845 እና 846 ይደነግጋሉ።

መ. በአራተኛ ደረጃ የሚጠሩ የሚች ወራሾች

ሚች በሦስተኛ ደረጃ ሊጠራ የሚችል ወራሽ የሌለው እንደሆነ የሚቹ ቅድመ አያቶች ወራሾች ይሆናሉ። ቅድመ አያቶቹ ኛክሕክኽ እንደሆነ የቅድመ አያቱ ተወላጆች የእሱን ቅድመ አያቶች በመተካት በሚች ውርስ ተካፋይ ይሆናሉ። ውርሱም በአባት መስመር ያለው እኩሌታ በእናት መስመር ያለው ደግሞ እኩሌታ የሚከፈል ሲሆን በአንዱ ቅድመ አያቱ በኩል ወራሽ ያልቀረበ እንደሆነ ውርስ ለሌላው ቅድመ አያቶቹ ወይም ለእነርሱ ተወላጆች እንደሚተላለፍ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 847 እና 848 ይደነግጋሉ።በአጠቃላይ የሥጋ ዝምድናን /ትውልድን/ መሠረት አድርጐ የሚፈፀመው የሚች ውርስ ሥርዓት በሥዕላዊ መግለጫ መልክ ተሰርቶ ሲታይ የሚከተለው መልክ

የእናት መስመር				የአባት መስመር			
ወንድ ቅ.አያት እና ተተኪዎቻቸው	ሴት ቅ.አያት እና ተተኪዎቻቸው	ወንድ ቅ.አያት እና ተተኪዎቻቸው	ሴት ቅ.አያት እና ተተኪዎቻቸው	ወንድ ቅ.አያት እናተተኪዎቻቸው	ሴት ቅ.አያት እናተተኪዎቻቸው	ወንድቅ. አያት እና ተተኪዎቻቸው	ሴት ቅ.አያት እናተተኪዎቻቸው

ይኖረዋል።

የሚች ወንድ አያት እናተተኪዎ ቻቸው	የሚች ሴት አያት እናተተኪዎ ቻቸው	የሚች ወንድ አያት እናተተኪዎ ቻቸው	የሚች ሴት አያት እናተተኪዎ ቻቸው
አባት እና ተተኪዎቻቸው		እናትና ተተኪዎቻቸው	
ሚች			
የሚች ልጆች እና ሌሎች ተወላጆች		1ኛ ደረጃ ወራሾች	

ከላይ የተመለከቱት ወራሾች ወይም የእነርሱ ተተኪዎች ተወላጆች በሌሉ ጊዜ ሚች ወራሽ የሥጋ ዘመድ እንደሌለው ተቆጥሮ የውርሱ ንብረት ለመንግሥት ገቢ ሊሆን እንደሚገባው የፍትሐብሔር ሕግ 851 ይደነግጋል።

በመጨረሻም ማየት የሚገባን ነጥብ የምትክ ወራሾችን አስመልክቶ በሕጉ የተቀመጡ ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ማየት ይገባል። የመጀመሪያው ወራሹ ሆኖ ወራሽነቱን አልፈልገውም በማለት ማረጋገጫ በሰጠ ወራሽ ተተኪ ሊገባበት የማይችል መሆኑ ነው። ለምሳሌ አምላሉ በሕይወት እያለ የአባቱ የአቶ ሽመልስ ውርስ ተከፍቶ ውርሱ በሚጣራበት ጊዜ አምላሉ የአባቱን የአቶ ሽመልስን ውርስ እንደማይፈልገው በጽሑፍ አሳወቀ። ከዚህ በኋላ አምላሉ ውርሱ ከመከፋፈሉ በፊት ቢሞት የአምላሉ ልጆች አምላሉን ተክተው በአያታቸው በአቶ ሽመልስ ውርስ በወራሽነት ሊቀርቡ እንደማይችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 854/1/ ይደነግጋል። ይኸም የሚሆነው ተተኪዎች ምን ጊዜም የወራሽነትን መብቱን የሚጠቀሙት ምትክ በሆኑለት ሰው እግር በመተካት በመሆኑ ነው። ወራሹ የወራሽነት መብቱን አልፈልገውም ካለ የእሱ ተተኪዎች የሚተኩት የወራሽነት መበት ስለማይኖር ዋናው ወራሽ አልፈልገውም ባለው ውርስ ላይ ተተኪዎች እን ፈ ቡ አይፈቀድላቸውም።

በሌላ በኩል ውርሱን አልፈልገውም የተባለውን ሰው ተክተው ለመግባት እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 863/2/ ይደነግጋል። ይኸ ማለት ከላይ ካየነው ምሳሌ ጋር ብናገናዝበው በአቶ ሽመልስ ውርስ አልፈልገውም ያለው አምላሉ ከሞተ በኋላ የአቶ ሽመልስ እና ወ/ሮ ሸዋየ ቢሞቱ፣ የአምላሉ ልጆች በአቶ ሽመልስ ውርስ ላይ በተተኪነት ወራሽነት ለመቅረብ አይችሉም። ነገር ግን በቅድመ አያታቸው በወ/ሮ ሸዋየ ውርስ ላይ ውርሱን አልፈልገውም የተባለውን የአያታቸውን አቶ ሽመልስ

ተወላጆች በመሆናቸው የአምሣሉ ልጆች አያታቸውን አቶ ሽመልስን በመተካት በቅድመ አያታቸው በወ/ሮ ሸዋየ ውርስ እንደሚሣተፉ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 854/2/ ለመረዳት ይቻላል::ከዚህ በተጨማሪ ከወራሽነት ያልተገባ ነው የተባለ ሰው ልጆች ወይም ተወላጆች በእሱ ተተኪ ሆነው ሟችን ሊወርሱ እንደማይችሉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 855 በግልጽ የተደነገገ መሆኑን ግንዛቤ መያዙ ጠቃሚ ነው::

ከሟች ጋር የስጋ ዝምድና ሣይኖራቸው ወይም በጉድፍቸ ውል መሠረት ሕግ የሚያስቀምጠው አግባብ ሣይተሣሠሩ የስጋ ዝምድናንና ወራሽነትን አስመልክቶ በሚነሱ ክርክሮች ላይ የበለጠ ግንዛቤዎችን ለማዳበር ይረዳ ዘንድ የሚከተለውን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 152ሐ87 የካቲት 10 ቀን 1991 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ ማየቱ ጠቃሚነት ይኖረዋል። ክርክሩ የተነሣው ይግባኝ ባይ ወሐሮ ጤና ገሠሠ እናመ ልስ ሰጭዎተ ወሐሮ ውጭት ገሠሠ አና ሙሉየ ገሠሠ መካከል ነው። ይግባኙ የቀረበው የሰሜን ጐንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት መጋቢት 29 ቀን 1987ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው። የክርክሩ መነሻ የሟች የእማሆይ ስመኝሽ ወርቁ ወራሽነት ጥያቄ ነው። የአሁን ይግባኝ ባይ በጐንደር ወረዳ ፍርድ ቤት በስራ ፋይል መዝገብ ቁጥር 47/81 እናቴ እማሆይ ስመኝሽ ወርቁ ነሐሴ 28 ቀን 1979ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየች ስለሆነ ወራሽነቴ ይረጋገጥልኝ በማለት አብትታ አቅርባ የወረዳው ፍ/ቤት ተቃዋሚ እንዳለ እንዲቀርብ ጥሪ አድርጐ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ አራት ምስክሮች አቅርባ አሰምታለች። የቀረቡት አራት ምስክሮች እማሆይ ስመኝሽ ወርቁ የጤና ገሠሠ እናት ናት በማለት ስለመሰከሩ ፍርድ ቤቱ ጤና ገሠሠ የሟች ስመኝሽ ወርቁ ወራሽናት በማለት ሕዳር 24 ቀን 1981ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል።

መልስ ሰጭዎች በበኩላቸው ሟች እማሆይ ስመኝሽ ወርቁ ያሣደገችው መሆኑን ገልፀው ነሐሴ 1 ቀን 1975ዓ.ም ባደረገችው ግልጽ ኑዛዜ ከባሏ ከአቶ ካሣ ገሠሠ ጋር ያፈራችውን የጋራ ንብረት የእሷ ድርሻ እና የግል ንብረቷ ጠቅላላ ወራሽ እንድንሆን የሾመችን ስለሆነ የሟች የኑዛዜ መሆናችን ይረጋገጥልን በማለት በስራ ፋይል መዝገብ ቁጥር 321/84 አመልክተዋል። ከዚሁ ጋር በማያያዝ እማሆይ ስመኝ ወርቁ በአምስት ምስክሮች ፊት ነሐሴ 1 ቀን 1975ዓ.ም ያደረጉትን ኑዛዜ አቅርበዋል::የወረዳው ፍርድ ቤት ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ አድርጓል በዚህ መሠረት የአሁን ይንባኝ ባይ በተቃዋሚነት ቀርባ የሟች እማሆይ ስመኝሽ ወርቁ ወራሽ እኔ መሆኔ በስራ ፋይ

መዝገብ ቁጥር 47/81 በዚሁ ወረዳ ፍርድ ቤት ሕዳር 24 ቀን 1981 የተረጋገጠ በመሆኑ በበሀሰት በተዘጋጀ ኑዛዜ ወራሽነታችን ይታወቅልን በማለት መዝገብ ማስከፈታቸው ተገቢ ስላልሆነ ይሻርልን በማለት ተቃውሞዋን አቅርባለች::መልስ ሰጭወች በበኩላቸው ተቃዋሚዋ ከእማሆይ ስመኝሽ ወርቁ ጋር ምንም አይነት የደምትስስር ሣይኖራት በበሀሰት የሚች ልጅ ነኝ ብላ በማስመስከሯ ወራሽነቷን ማረጋገጣቀን አውቀናል በመሆኑም እኛም ለመቃወም የሚያስችላት መብት የሌላት ከመሆኑም በላይ በሀሰት ምስክርነት የወሰደችውን የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ልትመልስ ይገባታል በማለት ተከራክረዋል::የግራ ቀኙን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት መልስ ሰጭዎችን ይግባኝ ባይ ወራሽ ነኝ በማለት ስታመለክት የኑዛዜ ጽሑፍ ይዘው ቀርበው ስላልተቃወሙ ከዚህ በኋላ የሚች ወራሽ ነን ብለው መጠየቃቸው ተገቢ ስላልሆነ ጥያቄአቸውን አልተቀበልኩትም በማለት አሰናብቷቸዋል::

መልስ ሰጭዎች በዚሁ ውሣነ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፈርድ ቤት አቅርበዋል:: የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ መልስ ሰጭወች የሚች እማሆይ ስመኝሽ ወርቁ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው ይግባኝ ባይንም ቀደም ሲል የተሰጣትን የወራሽነት ማስረጃ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1 በሚደነግገው መሠረት በሶስት ዓመት ውስጥ ቀርበው ስላልተቃወሙ ለይግባኝ ባይዋ የተሰጠው የወራሽነት ማስረጃ እንደፀና ይቆያል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል::ይግባኙ የቀረበው ይህንን ውሣኔ በመቃወም ነው:: ይግባኝ ባይ ሚች እማሆይ ስመኝሽ ወርቁ ለመልስ ሰጭዎች የደረጉት ኑዛዜ በውል አዋዋይ መስሪያ ቤት ፊት ስላልተፈፀመ የወራሽነት ጥያቄው የይርጋ ጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ በመሆኑና መልስ ሰጭዎች የሕግ ምስክሮች አቅርበው ስለአስመሰከሩ አላግባብ የወራሽነት ማስረጃው በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጣቸው ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክታለች::

መልስ ሰጭዎች በበኩላቸው ይግባኝ ባይ የእማሆይ ስመኝ ወርቁ ልጅ አይደለችም የሀሰት ምስክርነት አቅርባ የወራሽነት ማስረጃ መውሰዷ ሣያንሣት እኛን ለመቃወም የሚያስችላት ሕጋዊ መብት የላትም:: የይግባኝ ባይ ወላጅ እናት እማሆይ አዋጉ ተዋበ በሕይወት ይኖራሉ እኛ የሚች የኑዛዜ ወራሾች ነን:: ስለዚህ የይግባኝ ባይን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተን በማለት መልስ ሰጥተዋል::ይግባኝ ባይ መልስ አቅርባለች ይዘቱ ከይግባኙ ቅሬታው ጋር ተመሣሣይ በመሆኑ አልገለበጥነውም::በስርና በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ከላይ የተለገፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን

መርምረናል መዝገቡን እንደመረመርነው /1/ ይግባኝ ባይ የመልስ ሰጭወችን የኑዛዜ ወራሽነት ለመቃወም የማያስችላት ሕጋዊ መብት አላት ወይስ የላትም::

/2/ መልስ ሰጭዎች የሚች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው መባሉ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም የሚሉትን ነጥቦች ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል::የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ይግባኝ ባይ በዚህ መዝገብ ሁለት የወረዳ ፍርድ ቤት ውሣኔ በማስረጃነት አያይዛለች:: የመጀመሪያው የወረዳው ፍርድ ቤት በስራ ፋይል መዝገብ ቁጥር 253/75 በአቶ ገሠሠ ካሣ ውርስ ግንቦት 2 ቀን 1975 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ነው:: ይህ ውሣኔ እማሆይ ስመኝ ወርቄ የሚች ገሠሠ ካሣ ሚስት መሆናቸውን ይግባኝ ባይዋ ደግሞ አቶ ገሠሠ ካሣ ከማሆይ ስመኝ ወርቄ ሣይሆን ከሌላ ሴት ይግባኝ ባይዋ ጤና ገሠሠ የተወለደች ልጃቸው መሆኗን የሚያረጋግጥ ነው:: በዚህ ውሣኔ በግልጽ እንደተመለከተው ይግባኝ ባይ የሚች እማሆይ ስመኝ ወርቄ የስጋ ልጅ አይደለችም::

ሁለተኛው ይኸው የጐንደር ወረዳ ፍርድ ቤት በስራ ፋይል መዝገብ ቁጥር 47/81 የአራት ምስክሮችን ቃል ከሰማ በኋላ ይግባኝ ባይዋ ጤና ገሠሠ የእማሆይ ስመኝ ወርቄ ልጅና ወራሽናት በማለት የሰጠው ውሣኔ ነው::ይህ ውሣኔ የተሰጠው በሁለት የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግና ይግባኝ ባይ 1975ዓ.ም በወረዳው ፍርድ ቤት የአባቷን ወራሽነት ለማረጋገጥ ያቀረበችውን ማስረጃ ባለመገናዘብ ነው:: በአጠቃላይ የይግባኝ ባይ ወላጅ እናት እማሆይ ስመኝ ወርቄ እንደሆኑ ከመሞታቸው በፊት 1975ዓ.ም ይግባኝ ባይ እና ሚች ስመኝ ወርቄ በአንድ ላይ ባስከፈቱት መዝገብ ተረጋግጧል::ስለዚህ ይግባኝ ባይ ከሚች እማሆይ ስመኝ ወርቄን ያለኑዛዜ የምትወርስበት የስጋ ዝምድናና የደም ትስስር የላትም ይግባኝ ባይ የሚች ልጅ ሣትሆን ልጅ ነኝ በማለት በወራሽነት መቅረቧ ተገቢ ባለመሆኑ የመልስ ሰጭወችን የኑዛዜ ወራሽነት በመቃወም ክርክር የምታቀርብበት ሕጋዊ ምክንያት የላትም::

በመሆኑም መልስ ሰጭዎች የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን በመቃወም ይግባኝ ስላላቀረቡ ወይም የይግባኝ ባይ ይግባኝ እንደደረሣቸው የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት መስቀለኛ ይግባኝ ባለመቅረባቸው ይግባኝ ባይ የሚች እማሆይ ስመኝ ወርቄ ወራሽናት በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሸር ወይም ለማሻሻል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ስለማይፈቅዱ እንዳለ የተውነው ሲሆን ይግባኝ ባይዋ ሚችን ለመውረስ የሚያስችላት ሕጋዊ ሁኔታ ሣይሆር የሚችን የኑዛዜ ወራሾች ተቃዋሚ ሆኖ መቅረቧና በይግባኝ መከራከሯ ተገቢ ሆና አላገኘነውም::

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ መልስ ሰጭዎች የሚች እማሆይ ስመኝ ወርቁ ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሚች በግልጽ ያደረገችው ኑዛዜ በማስረጃነት ቀርቧል። የኑዛዜው ጽሁፍ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተመለከቱትን ፎርማሊቲዎች የሚያሟላና የሚች ትክክለኛ ቃል መሆኑን የማያሣይ በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት መልስ ሰጭዎች የሚች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል።ከዚህ በማስከተል የማነሣው ጥያቄ ይግባኝ ባይ የሚች ልጅ ነኝ በማለት የተሰጣትን የወራሽነት የምስክርነት ወረቀት መልስ ሰጭዎች ባለመቃወማቸው ይግባኝ ባይ የሚች የሕግ ወራሽ ሆናለች። በሌላ በኩል መልስ ሰጭዎች የሚች የኑዛዜ ወራሾች ናቸው ተብሏል። ስለዚህ ይግባኝ ባይና መልስ ሰጭዎች በሚች ውርስ ላይ ያላቸው መብት እንዴት ነው የሚለውነው።

ይህንን ነጥብ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ስንመለከተው የሚች ውርስ በከፊል በኑዛዜና በከፊል ያለኑዛዜ ሊፈፀም እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 829/2/ ያመለክታል። በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረት ይግባኝ ባይ የሚች ያለኑዛዜ ወራሽ ስትሆን መልስ ሰጭዎች ደግሞ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው። ሚች መልስ ሰጭዎችን ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ በማድረግ የሾማቸው በመሆኑ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ተቀባይ ያገኘ ሰው ያለኑዛዜ ወራሽ እንደሆነ እንደሚቆጠር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 915/1የተደነገገ በመሆኑ ከላይ በጠቀስናቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የሚች እማሆይ ስመኝ ወርቁ ንብረት፣ ይግባኝ ባይዋ ወ/ሮ ጤና ገሠሠ አንደኛ መልስ ሰጭ ወ/ሮ ሙጭት ገሠሠ ሁለተኛ መልስ ሰጭ ተማሪ ሙሉየ ገሠሠበወራሽነታቸው ቀርበው እኩል መካፈል ይገባቸዋል በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል በማለፍ ወስ_ል።

ጸውሣቷው ትተምትረ ው ጸሚኖ ር ምትም አቨትፍ ባስ ዝምታ ወቨም ባ ኑታዎኖ ውል መሠረፍ ትባቨትፍ ባሌላ ው ሰዎኖ ባሚኖ ቨለ ትዛዜ ወራሽ ትፆ በማለፍ በሚቀርቡበፍ ሁት መ ሩት ሲሆት በሌላ በጾል አትታ ተጸራካሪት አስመልክ ፡ ብት በስር ቨባው ዎርታ ቤፍ ባሰነ ው ውሣት ጸሥት ሥርዓፍ ሕ ፡ መሠረፍ ቨ ባፆ ወቨም መስቀለቾ ቨ ባፆ ካልቀረበበፍ ባሥር ዎርታ ቤፍ ባሰነ ው ውሣት መሠረ ዊ ስህተፍ ቢ ርበፍም ቨ ባፆ ሰሚው ዎርታ ቤፍ በራሱ አትሣሽትፍ ባማቨሸረው መሆትት ነው። በአነ ቃላቨ ባሚኖ ውርስ አስመልክ ጸሚትሡፍ በርካ አለመ ባባ ኖ ባሚኖ ቨለ

ትዝዜ ወራሽ ትፖ በሚሉ ትኳ ቦኖ ዙሪቨ ባሚተረ በመሆት ባሕ ጎት ታት ኃዎኖ ዓላማ ቭዘፔ በአ ባቡ መረ ፔ ሥራ ላቭ ማዋል ቨስወል ል።

የሙከራ ጥያቄዎች

የዘር ሀረግን አስመልክቶ የሚደረገው የውርስ መብት በደረጃ ማስቀመጡ ምን ጠ ቀሜታ አለው ብለው ያስባሉ።

በዋና ወራሽነት እና በተተኪ ወራሽነት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው።

ሟችን በተተኪነት ለመውረስ የማይቻልባቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው።

የሟች ሚስት ወይም ባል የሟች ወራሽ የሚሆኑበትን ስርዓት መፍጠር ተገቢ ነው ብለው የስባሉሕ ምን ጠቀሜታና ጉዳት ይኖረዋልሕ

የሟች ቅድመ አያቶች የሟች አራተኛ ደረጃ ወራሽ መሆናቸው ተገቢነት አለው ብለው ያምናሉሕ

የደቡብ ጐንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መነሻ አድርገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 833 እና የፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 842-2?፣ 844-2?፣ 848-2?፣ እንደዚሁም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 853 -1? መካከል መሠረታዊ የሆነ ቅራኔ አለው ብለው ያስባሉሕ ለምንሕ

በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 849 የአባትን ለአባት ወገን የእናትን ለእናት ወገን የሚለው ድንጋጌ፣ መሠረታዊ ዓላማና የተፈፃሚነት ወሰን አብራራሕ

የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 849 እፀ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1088 ድንጋጌዎች መካከል ያለው ተዛማጅና ለዩነት ምንድን ነው።

ከበደ ከአባቱ አንድ ሚሊየን ብር የሚወጣ ቤት በቁም ስጦታ አግኝቷል። ከበደ በድንገተኛ አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፣ ማዕዛ የተባለች ልጅ ነበረችው። ማዓዛ በአስር ዓመቷ ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ በአንደኛ ደረጃ ወራሽነት የሚጣራ ልጅ ወይም ሌሎች ተወላጆች አልነበራትም። የመዓዛ ወላጅ እናት ሐሩት የመዓዛ ወራሽ መሆኗን አረጋግጣ ቤቱን ለመረከብ ፍርድ ቤት ክስ ስታቀርብ የከበደ እህቶች ኬደነና ቤቱልሔም ቤቱን ከአባት ወገን በስጦታ የተገኘነ ስለሆነ የመዓዛ አና ሐሩት ሊሰጥ አይገባም በማለት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 849 ጠቅሰው ተቃውሞ አቀረቡ። እርስዎ ዳኛ ቢሆኑ ምን ይወስናሉ።

የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 849 ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 844 -3? በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 846-2? እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 851 ድንጋጌ ጋር እንዴት በመጣጣም ይተረጎማል።

ምዕራፍ አምስት

በሚች ኑዛዜ መሠረት የሚፈፀም ውርስ

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ
ስለ ኑዛዜ ምንነትና የኑዛዜ መሠረታዊ ባሕሪያት
ኑዛዜ ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች፣
ስለ ኑዛዜ ውድቅ መሆንና ስለኑዛዜ መሻር
ኑዛዜ ስለሚፈፀምበት ፎርም
ሚች በኑዛዜ ሊያከናውናቸው ስለሚችላቸው ተግባራት
ኑዛዜን ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚችል ማስረጃ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ መሠረት የሚች ኑዛዜ ስለሚያስከትለው ውጤትና ስለኑዛዜ ተፈጻሚነት ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው።

5.1. የኑዛዜ ፅንሰ ኃሳብ እድገትና ትርጉም፣

በምዕራፍ ሶሥት መግቢያ ላይ እንደተገለፀው ሚች በሕይወት ዘመኑ ኑዛዜ ትቶ ያለፈ እንደሆነ፣ የሚች የውርስ ሥርዓት በተወው ኑዛዜ መሠረት ይፈፀማል። በሥነ ሕግ ሊቃውንት በሰፊው ሥምምነት ላይ የተደረሰው በጥንታዊ ማሕበረሰብ ውስጥ የሚችን ንብረት ውርስ እንዴት ይፈፀም የሚለው ጭብጥ እንደመነጋገሪያ ሆኖ የመጣው ከግል ንብረት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ መልኩ ነው።በመጀመሪያው የሕብረተሰብ የእድገት ታሪክ ውስጥ የሚች ኑዛዜ በውርሱ ሥርዓት አፈጻጸም ላይ ይህ ነው የሚባል ቦታ አልነበረውም። ምክንያቱም ሚች ወደ ኋላ ጥሎት የሄደው ንብረት በሕይወት ላሉት ዘመዶቹ የሚከፋፈለው ለሚች ካላቸው የሥጋ ዝምድና ትሥሥር መሠረት በማድረግ ነው። ሆኖም የሥጋ ዝምድናን መሠረት በማድረግ፣ ይፈፀም የነበረው የውርስ ሥርዓት የሚችን ፍላጐት የማያሟላ አንድ አንኂዜም የሚቃረን በመሆኑ የሚች ውርስ በኑዛዜው መሠረት የሚፈፀምበት ሥርዓት እያደገ እንደመጣ ሙሁራኑ ይስማማሉ።

ይህም በመሆኑ በከፊል የኑዛዜ ፎርምና ይዘት ባለው የሚች ቃል መሠረት፣ የሚች የውርስ ንብረት የማከፋፈሉ ሥራ በጥንት ግብፃዊያን ከክርስቶስ ልደት በፊት 2900-2750 ይፈፀም እንደነበርና ከክርስቶስ ልደት በፊት 2250-2100 ሥራ ላይ ውሎ በነበረው (Hammurabicode) ውስጥም ሚች በኑዛዜ ልጆቹን ከውርስ የሚነቅልበት ሥርዓት ተደንግጐ ይገኝ እንደነበር፣ ስለ ውርስ ሕግ ፅንሰ ኃሣብ ታሪካዊ እድገት የተጻፉ ጽሑፎችን በማንበብ ለመረዳት ይቻላል::ከሁሉም በላይ፣ የሚች ውርስ ሥርዓት በኑዛዜው መሠረት የሚፈፀምበት ሁኔታ በተሚላ መልኩ ጸክርስቶስ ልደት በፊት 450 አካባቢ በወጣው የጥንታዊ ሮማዊያን የውርስ ሕግ ውስጥ በሰፊው ተካትቶና መሠረታዊ የሆነ ትንታናና ትምህርት እየተሰጠበት በተግባር ላይ እንዳዋለና የጥንት ሮማዊያን በሥነ ሕግ ደረጃ ያሣዩት እድገትና በመስኩ ይሰጡት የነበረው ጥልቀት ያለው ትምህርት ሌሎች አገሮችም በተለያየ መንገድ የተስፋፉ እንደሆነ በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያረጋግጣሉ::

በመሆኑም በሚች የኑዛዜ ቃል መሠረት የሚች የውርስ ሥርዓት እንዲፈፀም የማድረጉን ተግባር በጥንት ዘመን ይኖሩ የነበሩ የተለያዩ የማሕበረሰብ ክፍሎች ተግባራዊ ለማድረግና ይህንኑ የሚሸፍን የሕግ ማዕቀፍ በመደንገግ ሰፊ እንቅስቃሴ ያደረጉበት ሲሆን፣ በተሚላ ሁኔታና በዘመናዊ መልክ ግን የጥንት ሮማውያን በሕጋቸው አካትተው ተግባራዊ ማድረግ እንደጀመሩና ኃሣቡ ወደ ሌላው የምዕራብ አውሮፖ ሐገራትና ወደ ሌላው ክፍለዓለም እየተስፋፉ እንደሄደ በበርካታ ፅሑፎች ውስጥ ተጠቃልሎ ይገኛል::በሕብረተሰብ ታሪክ የሚች የኑዛዜ ቃል፣ እሱ ከሞተ በኋላ ሕጋዊ ውጤት መስጠትና የውርስ ሥርዓቱም በኑዛዜ ቃሉ መሠረት ማስፈፀም መቼ እንደተጀመረ ከገለፅኩ:: ኑዛዜ ማለት ምን ማለት ነው? ለመሆኑ ኑዛዜ የሚለው ቃል፣ በተለያዩ ሐገራት ሕግጋት ውስጥ ምን ዓይነት ትርጉም ተሰጥቶታል? የኢትዮጵያ የውርስ ሕግስ ለኑዛዜ የሰጠው ትርጉም አለውወይ? የሚሉትን ነጥቦች በአጭሩ መግለፅ ፅንሰ ኃሣቡን ለመረዳት የሚጠቅም ሆኖ ይሆናል::

በአጠቃላይ በሥነ ሕግ ዘርፍ (Jurispudence) ውስጥ፣ ስለ ኑዛዜ ወጥ እና ግልፅ የሆነ አንድ ትርጉም ማግኘት አይቻልም:: ለምሣሌ በወንጀል ሕግ ውስጥ የሚሞት ሰው የተናገረው ንግግር/ኑዛዜ/ የሚኖረው ውጤትና የሚሰጠው ትርጉም በፍትሐብሔር የሕግ ክፍል ለኑዛዜ በምንሰጠው ትርጉም የተለየ ነው:: በፍትሐብሔር የሕግ ክፍልም ውስጥ ቢሆን ለኑዛዜ (will) ሁሉም ሐገራት የተስማሙበት አንድ ወጥና ግልፅ ትርጉም ማግኘት አስቸጋሪ፣ ነው:: በመሆኑም የተለያዩ ሐገራት፣ ኑዛዜን በተለያየ መንገድ

ትርጉም ሰጥተው እናገኛለን። በመሆኑም፣ ለሠልጣኞች በኑዛዜ ትርጉም ዙሪያ ያሉትን ልዩነቶች ለማጣየት በምሣሌነት የሁለት አገር ሕጐች የሰጡትን ትርጉም ማስቀመጡ አስፈላጊ ነው።

በመጀመሪያ ኑዛዜ (will) በእንግሊዝ ሕግ ውስጥ የሰጠውን ትርጉም ስንመለከት " will is adeclaration of intention in a prescribed form, if any of a person making it which and untile such time revocable" በማለት ኑዛዜ፣ በሕጉ በሚያስቀምጠው ፎርም መሠረት አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ሊፈፀሙ ስለሚችሉ ተግባራት የሚሰጠው የሐሣብ መግለጫ እንደሆነና በሕይወት እስካለ ድረስ ሊሽረው የሚችለው የሕግ ተግባር መሆኑን ያስቀምጣል። በሁለተኛ ደረጃ አዲሱን የሞሮኮ የውርስ ሕግ ኑዛዜን በሚከተለው አኳኋን ተርጉሞታል። " will is an act by which the author there of creats one third of his property aright which becomes exigible at death" በዘመናዊ መንገድ፣ ፀድቆ በሥራ ላይ የዋለው የሞሮኮ ሕግ ኑዛዜ አንድ ሰው ከንብረቱ አንድ ሦስተኛውን ከሞተ በኋላ ለኑዛዜ ተጠቃሚው ለማስተላለፍ የሚፈፅመው የሕግ ተግባር እንደሆነ ያስቀምጣል። ከዚህም ትርጉም ሚች ከሞተ በኋላ ከአንድ ሶስተኛው በላይ ንብረቱን ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ የሚፈፅመው ተግባር እንደ ኑዛዜ እንደማይቆጠርና በኑዛዜ ትርጉም ውስጥ የማይሸፈን መሆኑን ለመረዳት ይቻላል።

የእንግሊዝ ሕግ ሚች በኑዛዜ በሚያስተላልፈው የንብረት መጠን ስንት ፐርሰንት እንደሚሆን ገደብ ያላስቀመጠ ሲሆን፣ የሞሮኮ ሕግ ደግሞ የሚች ተግባር ኑዛዜ ነው ተብሎ የሚያዘው ካለው ንብረት አንድ ሶስተኛውን ብቻ የሚመለከት እንደሆነ ብቻ መሆኑን ያስቀምጣል። ከላይ በምሣሌነት በሁለቱ ሐገራት ሕጐች መካከል ለኑዛዜ የተሰጠውትርጉም የተለያየ የመሆኑን ያህል፣ የሌሎች ሐገራት ሕግጋትንም ብንመረምር ለኑዛዜ የሚሰጡት ትርጉም እንደየሐገሪቱ የፖለቲካ የማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊና ኃይማኖታዊና ማሕበረሰባዊ እሴት መሠረት የተለያየና ወጥነት የሌለው ሆኖ እናገኘዋለን። የሌሎች ሐገራት ሕግጋት ውስጥ ለኑዛዜ የተሰጠው ትርጉም የተለያየ ይዘት ያለ መሆኑን ግንዛቤ ከያዝን በኋላ ለመሆኑ የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ "ለኑዛዜ" የሰጠው ትርጉም አለወይ? የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ፣ የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ " ለኑዛዜ " የሰጠው ትርጉም የለም። ይልቁንም በኑዛዜ መሠረት ስለሚፈፀም ውርስ ሲደነግግ የሚጀምረው ለኑዛዜ ትርጉም በመስጠት ሣይሆን የኑዛዜ ዋጋ መኖር ሁኔታዎችን በመዘርዘርና በመደንገግ ነው።

ይኸ በሕግ አቀራረፅ ሥርዓት የሚደገፍ አይደለም። ምክንያቱም ኑዛዜ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ፅንሰ-ሃሳቡን የሚያስጨብጥ ድንጋጌ ሣይኖር፣ በቀጥታ ኑዛዜ በሕግ ፊት ውጤት እንዲኖረው ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ተግባራትና ሊሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች ዝርዝር ድንጋጌዎችን ማስቀመጡ፣ ፅንሰ ሃሣቡን ለመተንተንና ለመገንዘብ አስቸጋሪ ስለሚሆን በዚህ በኩል የውርስ ሕጋችን ክፍተትና ጉድለት ያለበት ሆኖ ይታያል።ሆኖም የተለያዩ ሐገራት ስለኑዛዜ በውርስ ሕጋቸው ውስጥ የተለያየ ትርጉም የሰጡትና የኢትዮጵያ የውርስ ሕግም " ኑዛዜ " የሚለውን ፅንሰ ሃሣብ ትርጉም ሣይሰጠው ያለፈው ሲሆንም ኑዛዜ እንደ አንድ የሕግ ተግባር (lgal transalation) በሚወሰድበት ጊዜ በሁሉም አገሮች የሕግ ሥርዓት ውስጥ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ ዕውቅና የተሰጣቸውና በዋቢነት ሊጠቀሱ የሚችሉ *መሠረታዊ ባሕሪያት* (Basic features) አሉት። በመሆኑም በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ውስጥ ኑዛዜ ዋጋ የሚኖረው በምን ዓይነት መንገድና ምንምን ሁኔታዎችን አሟልቶ ሲገኝ ነው? የሚሉትን ነጥቦች ከማየታችን በፊት በሥነ ሕግ ጥናትና ምርምር ውስጥ፣ የኑዛዜ *መሠረታዊ ባሕሪያት* ናቸው ተብለው የተቀመጡትን ፅንሰ-ሃሣቦች በቅድሚያ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

5.2. **የኑዛኔ *መሠረታዊ ባሕሪያት***(Basic feaures of will)

በክፍል አንድ ለመግለፅ እንደተሞከረው የተለያዩ ሐገራት በውርስ ሕጋቸው ውስጥ ለኑዛዜ የተለያየ ትርጉም ሰጥተው የምናገኛቸው ቢሆንም የሁሉም አገሮች ሕግጋትና የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ኑዛዜ የሚከተሉት *መሠረታዊ ባሕሪያት* እንዳለው ያስቀምጣሉ።

ሀ/ ኑዛዜ በየትኛውም ሐገር ሕግጋት ውስጥ የሚያያዘው ከአንድ ሰው ሞት ጋር ነው። ማንም ቢሆን ስለሞት ክስተት በሕሊናው ሣያስብ ስለ ኑዛዜ መጻፍም ሆነ ለመናገር አይችልም። ሟች ከመሞቱ በፊት የኑዛዜ ቃል የሚናገረው ወይም የሚፅፈው አንድ ቀን ባላሰብኩበት ሁኔታ በድንገት ልሞት እችላለሁ የሚል ሥጋት ስለሚያድርበት የመሆኑ ሁኔታ የኑዛዜ *መሠረታዊ ባህሪ* ነው።

ለ/ ኑዛዜ ተራ የቃላት *መግለጫ* ነው። ኑዛዜ አንድ ሰው ሲሞት መፈፀም ስለሚገባቸው ነገሮች በሕይወት እያለ የሚሰጠው የተስፋ ቃል ነው። በመሆኑም ተናዘዝ፡ በሕይወት እስካለ ድረስ በሕግ በኩል የሚያስከትለው ምንም ውጤት የለም።

በመሆኑም ኑዛዜ የአንድ ሰው ተራ የኃላፊ መግለጫ መሆኑ የሚያስከትላቸው በርካታ ተጨባጭነት ያላቸው ጽንሰ ሀሳቦች አሉ።

የመጀመሪያው አንድ ሰው ኑዛዜ መፈፀሙ ንብረቱን፣ በመጠቀም፣ በመሸጥ፣ በመለወጥ እንደዚሁም ንብረቱን ለማውደም ያለውን የባለቤትነት መብት በምንም ዓይነት መልኩ የሚያሣጣ አይደለም። ምንም እንኳን አንድ ሰው ጠቅላላውን ንብረቴን ወይም ከንብረቱ አንዱ ክፍል እኔ ስሞት ለእገሌ ይሰጥልኝ ብሎ የተናዘዘና ኑዛዜውን ሥልጣን ላለው አካል ያስመዘገበ ቢሆንም ኑዛዜ ያደረገበትን ንብረት ዋጋ በመቀበል ወይም ዋጋ ሣይቀበል በነጻ ለሌላ ሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ ሙሉ መብት ይኖረዋል። በሁለተኛ ደረጃ ኑዛዜ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ መፈፀም ስለሚገባቸው ተግባራት ወይም ለኑዛዜ ተጠቃሚው መተላለፍ ስለሚገባቸው ንብረቶች የሚሰጠው የተስፋ ቃል በመሆኑ ውጤት ሊኖረው የሚችለው፣ ኑዛዜውን የተወው ሰው ከሞተ በኋላ ነው። በመሆኑም የኑዛዜ ተጠቃሚው የሚችን ኑዛዜ መሠረት በማድረግ ከሚች መሞት በፊት ምንም ዓይነት ጥያቄ እንዲያቀርቡ መብት የላቸውም። የኑዛዜ ተጠቃሚዎች ሚች በሕይወት እስካለ ድረስ በሚች ንብረት ላይ ማናቸውንም የይገባኛል ወይም ሌላ ዓይነት ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም። ከዚህ በተጨማሪ በኑዛዜ ተጠቃሚና የሚች ወራሽ ለመሆን ሚችን ለመውረስ ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል ይኸም ማለት ሚች ሲሞትና የሚች ውርስ ኪፈት በሕይወት መኖር አለባቸው። በሌላ በኩል ሚች የፈፀመው የሕግ ተግባር ውጤት የሚያመጣው ሚች በሕይወት እያለ የሚሆን ከሆነ የዚህ ዓይነት ተግባራት ኑዛዜ በሚለው ፅንሰ ኃላፊ ሊሸፈኑ የማይችሉ መሆናቸው ነው።

በሦስተኛ ደረጃ ኑዛዜ ተራ የኃላፊ መግለጫ ተግባር በመሆኑ ሚች በኑዛዜ ይተላለፉ ያላቸው ንብረቶች ለሚች ዕዳ መክፈያነት የሚያዙና የሚሸጡ ይሆናሉ። ይኸም ማለት ተናዛዡ በሕይወት ዘመኑ ሊከፍለው የሚገባው ዕዳ ካለበት፣ የኑዛዜ ተጠቃሚዎቹ የሚችን አበዳሪዎች ንብረቱን በኑዛዜ አግኝተነዋልና ሊወሰዱ ወይም ሊያሸጡብን አይገባም በማለት ለመሞገት የሚያስችል ሕጋዊ መብት አይፈጥርላቸውም። በተቃራኒው የኑዛዜ ተጠቃሚዎቹ ከሚች ውርስ እና ንብረት ገንዘብ ሊያገኙ የሚችሉት የሚች ዕዳ ከተከፈለ በኋላ የሚተርፍ ከሆነ ነው።

ሐ. ኑዛዜ በማናቸውም ጊዜ ተናዛዡ ሊሽረው የሚችል መሆኑ ነው። ኑዛዜ በኑዛዜ አድራጊው በማናቸው ጊዜ የሚሽረው ተግባር የመሆኑ ባሕሪ የሚመነጨው ኑዛዜ ተናዛዥ በሕይወት እስካለ ድረስ የተናዛዡ ረቂቅ የምኞትና የኃላፊ መግለጫ በመሆኑ

ነው፡፡ በመሆኑም ኑዛዜ ያደረገው ሰው በማናቸውም ጊዜ ኑዛዜውን የመቀየር፣ የመሰረዝ ወይም ማጥፋትና የመሻር መብት አለው፡፡

መ. ኑዛዜ ከተፈፀመ በኋላ በተፈራ ንብረት ላይ ውጤት ያለው መሆኑ ነው፡፡
(will is ambulatory) ባሚለው ባህሪ ይኸም ማለት ለምሣሌ አቶ ሽመልስ የጠቅላላ የንብረቴ ወራሽ ወንድሜ ሳምሶን ነው ብሎ ታህሣሥ 1990 ዓ.ም በጽሑፍ ሲናዘዝና ኑዛዜውን ሲ.ናዘዝ የነበረው ንብረት ብር 500000 (አምሥት መቶ ሺ) የሚያወጣ ቢሆን አቶ ሽመልስ ኑዛዜውን ከፈፀመ ከአራት ዓመት በኋላ ጥር 1995 በሞት ሲለይ የነበረው ንብረት ግምቱ ብር 1000 000፣ (አንድ ሚሊየን ብር) ቢሆን፣ አቶ ሽመልስ በታህሣሥ ወር 1990 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ኑዛዜው ከተደረገ በኋላ በተፈራው ንብረት ላይ ጭምር ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ሳምሶን ከአቶ ሽመልስ የሚወርሰው ኑዛዜ ሲያደርጉ የነበረውን የብር 500 000 (አምሥት መቶ ሺ) ንብረት ብቻ ሣይሆን ከዚያ በኋላ የተገኘውንም ብር 500 000 (አምሥት መቶ ሺ ብር) ጨምሮ ነው፡፡ በመሆኑም ተናዛዡ በግልፅ በኑዛዜው ውስጥ እስካላስቀመጠው ድረስ ኑዛዜ ከተፈፀመ በኋላ በተገኙ ንብረቶች ላይ ጭምር ተፈጻሚነት ያለው ሐ ጽመበጭለታተጸረየ ጽፈፈጵቸተ? ያለው የሕግ ተግባር ነው፡፡

ሠ. ኑዛዜው በይዘቱና ማዕቀፉ ንብረትን ከማስተላለፍ ተግባር ጋር ብቻ የተያያዘ አለመሆኑ ነው፡፡ አንድ ሰው አካለመጠን ስላላደረሱ ልጆቹ፣ በውርሱ መካፈል ስለማይገባው ልጁ ወይም ወራሹ ስለ ቀብሩ ሥርዓት አፈጻጸም፣ ሲሞት የውርስ አጣሪና አስፈጻሚ ሆኖ ማገልገል ስለሚገባው ሰው በህይወት ዘመኑ ስላለበት ዕዳ፣ ከሌላ ሰው ላይ ስላለው ገንዘብ እና ስለሌሎች ጉዳዬች ኑዛዜ የማድረግ መብት አለው፡፡ ሕጉም የኑዛዜ ቃሉ፣ በሕጉ መሚላት ያለባቸውን ሁኔታዎች እስካሚላ ድረስ ሕጋዊ ውጤት ይሰጠዋል፡፡

ረ. ኑዛዜ የተናዛዡ በግሉ ብቻ ሊፈፅመው የሚገባው ተግባር የመሆኑ ሁኔታ ነው፡፡ ማንም ሰው ስለ እሱ ሆኖ ኑዛዜ እንዲያደርግለት የእንደራሴነት ወይም የወኪልነት ሥልጣን ለመስጠት አይችልም፡፡ የተለያዩ ተግባራትን በእንደራሴ በመወከል መፈፀም እንደሚቻል፣ የብዙ ሐገር ሕግጋት የሚፈቅዱ ቢሆንም፣ ኑዛዜን በተመለከተ ግን ተናዛዡ በግሉና ራሱ ብቻ ሊፈፅመው የሚገባው ተግባርና በወኪል ወይም በእንደራሴ በኩል ከማይፈፀሙት ተግባራት አንዱ መሆኑ የኑዛዜ መሠረታዊ ባሕሪና ልዩ መገለጫ ነው፡፡

በመጨረሻም ሚች ንብረት ለኑዛዜ ተጠቃሚው እንዲተላለፍለት የሚናዘዝ ከሆነ ከኑዛዜ ተጠቃሚው በዓይነትም፣ በገንዘብም ሆነ በአገልግሎት መልክ የሚከፈለው ምንም ዓይነት ክፍያ መኖር የለበትም። በመሆኑም ኑዛዜ ዋጋ የማይከፈልበትና በነጻ የሚደረግ ሚች ከሞተ በኋላ የሚፈፀም ስጦታ መሆኑ አንደኛው ባህሪው ንወዉዉ ከላይ ያነሳናቸው መሠረታዊ ነጥቦች ኑዛዜ ምን እንደሆነ መቼ ሕጋዊ ውጤት እንደሚያስከትልና የሚያስገነዝቡና ስለ ኑዛዜ በፅንሰ ኃሣብ ደረጃ ስንነጋገር ሊነሱ የሚገቡ መሠረታዊ ባህሪያትና መግለጫዎች ናቸው። በመሆኑም ሰልጣኞች የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ውስጥ ስለ ኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እነዚህን መሠረታዊ ባህሪያት የሚያቅፉና የሚቀበሉ መሆን አለመሆናቸውን እንደዚሁም የትኛው መሠረታዊ ባህሪ በየትኛው የሕግ ድንጋጌ ውስጥ ተከታትቶ እንደሚገኝ፣ በዝርዝር በማየት፣ የሕጉን ድንጋጌዎች ከላይ ከተቀመጡት ነጥቦች ጋር በማዛመድ በአፈጻጸም እና በአተረጓጐም ወቅት ምን መሆን እንዳለበት የበኩላቸውን ግንዛቤ ማዳበር ይጠበቅባቸዋል። እነዚህን ባህሪያት የሚያንፀባርቁ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች ለይተው ያውጡ።

5.3 የኑዛዜ ዋጋ መኖር ሁኔታዎች

በምዕራፉ የመጀመሪያ ክፍል እንደተገለፀው፣ የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ኑዛዜ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሰጠው ትርጉም ባይኖርም አንድ ኑዛዜ ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ማሟላት የሚገባቸው ምን እንደሆኑ በዝርዝር የሚያስቀምጡ የሕግ ድንጋጌዎችን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 857 እስከ 908 አስቀምጦ እናገኘዋለን። ሆኖም እነዚህ በሕጉ ውስጥ የተቀመጡትን የኑዛዜ ዋጋ መኖር ሁኔታዎች ለመገንዘብና የሕጉን ድንጋጌዎችን ይዘት ለመረዳት ከሕጉ ድንጋጌዎች በተጨማሪ፣ በተለያዩ ሐገራት ውስጥ አንድ ኑዛዜ ዋጋ እንዲኖረው እንዲያሟላ የሚጠበቅበት ሁኔታዎች ምንድን ናቸው የሚለውን ነጥብ ማየቱ ጠቃሚ ነው። ኑዛዜ ሁለት መሠረታዊ ተዋፅኦዎች (Elements) አሉት። የመጀመሪያው በዚህ ምዕራፍ በሁለተኛ ክፍል እንዳየነው የተናዛዡ ኑዛዜ ለመፈጸም ኃሳብ ያለው መሆኑን፣ የተናዘዡ ኑዛዜውን ሲፈፅም የነበረውን የአእምሮ ሁኔታ (The intention to make a will) ሁለተኛው ደግሞ ተናዛዡ ኑዛዜውን የሚገልፀው በሕጉ በተቀመጠው ፎርምና ሥርዓት መሆን ያለበት መሆኑ ነው።

በመሆኑም አንድ ሠነድ የሚች የኑዛዜ ቃል ነው ተብሎ በማስረጃነት ለመቅረብ ተናዛዡ ሙሉ እና ነፃ ኃሣብ (in herent or_ internsic element) እና ኑዛዜው በሕጉ በተቀመጠው ፎርም የተፈፀመ መሆኑ Extrinsic element የያዘ መሆን አለበት::የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ፣ ሁለቱን የኑዛዜ element ከላይ ባስቀመጥነው መንገድ የማይገልጻቸው ቢሆንም የኑዛዜ ዋጋ መኖር ሁኔታዎች የሚላቸውን ነገሮች በሶስት ክፍሎች ከፋፍሎ አስቀምጧቸው እናገኛለን:: የመጀመሪያው ክፍል ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አስፈላጊ የሆኑ የሥረ ነገር ሁኔታዎች በፍትሐብሔር ሕግ 857 እስከ 879 በሁለተኛው ክፍል የኑዛዜዎች ፎርምና ማስረጃ 880_898 በሶስተኛው ክፍል ደግሞ ስለኑዛዜዎች መሻርና ውድቅ መሆን ከ898-908 ደንግጌ እናገኝዋለን::በመሆኑም በሕጉ ድንጋጌ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት፣ ከላይ ያነሳናቸው ኃሣቦች በሕጋችን የተካተቱ መሆን አለመሆናቸውን በማገናዘብ ቄምር በሕጋችን ኑዛዜ ዋጋ የሚኖረው ምን ምን ሁኔታዎችን ሲያሟላ ነው የሚለውን ነጥብ በማስከተል እናያለን::

5.3.1 ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አስፈላጊ የሆኑ የስረ ነገር ሁኔታዎች

በውርስ ሕጋችን ውስጥ ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አስፈላጊ የሆኑ የሥረ ነገር ሁኔታዎች /Essential Conditions of Will/ በሚለው ርእስ ስር የተደነገጉት ድንጋጌዎች አንድ ኑዛዜ ኑዛዜ ነው ተብሎ በሕግ ፊት ውጤት ለመስጠት ምን ምን የሥረ ነገር ሁኔታዎችን ማሟላት እንዳለበት የሚደነግጉ ናቸው:: ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አስፈላጊ የሆኑ የሥረ ነገር ሁኔታዎች ተብለው በሕጉ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች በሁለት ከፍሎ ማየትና መተንተን ይቻላል::የመጀመሪያዎቹ ኑዛዜውን ሁለንተናዊ ወይም ተፈጥሯዊ አስፈላጊ ነገር /Inherent or intrinsic elements of will/ የሚባሉትን የሚደነግጉ ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ የኑዛዜውን ይዘት ላይ የሚያተኩሩና ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ መሆን ወይም አለመሆኑን የሚቆጣጠሩ ናቸው:: ከላይ ክፍል ውስጥ በግልጽ እንደተመለከተው የኑዛዜ ሁለንተናዊ ወይም ተፈጥሯዊ ነገር / inherent Elements of will/ የሚባለው ተናዛዡ ኑዛዜውን በሚፈጽምበት ሰዓት የነበረው የአእምሮ ሁኔታ ወይም ኑዛዜ የማድረግ ሀሣብ የነበረው መሆኑ /Animus testandi/ የምንለው ነው:: ሆ ም አጸራካሪው ፦ ቭ ስለ ትዛዜ ክርክር ባሚትሣው ትዛዜ አታራ ፈው ጸሞተ በኋላ ስለሆት ትዛዜ አታራ ፈው በሙሉ ሀሣብ ምላ ፦ፔ ትዛዜውት ቨተረ ስለመሆት ትቲፔ ር ኀ ቾ መሆት ቭናልል ባሚለው ትኅ ብ ትው:: ቭህትትም ለመረ ፔ ባሚጸተሉፔ ሁት ምኖ ጸ ምፔ ውስኀ ቭ ባሉ::

ሀ/ ተናዛዡ ራሱ በሙሉ ሀሣብ ኑዛዜ የፈጸመ መሆኑ፣

በእርግጥ ሟች ኑዛዜውን ያደረገው የተሟላና ነጻ የሆነ ኑዛዜ የማድረግ ሀሣብ /With full intent to make a will ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነገር በአርግጠኝነትና በአጭሩ ለማግኘት እጅግ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ በውርስ ሕግ በተለይም የሟችን ኑዛዜ መሠረት በማድረግ በሚፈፀም የውርስ ስርዓት ላይ ጥናት ያደረጉ ሙሁራን ይገልጻሉ::ሆኖም አንድ ተናዛዥ ኑዛዜውን በሚፈጽምበት ሠዓት ኑዛዜ የመፈፀም ሀሣብ/Animus testandi/ የነበረው መሆኑን ለመለካት ወይም ለመገመት ያስችላሉ ያሏቸውን መሠረታዊ ሁኔታዎች አስቀምጠዋል::

በእነርሱ አገላለጽ አንድ ተናዛዥ ኑዛዜውን በሚያደርግበት ሠዓት ነጻና የተሟላ ኑዛዜ የማድረግ ሀሣብና ፍላጐት አለው የሚባለው

ኑዛዜውን በሚፈጽምበት ጊዜ እየፈፀመው ያለው ተግባር ኑዛዜ የመፈፀም ተግባር መሆኑን የተረዳ እንደሆነ

ተናዛዡ ኑዛዜ በሚፈጽምበት ጊዜ ማናቸውም አይነት የአእምሮ መቀወስ ወይም መዛባት የሌለበት እንደሆነ

ተናዛዡ ኑዛዜውን ሲፈጽም ምንም አይነት ተጽእኖ የሚያሣድርበት ሁኔታና የሚያስገድደው የሀይል ድርጊት የሌለ እንደሆነ

ተናዛዡ የሚፈጽመውን ኑዛዜ ይዘት እውቀቱ ኖሮት እና ኑዛዜውን የፈፀመ አንደሆነ ነው::

ለኑዛዜው ዋጋ መኖር አንዱ የተናዛዥ ኑዛዜውን ሲፈጽም ኑዛዜ የመፈፀም ሀሣብ /Animus testandi/ የነበረው መሆኑ እንደ አንድ መሠረታዊ ሁኔታ የሚቀመጠው ያለ ምክንያት አይደለም:: ምክንያቱም ኑዛዜ በሕግ ፊት ውጤት የሚኖረውና እንደ መብት ማግኛ ሰነድ ሆኖ በማስረጃነት የሚቀርበው፣ የክርክርና የውዝግብ መነሻም የሚሆነው ሟች ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በኋላ ነው:: ይህም በመሆኑ ሟች ሰነዱን ያዘጋጀው ለኑዛዜ ተጠቃሚው ኑዛዜ ለማድረግ በነጻ ሀሣቡና ፍላጐቱ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ሟችን እራሱን በመጠየቅ ለማረጋገጥ ፈጽሞ የማይችል ነው::

ይኸም በመሆኑ ከውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ውስጥ ኑዛዜን የሚመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎች መስፈርቶችንና ሁኔታዎችን ይጠብቃሉ:: የኢትየጵያ የውርስ ሕግም የኑዛዜ ዋጋ መኖር የስረ ነገር ሁኔታዎች / Essemtial Conditions of will/ በማለት ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች በተቻለ መጠን ሟች ትቶት የሄደው ኑዛዜ የእሱን ሀሣብና ፍላጐት የሚያንፀባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዱ መስፈርቶችን ያስቀምጣል::

ከነዚህ ሁኔታዎች የመጀመሪያው ኑዛዜ የሚቹ ጥብቅ የሆነ የግል ሥራ መሆኑን መደንገጉ ነው። ይኸ የሕግ ድንጋጌ ሚች ኑዛዜ የማድረግ ሀሣብና ፍላጐት ኖሮት እንደዚሁም የኑዛዜውን ይዘት በመረዳት በጥቅሉ /Animus testandi/ በተሚላበት ሁኔታ ኑዛዜ ማድረግ ያለበት እሱ ራሱ ብቻ መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል። ሕጉ የሚች ሀሣብ በሌሎች ሰዎች ማለትም በወኪሎቹ በኩል በኑዛዜ ላይ መግለጽ እንደማይገባው በመከልከል ኑዛዜውን የሚች የግል ሥራና የራሱ የሀሣብ መግለጫ መሆን እንዳለበት በግልጽ ያስቀምጣል። አንድ ሰው ለሌላ ሰው በስሙ ኑዛዜ እንዲያደርግ እንዲለወጥ ወይም እንዲሽር ስልጣን ሊሰጠው እንደማይችልና አንድ ሰው ሌላ ሶስተኛ ወገን /ለሌላ ሰው / ወራሹን እንዴት እንደሚወስንና ውርሱ ለማን መተላለፍ እንዳለበት እንዲፈፀም ሊያደርግ እንደማይችል የውርስ ህግ ይደነግጋል።

ኑዛዜን በተመለከተ ሚች ያለማንም ሶስተኛ ወገን ተሣታፊነት ጣልቃ ገብነትም ሆነ ያለ ወኪል እሱ ራሱ ብቻ በቀጥታ ሀሣቡን የሚገልጽበት የሕግ ተግባር እንደሆነና ይኸም ለኑዛዜው ዋጋ መኖር እንደ አንድ የሥረ ነገር ሁኔታ የተቀመጠ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 857 ድንጋጌዎች በማንበብ ለመረዳት ይቻላል።ከዚህ በተጨማሪ ሕጋችን ሚች ኑዛዜ በሚያደርግበት ጊዜ ብቻውን በተለየና ራሱን በቻለ ሰነድ መፈፀም እንዳለበትና ብዙ ሰዎች በአንድ ሰነድ ውስጥ የተናዘዙ እንደሆነ ኑዛዜው እንደሚፈርስና ሕጋዊ ውጤት እንደማይኖረው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 858 ይደነግጋል። ይኸም የኑዛዜውን ፎርም ለመጠበቅ ተብሎ የገባ የሕግ ድንጋጌ አይመስልም። በዋነኛነት ኑዛዜው የሚች የግል ሥራና የሀሣብ መግለጫ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ተናዛዡን ኑዛዜ የመፈፀም ሀሣብ /Animus testandi/ ለማረጋገጥና ሚች በሌላ ማናቸውም ግፊት ኑዛዜ ቢፈጽም ውጤት የማይኖረው መሆኑን በሕጋችን የሚደነግገው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 859 ነው። በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረት በተለያየ ምክንያት ሚች ኑዛዜ ለማድረግ ለመለወጥ ወይም ለመሻር የገባው ስምምነት ወይም የሰጠው የተስፋ ቃል ቢኖር ሕጉ ይህንን ኑዛዜ ለማድረግ ለመለወጥ ወይም ለመሻር የተደረገ ስምምነት ወይም የተሰጠ የተስፋ ቃል ውጤት እንደማይኖረው በመደንገግ ከራሱ ፈቃድና ሀሣብ ውጭ አንድ ሰው ኑዛዜ እንዲያደርግ ባሚቨስ ታቱ ውሎች ወይም የተስፋ ቃሎች ሕጋዊ ተፈጻሚነት ሊኖራቸው እንደማይገባ ያስቀምጣል።

ለ/ የተናዛዡ ኑዛዜ የመፈጸም ችሎታ

በሁለተኛ ደረጃ የኢትዮጵያ ሕግ የተናዛዡን ኑዛዜ የመፈፀም ሀሣብ/Animus testandi/**እያለው ኑዘዜ የፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥና ለኑዛዜው ዋጋ ለመስጠት ወይም ላለመስጠት እንደ መስፈርት የያዘው የተናዛዡ ኑዛዜ የመፈፀም ችሎታ** / Capacity to make a will/ **ነው፡፡ የተናዛዡ ኑዛዜ የመፈፀም ችሎታ የሚመዘነው የተናዛዡ የሚፈጽመው ተግባር ኑዛዜ መሆኑንና የሚፈጽመውን ኑዛዜ ይዘት በአግባቡ የሚረዳ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በመመዘን ነው፡፡**

እዚህ ላይ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ነገር አንድ ሰው በሕግ ችሎታ ያለው መሆን አለመሆኑ ጉዳይ ኑዛዜ ለመፈፀም ካለው ችሎታ ጋር በቀጥታ የማይገናኝ መሆኑን ነው፡፡ በሕግ ችሎታ የሌላቸው ሰዎች ኑዛዜ ለመፈፀም ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል፡፡የአንድ ሰው ኑዛዜ የመፈፀም ችሎታ/ Capacity to make a will/ **የሚመዘነው ተናዛዡ የሚፈጽመው ተግባር ኑዛዜ መሆኑንና የሚፈጽመውን ኑዛዜ ይዘት በአግባቡ የሚረዳ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በመመዘን ነው፡፡ ከዚህ መሠረታዊ መርህ በመነሣት የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ስንመረምር፣**

ኑዛዜ ለመፈፀም የሚያስፈልገው እድሜ አስራ አምስት ዓመት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህም ማለት ማንኛውም አስራ አምስት ዓመት ያደረሰ ሰው ያለማንም ሰው አመራር ሰጭነትና ተቆጣጣሪነት በሕግ ፊት ውጤት ያለው ኑዛዜ ለመፈፀም እንደሚችልና ከአስራ አምስት ዓመት ሣይሆነው የፈፀመው ኑዛዜ ግን በሕግ በኩል ውጤት እንደማይኖረው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 308 **ለመረዳት ይቻላል፡፡**
በፍርድ የተከለከሉ ሰዎች በፍርድ ከመከልከላቸው በፊት ያደረጉት ኑዛዜ ውጤት የሚኖረው ሲሆን በፍርድ ክልከላ ከተደረገ በኋላ የሚያደርጉት ኑዛዜ ውጤት እንደማይኖረው የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 368 **ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በፍርድ መከልከል ኑዛዜ የመፈፀም ችሎታን እንደሚያሣጣ በሕጋችን የተመለከተ ሲሆን ሚች በፍርድ ከመከልከሉ በፊት ያደረገውን ኑዛዜ ዳኞች መርምረው በሙሉ ወይም በከፊል የሚያፈርሱበት ሁኔታ በሕጉ ተቀምጧል፡፡ሆኖም በሰዎች ሕግ ክፍል ውስጥ በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር** 368 **ድንጋጌዎችና የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች በሆኑት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር** 861 **እና** 862 **መካከል የመልእክት አለመጣጣምና የይዘት ልዩነት ያለ የሚመስል በመሆኑ ሰልጣኞች የሕጉቹን ድንጋጌዎች በማንበብ የበኩላቸውን ትርጉምና ትንታኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡**

የአእምሮ መጓደል፣ የአንድን ሰው ኑዛዜ የመፈፀም ችሎታ ለማጣጣት ምክንያት አይደለም። በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ መሠረት ኑዛዜውን ሲፈጽም እብደቱ በግልጽ የታወቀ ሰው ካልሆነ በስተቀር ሌሎች እብደታቸው በግልጽ ያልታወቀ ሰዎችና የሚፈጽሙት ኑዛዜ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል። ይህንንም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 863 ለመረዳት ይችላል።
በሕግ የተከለከለ ሰው ኑዛዜ የማድረግ ሙሉ ችሎታ አለው። በመሆኑም በሕግ የተከለከለ ሰው በሕግ ከመከልከሉ በፊትም ሆነ በኋላ የሚፈጽመው ኑዛዜ ሕጋዊ ውጤት እንደሚኖረው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 864 ይደነግጋል።

በአጠቃላይ ከላይ በተገለፀው መንገድ የኢትዮጵያ ሕግ ኑዛዜው ኑዛዜ የመፈፀም ችሎታ/ Capacity to make a will/ ያላቸው ሰዎች የተፈፀመ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በመመዘን፣ ኑዛዜው ዋጋ የሚያገኝበትን ወይም ዋጋ የሚያጣበትን ሁኔታዎች እንደ አንድ መሠረታዊ መስፈርት አስቀምጧቸው እናገኛለን።

ሐ/ ኑዛዜው በመገደድ ወይም በስህተት ወይም በመንፈስ መጫን ያልተደረገ መሆኑ፣

በሶስተኛ ደረጃ የኢትዮጵያ ሕግ ኑዛዜ የፈፀመው ሰው ኑዛዜውን በሚፈጸምበት ወቅት በነጻ ፈቃዱና የኑዛዜውን ይዘት በአግባቡ ተረድቶ መሆኑን እንደ አንድ ሁኔታ ያስቀምጣል። በመሆኑም ሟች ኑዛዜ ያደረገው በሀይል ተገድዶ ከሆነ ወይም በስህተት ምክንያት ፈጽሞ ከሆነ ኑዛዜው ሊፈርስ የሚችልባቸው የሕግ ሁኔታዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 867 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 877 ተመልክተዋል።ከዚህ በተጨማሪ ሟች በወቅቱ በደረሰበት የመንፈስ መጫን ምክንያት ኑዛዜ አድርጌ ከሆነ ዳኞች በመንፈስ መጫን ምክንያት የተደረገውን ኑዛዜ ለመቀነስ ወይም ለማሻር የሚችሉባቸው ሕጋዊ መሠረቶች እና የአፈጻጸም ስርዓቶቹ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 868 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 875 በግልጽ ተደንግገዋል።

እነዚህ ከላይ ያየናቸውና የኢትዮጵያ ሕግ የኑዛዜ ዋጋ መኖር የስረ ነገር ሁኔታዎች በማለት ያስቀመጣቸው " inherent elements of will " በማለት የሌሎች አገር የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ከሚያስቀምጧቸው ሁኔታዎች ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው።ሆኖም የኢትዮጵያ ሕግ '' የተናዛዡ ኑዛዜ የማድረግ ሀሣብ'' መኖር አለመኖሩን ብቻ ለኑዛዜ ዋጋ መኖር የሚያስፈልጉ የሥረ ነገር ሁኔታች እንዳልሆኑ በመገንዘብ ከተናዛዡ " Mental element" ወጣ ብሎ ተናዛዡ የፈፀመውን ኑዛዜ ይዘት በመመርመር ኑዛዜው ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው እንደሚገባ ወይም ዋጋ ሊኖረው እንደማይገባ ይደነግጋል።

ሚች በነፃ ፍቃዱ የፈፀመውን ኑዛዜ፣ የይዘት ችግር ካለበትና ከህዝብ ሞራልና ከመንግስት ፖሊስ ጋር የሠይጣጣም ከሆነ ህጋዊ ውጤት አይኖረውም።

መ. ኑዛዜው ሕጋዊ መሆኑ፣

በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ መሠረት አንድ ኑዛዜ በሚበቃ አኳኋን የኑዛዜውን ተጠቃሚ ወይም በኑዛዜው መሠረት መፈፀም ስለሚገባው ጉዳይ ካላመለከተ እንደዚሁም የኑዛዜ ቃሉ ሊፈፀም የማይችል ከሆነ ፈራሽ እንደሚሆን ተደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ አንድ የኑዛዜ ቃል ለሕግ ወይም ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ ከሆነ ሕጋዊ ውጤት እንደማይኖረው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 865 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 866 ድንጋጌዎችን በማንበብ ለመረዳት ይቻላል።

የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ የኑዛዜ ቃል ዋጋ መኖር አስፈላጊ የሆነ የሥረ ነገር ሁኔታዎች በማለት ያስቀመጣቸው ከላይ በዝርዝር ያየናቸው ሁኔታዎች ሲሆኑ በአከራካሪ ሁኔታዎች ኑዛዜ በማስረጃነት በሚቀርብበት ጊዜ እነዚህ የሥረ ነገር ሁኔታዎች መሟላታቸውን በመመዘን ኑዛዜው የሕግ ውጤት ያለው ስለመሆኑ ወይም ውጤት የሌለው ስለመሆኑ ውሣኔ መስጠት ይገባል።

5.3.2 በሕጉ የተቀመጠውን ፎርም አሟልቶ መገኘት

ሁለተኛው ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አስፈላጊ የሆነው ሁኔታ፣ ኑዛዜው በሕጉ የተደነገገውን ፎርም አሟልቶ የመገኘቱ ሁኔታ ነው። የብዙ አገሮች የውርስ ሕግ ኑዛዜ በምን ፎርም ሊፈፀም እንደሚባ የሚደነግጉ የሕግ ድንጋጌዎች ይዘው እናገኛለን። ምክንያቱም ኑዛዜው በሚፈፀምበት ጊዜ ተናዛዡ ኑዛዜ ለማድረግ የነበረውን ሀሣብ በቀላሉ ማረጋገጥ የማይቻልና ሚችንም አንድን ተግባር የፈፀመው ኑዛዜ ለማድረግ አስቦ መሆን አለመሆኑን ጠይቆ ለመረዳት የሚቻልበት አጋጣሚ ስለሌለ ሕግ አውጭው አንድ ተግባር ኑዛዜ መሆኑንና ኑዛዜው በሕግ ፊት ውጤት እንዲኖረው የሚፈልግ ኑዛዜ አድራጊ ኑዛዜውን በምን አይነት መንገድ ማከናወን እንደሚገባው ስለ ኑዛዜ ፎርም በሚደነግጉ ድንጋጌዎች ይወሰናል።

የኑዛዜ ፎርም ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አንደኛው አስፈላጊ ነገር ሲሆን ይኸም /Extrinsic/ or Formal elements of will በማለት ይጠቀሣል። የኑዛዜ ፎርም ከተናዛዡ ውጭ በሆነ በሌላ ሀይል ሕ አው ው ኑዛዜው በምን መልክ መዘጋጀት እንዳለበት በህግ የሚደነግግው ነው። ሌላው ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነገር በውርስ ሕግ ውስጥ ስለ ኑዛዜ ፎርም የሚደነግጉት የሕግ ድንጋጌዎች እጅግ በጣም ጥብቅና የአስገዳጅነት ባህሪ ያላቸው መሆኑን ነው። ይኸም ማለት ኑዛዜው በሕጉ የተመለከተውን ፎርም አሟልቶ ካልተገኘ በሕግ ፊት ውጤት አይኖረውም። በመሆኑም የኑዛዜ ፎርማቶችን የማሟላቱ ጉዳይ ኑዛዜ አድራጊው ሲፈልግ የሚከተላቸው ሣይፈልግ ደግሞ የሚተዋቸው አይደሉም። አንድ ሰው የሚፈጽመው ኑዛዜ በሕግ ፊት ውጤት እንዲኖረው ከፈለገ በሕጉ የተቀመጡትን ፎርማሊቲዎች አሟልቶ ኑዛዜውን መፈፀም ይጠበቅበታል። በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ኑዛዜ በሶስት ዓይነት ፎርም ሊፈፀም እንደሚችል ይደነግጋል።

ይኸውም

በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ /Public will/

በተናዛዡ ጽሑፍ የሚደረግ ኑዛዜ / Holographic will/

በቃል የሚደረግ ኑዛዜ /oral will / ናቸው።

ሀ/ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ

በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ /Public will/ ስሙ ራሱ እንደማየመለክተው አነድ ሰው ኑዛዜውን ሲፈጽም ሌሎች ሰወች /እማኞች ባሉበት የተደረገ በዚህም ምክንያት ለአካባቢው ሕብረተሰብ ግልጽ የሆነ /will made in the presence of the public/ ማለት ነው።በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሚከተሉትን ሁኔታዎች አሟልቶ መገኘት አለበት።

ተናዛዡ እየተናገረ ተናዛዙ የሚናገረውን ማናቸውንም ቃል ሣይቀንስ ወይም ሣይለውጥ ሌላ ሰው የጸፈው ወይም ተናዛዡ ራሱ የጸፈው መሆን አለበት።

ኑዛዜው በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት መነበብና ኑዛዜው የተደረገው አራት ምስክሮች ባሉበትና በመጨረሻም በተናዛዡና በምስክሮቹ ፊት የተነበበ መሆኑን መግለጽ አለበት።

ኑዛዜው የተጻፈበትን ቀን ማመልከትና ተናዛዡና ምስክሮቹ ወደያውኑ ፊርማቸውን ወይም የአውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረግ እንደሚገባቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 ይደነግጋል።

በግልጽ የተደረገው ኑዛዜ የሚፈፀመው አንድ ዳኛ ወይም ውል የማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ከሆነ ለኑዛዜው ዋጋ ማግኘት የሁለት ምስክሮች መገኘትና የኑዛዜውን ጽሑፍ ተነብቦላቸው መፈረማቸው በቂ እንደሆነ የሕጉ ድንጋጌዎች የሚያመለክቱ ሲሆን በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ምስክር የሚሆኑ ሰዎች አካለ መጠን ያደረሱ በፍርድ ወይም በሕግ ያልተከለከሉ ምስክሮቹ ኑዛዜው የተጻፈበትን ቋንቋ ለማወቅና የተጻፈውንም ለመስማት ወይም ለማንበብ ችሎታ ያላቸው መሆን እንዳለባቸውና እነዚህ ሁኔታዎች ሣይሟሉ ኑዛዜው ተፈጽሞ ቢገኝ ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 883 ይደነግጋል። በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜን አስመልክቶ በሕጉ የተመጡት የአፈጻጸም ስርዓቶች ብናያቸው እጅግ በጣም ጥብቅ ናቸው። መስፈርቶቹም ኑዛዜውን ይዘት ተናዛዡና ምስክሮቹ እንዲያውቁት የሚያደርግና ለተናዛዡም ሆነ ምስክሮቹን የኑዛዜውን ይዘት እንዳያውቁ የሚያደርግ ለምሣሌ ኑዛዜው ለምስክሮቹ ካልተነበበላቸው ኑዛዜው ተናዛዡም ሆነ ምስክሮቹ በማያውቁት ቋንቋ የተጻፈ ከሆነ ፈራሽ እንደሚሆን የሚደነግጉ ናቸው።

እዚህ ላይ ኑዛዜው በሌላ ቋንቋ ተጽፎ ለተናዛዡና ለምስክሮቹ በአስተርጓሚ እየተተረጐመ ቢፈፀም ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። የኑዛዜው ፎርም በሕግ መደንገግ የሚያስፈልገው ኑዛዜው የተናዛዡን ፍላጐትና ሀሣብ አሚልቶ መገኘቱን ለማረጋገጥ ነው። ስለዚህ በአስተርጓሚ የሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡ ከማያስበውና ከሚፈልገው ውጭ ለመጨመር ወይም ለመቀነስ ሰፊ በር የሚከፍት በመሆኑ ተፈጽሞ ቢገኝ ፈራሽ እንደሚሆን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 883 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል። ምክንያቱም ሕጉ ምስክሮቹ በመጀመሪያ ኑዛዜው የተጻፈበትን ቋንቋ ማወቅ እንዳለባቸው ይደነግጋል። በሁለተኛ ደረጃ የተጻፈው ሲነበብላቸው ለመስማት ወይም የጽሑፉን ይዘት አንበው ለመረዳት ችሎታ ያላቸው መሆን ት ለባ ው ይደነግጋል። ይህንን መስፈርት በግልጽ በሚደገግ ኑዛዜ የሚች ቃል በሚናገረው ቋንቋ ቃል በቃል መጻፍ እንዳለበት ከሚደነግገው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማጣመር ስናየው ሚች ከአማርኛ እየተናገረ በእንግሊዝኛ ተተርጉሞ ተጽፎ ተናዛዡና ምስክሮቹ ቢፈረሙበት ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ትችላል ለመገንዘብ ይቻላል።

ለማንኛውም በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ዙሪያ የሚቀርቡ ክርክሮች በርካታ ናቸው ለምሣሌ ሶስት ምስክሮች ፊት የተደረገ ኑዛዜ ውጤት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም? ከአራቱ ምስክሮች አንደኛው አካለ መጠን ያላደረሰ ወይም በሕግ የተከለከለ ቢሆን ውጤቱ ምን ይሆናል የሚሉትና ሌሎች በርካታ ጥያቄዎች ይነሣሉ::አንድ ነገር በእርግጠኝነት ለመናገር የሚቻለው የእኛ አገር የውርስ ሕግ ብቻ ሣይሆን የብዙ አገሮች የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች የኑዛዜ ፎርሞች ጥብቅና አስገዳጅ እንዲሆኑ የሚያደርጉት ሚች ኑዛዜ የማድረግ ሀሣብ ኖሮትና ባሚወሰመውት ኑዛዜ ይዘት ተረድቶና አውቆት መሆኑ ለማረጋገጥ ጥብቅ የኑዛዜ አፈጻጸም ስርዓት አስቀምጠ ፎርማሊቲዎቹ መሚላታቸው ከመቆጣጠር ውጭ ሌላ መንገድ ስለሌላቸው ነው:: ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ሕግም በሕጉ ከተቀመጠው አንዱ ካልተሟላ ኑዛዜው ፈራሽ እንደሚሆን ማስቀመጡ ተገቢነት ያለው ነው::

ለ/ በተናዛዡ ጽሁፍ የሚደረግ ኑዛዜ

በእኛ የውርስ ሕግ አንድ ሰው በራሱ የእጅ ጽሑፍ ኑዛዜ እንዲፈጽም ይፈቅዳል:: ተናዛዡ በራሱ እጅ ጽሑፍ ያደረገው ኑዛዜ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው
ተናዛዡ ኑዛዜው ሙሉ በሙሉ በፊርሱ የእጅ ጽሁፍ የጻፈው እንደሆነ
ተናዛዡ የጻፈው ጽሑፍ ኑዛዜ መሆኑን በግልጽ ያመለከተ እንደሆነ
ተናዛዡ የጻፈው ጽሑፍ ኑዛዜ መሆኑን በግልጽ ያመለከተ እንደሆነ
ኑዛዜው ከአንድ ገጽ በላይ ከሆነ ተናዛዡ እያንዳንዱ ገጽ ላይ ከፈረመበትና ቀን የጻፈበት እንደሆነ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 884 ይደነግጋል::

ከዚህ በተጨማሪ ተናዛዡ ያደረገውን ኑዛዜ ራሱ በመኪና ጽፎት እንደሆነና በእያንዳንዱ ቅጠል ራሱ በመኪና የጻፈው መሆኑን በእጅ ጽሑፍ ካመለከተ ውጤት እንደሚኖረውና ይህንን ካላደረገ ግን ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 885 ይደነግጋል::
እንደዚሁም በተናዛዡ እጅ ጽሑፍ የሆነው ኑዛዜ ተናዛዡ ያልተማረ ማህይም በመሆኑ ወይም ኑዛዜውን የተጻፈበትን ቋንቋ ካላወቀው ወይም ፍቻቸውን በማያውቃቸው ፊደሎች ጽፎ ቢገኝ ፈራሽ እነደሚሆንና ኑዛዜው የተደረገበትን ቀን ወርና ዓመት ምህረት ማመልከት እንደማገባው ይደነግጋል::

ሐ/ በቃል የሚደረግ ኑዛዜ

አንድ ሰው የሞቱ መቃረብ ተሰምቶት የመጨረሻ ፈቃድ ቃሎቹን በሁለት ምስክሮች ፊት ሊሰጥ እንደሚችልና ይኸም የቃል ኑዛዜ በመባል እንደሚታወቅ የቃል ኑዛዜ በሕግ ውጤት እንዲኖረው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት እንዳለበት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 892 **ይደነግጋል፡፡**

ኑዛዜው ቨተረ ው የመሞቻ ጊዜው መቃረቡን ተሰምቶት መሆን ይገባዋል፡፡ ይኸ ማለት ምንም አይነት የሕመም ስሜት ወይም አደጋ ሣይገጥመው ሟች እኔ ስሞት እከሌ ይህንን ይወስዳል በማለት የሚያወራው ወሬ ሁሉ የቃል ኑዛዜ ነው ተብሎ እንደማይወሰድ '' የመሞቻ ጊዜው መቃረቡ ተሰምቶት'' የሚለው የሕጉ ድንጋጌ ሀረግ፣ ያመለክታል
ለኑዛዜው ያደረገው ቢያንስ ሁለት ምስክሮች ባሉበት መሆን አለበት እንደዚሁም ምስክሮቹ አካለ መጠን ያደረሱ በፍርድ ወይም በሕግ ያልተከለከሉ መሆን አለባቸው፡፡ከዚህ በተጨማሪ በቃል ኑዛዜ ሊደረግባቸው የሚችሉት ጉዳዮች ምን እንደሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 893 **ይደነግጋል፡፡**

ከዚህ ላይ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ነገር ሟች በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ወይም በራሱ እጅ ጽሑፍ ባደረገው ኑዛዜ በርካታ ጉዳዮች አንዲፈፀሙለት መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፣ ይኸም ማለት ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ መሾም ከፍተኛ የዋጋ ግምት ያለውን ንብረቱን በልዩ የኑዛዜ ስጦታ መስጠት፣ ከወራሾቹ አንዱን ወይም ሁሉንም ከውርስ መንቀል እና ሌሎች ጉዳዮችን አስመልክቶ ኑዛዜ መተው ይችላል፡፡በቃል ኑዛዜ ሊያካትታቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ግን በሕግ ገደብ ተደርጐበታል፡፡

ሟች በሚያደርገው የቃል ኑዛዜ ስለ ቀብሩ ሥነ ሥርዓት መመሪያ መስጠት የእያንዳንዱ የስጦታ ዋጋ ከብር 500 **ለመብለጥ ሣይችል ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ማድረግ አካለ መጠን ላለደረሱ ልጆች ሞግዚት ወይም አስተዳዳሪ መሾም እንደሚችል የሕጉ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ሟች በቃል ኑዛዜ ከነዚህ ውጭ የሆነ ነገር ቢናገር ለምሣሌ ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ ቢሾም ወይም ከወራሾቹ አንዱ ከውርስ እንዲነቀል ቢናዘዝ ውጤት እንደማይኖረው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥርግ** 894/1/ **የሚደነግግ ሲሆን ሟች በቃል ኑዛዜ ግምቱ** 500 **ብር በላይ የሆነ ስጦታ ቢሰጥ ከዚህ በላይ ያለው ነገር እንደሚቀንስ በፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር** 894/2/ **ተደንግጓል፡፡በአጠቃላይ በቃል የሚደረግ ኑዛዜ ሟች ሁለት ምስክሮቹ ባለበት ከሞተ በኋላ ስለሚፈፀሙ ነገሮች የሰጠውን ቃል የሚመለከቱ**

በመሆናቸውኛ ከሚች ቃል ሊረሣ ወይም ሊጨመርበት የሚችሉበት አጋጣሚ ሰፊ በመሆኑ ሕጉ በቃል ኑዛዜ ሊካተቱ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ገደብ በመጣል በዚህ በኩል ሊመጣ የሚችለውን ችግር ለመቀነስ ጥንቃቄ አድርጓል፡፡ በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ከሶስቱ በአንደኛ ፎርም የሚጠይቀውን ሁኔታ ሣያሟላ የተፈፀመ ኑዛዜ እውቅና የማይሰጥና ኑዛዜውም ዋጋ እንደማይኖረው በኑዛዜ ፎርም ጥብቅና አስገዳጅ መሆኑን ፎርሙን አለማሟላት ኑዛዜውን ፈራሽ ሊያደርገው እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ስለ ኑዛዜ የተደነገጉት የውርስ ሕግ የሕግ ድንጋጌዎች በፍርድ ቤቶች የሚሰጣቸውን ተርጓሜ ፍርድ ቤቶች ከሰጧቸው ውሣኔ አንጻር መመልከቱ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዳኝነት በቆየሁባቸው ዘመናትና ካነበብኳቸው የፍርድ ቤት ውሣኔዎች የተረዳሁት ኑዛዜን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮች አብዛኛቻቹ ዙዛዜው የሚች አይደለም? ኑዛዜው ላይ ያለው ጽሑፍ ወይም ፊርማ የሚች አይደለም? የሚሉ የክደት ክርክሮች ከሚች የስጋ ወራሾች በኩል እንደሚቀርቡና ፍርድ ቤቶችም የእጅ ጽሑፍ ወይም ፊርማው የሚች መሆኑን ለማረጋገጥ ለፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ክፍል በመላክ ይኸ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ኑዛዜው ሲደረግ ምስክር የሆኑ ሰዎችን ቃል በመስማት ውሣኔ እንደሚሰጡ በርካታ አብነቶችን በማንሣት ለማየት ይቻላል፡፡

ይኸም ኑዛዜው የሚች የይደለም ወይም ኑዛዜው ጽሑፍ ወይም ፊርማ የሚች አይደለም የሚል ክርክር በሚቀረብ ጊዜ ኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሚች መሆኑን ለማረጋገጥ ምን አይነት ማስረጃ ነው መቅረብ ያለበት የሚለውን ነጥብ ለመገንዘብ የሚረዳ ይሆናል፡፡ ይህንን አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1207ሐ88 ጥቅምት 6 ቀን 1993 ዓ.ም በይግባኝ ባይ በወሐሮ ደመቀች ልባሴ እና በመለስ ሰጭዎች በእነ ሻንበል ባሻ ተዘራሽ ሙሉነህ መካከል የነበረውን የይግባኝ ክርክር አይቶ የሰጠው ውሣኔ በአጭሩ ማየቱ ይጠቅማል፡፡ የክርክሩ መነሻ የሆነው የሚች ሙሉነህ ተክለወልድ ሚስት ነኝ የምተለው ይግባኝ ባይ ወሐሮ ደመቀች ሰኔ 2 ቀን 1980 ዓ.ም ከዚህ ዓለም የተለየው ባለቤቱ ኑዛዜ የተወልኝ ሰለሆነ የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ ይጽናልኝ በማለት ጉዳዩን በመጀመሪያ ለሚያየው ፍርድ ቤት ያቀረበችው ማመልከቻ ሲሆን መልስ ሰጭዎች በተቃዋሚነት ቀርበው አባታችን 1976 ዓ.ም ጀምሮ ማየት ስለማይችል ኑዛዜ ይጸናልኝ በማለት ያቀረበችው ሰነድ የሀሰት ሰነድ ነው፡፡ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የአባታችን ስላልሆነ ይመረመርልን በማለት ክርክራቸውን አቀረበዋለ፡፡ ጉዳዮን በመጀመሪያ ያየው የአራዳ አውራጃ ፍርድ

ቤት ኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች ፊርማ ስለመሆኑ ተመርምሮ ውጤቱ እንዲቀርብ ለፖሊስ ቴክኒክ ምርመራ ክፍል ትዕዛዜው ላይ ያለው ፊርማም ሆነ ለማመሣከሪያ የተላከው ፊርማ የተበላሸ ስለሆነ ፊርማው የእገሌ ነው ብለው ለመለየትና ለማረጋገጥ አልቻልንም በማለት ምላሽ ሰጥቷል፡፡

የአውራጀው ፍርድ ቤት ወሐሮ ደመቀች የሟች ሚስት ስለመሆኗና ሟች ኑዛዜ ያደረገላት ስለመሆኑ አራት ምስክሮችን ከሰማ በኋላ የሟች ሚስት መሆኗን በኑዛዜ ካረጋገጠ በኋላ ኑዛዜውን በተመለከተ ሟች የፈረመበት ስለመሆኑ ግልጽ ሆኖ በቴክኒክ ምርመራ ያልቀረበ ስለሆነ ወሐሮ ደመቀች የሟች የኑዛዜ ወራሽ አይደለችም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ባይ በዚህ ውሣኔ ይግባኝ ብሎ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን ብታቀርብም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 872 እና 938ሐ1ሐ የሚቃረን በመሆኑ ይግባኙን አልተቀበልነውም በማለት የአውራጃው ፍርድ ቤት በውሣኔው ከሰጠው የተለየ የሕግ ምክንያት በመጥቀስ የይግባኝ ባይን ይግባኝ ውድቅ አድርጐታል፡፡ ይግባኝ ባይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ባለመቀበል ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርባለች፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተለያየ ምክንያት በመስጠት የአውራጃው እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ የሚከተለውን ትችት በመስጠት ሽሮታል፡፡

ጓከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው የፖሊስ የቴክኒክ የምርመራ ውጤት ፊርማው የሟቹ ነው አይደለም ለማለት አንችልም ከማለት ውጭ በግልጽ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ ይህም በመሆኑ ሟች ኑዛዜው ላይ ሲፈረሙ የነበሩና በኑዛዜው ላይ በምስክርነት የተጠቀሱት ምስክሮች ቀርበው በኑዛዜው ላይ ሟች መፈረማቸውን አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም ፊርማው የሟች ለመሆኑ በቴክኒክ ምርመራ ለማረጋገጥ ባይቻልም በኑዛዜው ወቅት ነበርን የሚሉ ምስክሮች የሰጡት ቃል ሲመዘን ዋጋ ያለው ሆኖ በመገኘቱና ማስተባበያ ማስረጃም ያልቀረበበት ስለሆነ ኑዛዜው የሟች ኑዛዜ ነው ለማለት ተችሏል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የይግባኝ ባይ የኑዛዜ የጽደቅልኝ ጥያቄ ኑዛዜው ሕገ ወጥ ነው በማለት ውድቅ ማድረጉ አግባቡ ስላልሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348ሐ1ሐ መሠረት ሽረነዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ አስተያየት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገቢነት ያለው ነው። ኑዛዜን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮች ሟች ከሞተ በኋላ የሚቀርቡ በመሆናቸው የሟች የስጋ ዘመዶችና የሕግ ወራሾች የተለያየ ምክንያት እየፈጠሩ የሟችን ኑዛዜ በመቃወም ሙሉ ውርሱን ለመውሰድ ይጥራሉ። አንድ አንድ ጊዜ የሟች የማመሣከሪያ ፊርማዎች አንዳይገኙ ለማድረግ ሰነዶችን ሆነ ብለው በመቅደድ በማቃጠልና በማበላሸት ለቴክኒክ ምርመራ አሰፈላጊ የሆነውን የማመሣከሪያ ፊርማ የሚያጠፉበት ወይም የሚያበላሹበት ሁኔታ ያጋጥማል። እንደዚሁ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በኑዛዜው ለይ ስማቸውና ፊርማቸው በምስክርነት የተገለጹት ሰዎች ሟች በኑዛዜ ሰነዱ ላይ ፊርማ የፈረመ ስለመሆኑ በአጥጋቢ ሁኔታ ካስረዱ የሟችን ኑዛዜ ውድቅ ማድረግ ሟቹ ከሞተ በኋላ ንብረቱን ለማስተላለፍ አስቦ የፈፀመውን ተግባር ያለ ምክንያት ህጋዊ ውጤት እንዳያገኝ ማድረግና የሟች የሕግ ወራሾች የሟችን የኑዛዜ ጽሑፍና ፊርማ ወይም ለማመሣከሪያ የሚሆኑ ሰነዶችን ሆነ ብለው እያጠፉ እና እያበላሹ የሕግ ወጥ ተግባራቸው ፍሬ እንዲሰበሰቡ በፍቃድ ጭምር ሆኖል። በመሆኑም ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስረጃውን የመዘነበትና የተቀበለበት አግባብ የሟችን ኑዛዜ እና ፍቃድ ከማስፈፀም አንጻር ፍርዱ ብዙ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ሌላው በኑዛዜ ዙሪያ የሚደረጉ ክርክሮች የኑዛዜ ፎርሞችን መነሻ ያደረጉ ናቸው። ከዚህ በፊት እንዳየነው ሟች ኑዛዜው በሕግ ፊት ውጤት እንዲኖረው ከፈለገ በሕጉ መሟላት አለባቸው የተባሉ ፎርሞችን በማሟላት ኑዛዜውን ማድረግ አለበት። እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ ሟች በሕጉ ከተገለፀው ፎርም አንዷን እንኳን መስፈርት ባያሟላ ምን ይሆናል የሚለው ነጥብ ነው።

በዚህ ዙሪያ የሚነሱ ክርክሮችንና የሚሰጡ ውሣኔዎችን ለመረዳት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1152 ሚያዝያ 19 ቀን 1993 ዓ.ም በይግባኝ ባዩ በአቶ ገብረየስ አርፍቶ እና በመልስ ሰጭ አፀደ ተፈራ መካከል የቀረበውን ክርክር ሰምቶ የሰጠውን ውሣኔ ማየቱ ለግንዛቤ ይረዳል። ክርክሩ የተነሣው ይግባኝ ባይ ሟች እናቴ ወሐሮ ለተየሰ መካሻ መሆኔ ይረጋገጥ በማለት በወቀቱ ለነበረው ለአውራጃው ፍርድ ቤት በማመልከቱ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተቃዋሚ ስላልቀረበ ምስክሮችን ሰምቶ ኑዛዜውን አጽድቋል። በዚህ በኋላ መልሰ ሰጭ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሠረት ውሣኔው ላይ ሟች የተናዘዘችበት ንብርት የሟች ሣይሆን የእኔ አባት ቤት ስለሆነ ውሣኔው ይሠረዝልኝ

በማለት ውሣኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት በማመልከቷ የአውራጃው ፍርድ ቤት ሚች የተናዘዘችበት ቤት የተቃዋሚዋ ሐመልስ ሰጭሐ አባት ቤት ስለሆነ መጀመሪያ የሰጠሁትን ውሣኔ ሽሬዋለሁ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን ይግባኝ ባይ የአውራጃው ፍርድ ቤት ጉዳዮን በድጋሚ አይቶ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የፊተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የቀረበው ኑዛዜ በሚች የእጅ ጽሑፍ የተደረገ ኑዛዜ ሣይሆን በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ ነው፡፡ ሆኖም ኑዛዜው የተደረገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881ሐ2ሐ በሚደነግገው መሠረት በአራት ምስክሮች ፊት ሣይሆን በሶስት መስክሮች ፊት ስለሆነ በሕጉ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አላሟላም በማለት የአውራጃው ፍርድ ቤት የሰጠውን ምክንያት ለውጦ ኑዛዜው አይፀናም የሚለውን የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

ይግባኝ ባዩ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም የይግባኝ ባይነና የመልስ ሰጭን ክርክር ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሣኔ ይህ ፍርድ ቤት መዝገቡን ከሕጉ ጋር መርምሯል፡፡ ይህንን ጉዳይ ለመወሰን መልስ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ ኑዛዜው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881ሐ1ሐ መሠረት ፈራሽ ነው መባል ይገባዋል ወይስ አይገባውም የሚለው ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881ሐ1ሐ እና 2 እንደተመለከተው ተናዛዡ እየተናገረ ማናቸውም ሌላ ሰው በተናዛዡና በአራት መስክሮች ፊት ካልተነበበና ይኸው ስርዓት ሐፎርማሊቲሐ መፈፀምንና የተፈፀመበትን ቀን የሚያመለክት ካልሆነ በቀር ፈራሽ ነው፡፡ ወደዚህ ጉዳይ ስንመለስ ኑዛዜው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተመለከተውን ፎርም አላሟላም፡፡ ኑዛዜው የተደረገው በአራት መስክሮች ፊት ነው የሚል ክርክር በይግባኝ ባይ በኩል አልቀረበም፡፡፡ በኑዛዜው ላይ በምስክረነት የተጠቀሱት ሶስት ሰዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት ነው የሚል ክርክር በይግባኝ ባይ በኩል አልቀረበም፡፡ በኑዛዜው ላይ የምስክርነት የተጠቀሱት ሶስት ሰዎት ናቸው፡፡ ስለዚህ ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት አለመደረጉ አላከራከረም፡፡ ይህ ማለት ኑዛዜው የተደረገው በአራት ምስክሮች ፊት ሣይሆን በሶስት ምስክሮች ፊት ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ የተጠቀሰው ኑዛዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881ሐ2ሐ መሠረት ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ ስላለሆነ ይግባኝ የቀረበበት ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 881ሐ1ሐ መሠረት ፀንቷልቃ በማለት ወስኗል፡፡

እዚህ ላይ የአንድ ምስክር ኑዛዜው ሲደረግ አለመኖር የኑዛዜውን ፈራሽነት ማስከተሉ ምን ያህል ሚዛናዊና ፍትሐዊ ነው የሚለውን ክርክር የሚያነሡ ሰዎች አሉ፡፡ ሆኖም ዳኞች በሕጉ በግልጽ የተቀመጠውን ድንጋጌ ሥራ ላይ የማዋል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ዳኞች ሕግ የሚተረጉሙት የሕጉ ድንጋጌ ግልጽ ካልሆነ ወይም ከፍተት ያለበት ሲሆን እንጅ በሕግ የተገለፀውን ሁኔታ በርትዕና ሚዛናዊነት ሰበብ ሊጋፉት አይገባም፡፡ በአጭሩ ዳኞች ሕግ ሊተረጉሙ እንጅ በሕግ መተርጎም ሰበብ ሕግ እንዲያወጡና ሕግ አውጭው በግልጽ ያስቀመጠውን የሕግ ድንጋጌ እንዲሽሩ አይፈቀድላቸውም፡፡ በሌላ በኩል የኑዛዜ ፎርሞች አለመሟላት ጥብቅ የሆነ አፍራሽ ውጤት እንደሚያስከትሉ በሕጉ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

ስለዚህ ሟች ኑዛዜው ዋጋ እንዲኖረው ከፊለገ በሕጉ የተቀመጠውን ጥብቅ ስርዓት አሟልቶ ኑዛዜውን መተው አለበት፡፡ በመሆኑም የፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 881ሐ1ሐ አለመሟላት ምክንያት በማድረግ በከፍተኛው ና በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ የኑዛዜ ፎርም የሚደነግጉ ድንጋጌዎች አስገዳጅና ጥብቅ መሆናቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ የተሰጡ ሆነው አግኝቸዋለሁ፡፡ ሌላውን በተኩረት መታየት ያለበት የኑዛዜ ፎርም አለመሟላት አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍሐመሐቁ 292 የካቲት 16 ቀን 1993 ዓ.ም ይግባኝ ባይ በአቶ አፍወርቅ ደምሴና መልስ ሰጭ በወሐት እጅግአየሁ ደምሴ መካከል የሰጠውን ውሣኔ ማየቱ የኑዛዜ ፎርም መሟላት ጉዳይ ኑዛዜውን በሕግ ፊት ዋጋ አንዲኖረው ለማድረግ አስፈላጊና አስገዳጅ እንደሆነ ለመገንዘብ ይጠቅማል፡፡ ተከራካሪዎቹ የሚከራከሩት በሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ነው፡፡ የመጀመሪያው በውርስ ንብረት ክፍፍል ቢሆን ሁለተኛው አቶ አፈወረቅ ደምሴ ሟች እናቴ ወሐሮ ዘነበች ቦጋለ ቤቱንና የቤቱን እቃ እፀነ እንድጠቀምበት በግልጽ ኑዛዜ አውርሣኛለች በማለት ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ ነው፡፡

ጉዳዮን በመጀመሪያ ያየው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይና መልስ ሰጭ የሟችን ንብረት እኩል እንዲካፈል ሲወስን ይግባኝ ባይ የሟች የኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ በማለት ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጐበታል፡፡ ይግባኝ ባይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሟች ለእኔ ኑዛዜ የተውልኝ ስለመሆኑ የሰነድ ማስረጃውን ሣይመረምርና ምስክሮችን ሣይሰማ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚልና በንብረት ክፍሉ በተሰጠው ትዕዛዝ ቅር

በመሰኘት ይግባኙን በጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቅረቡ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ኑዛዜውን በተመለከተ የይግባኝ ባዩን ሁለት ምስክሮ በማስቀረብ ሰምቷል። ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ምስክሮችን ሲሰማ ከምስክሮቹ አንደኛው አቶ ታደሠ በርቄ የተባለው ሟች ኑዛዜ ስታደረግ በቦታው የነበረው መሆኑን ገልጾ ነገር ግን በኑዛዜው ላይ እንዳልፈረመና በእሱ ስም ፊት ለፊት ያለው ፊርማ የእሱ እንዳልሆነ እሱ በጣት አሻራ ካልሆነ በስተቀር ማንበብና መጻፍ ስለማይችል በጽሑፍ መፈረም እንደማይችል አስረድቷል።

ጉዳዮን ካዩት ሁለት ዳኞችም ኋይህ የሟች ኑዛዜ የተባለው በሕግ ፊት የፀና እንዲሆን ሕጉ የሚለውን አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል። በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሟችና የአራት ምስክሮች ፊርማ መኖር አለበት። በኑዛዜው ላይ የአራት ምስክሮች ስምና ፊርማ በግልጽ ይታያል። ይሆን እንጅ በኑዛዜው ላይ ስማቸው በአራተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት አቶ ታደሰ ብርቄ ኑዛዜውን ተመልክተው በስማቸው ፊት ለፊት ያለው ፊርማ የእሣቸው አለመሆኑን በዕለቱም በኑዛዜው ላይ አለመፈረማቸውን መጻፍም ሆነ ማንበብ አለመቻላቸውን ገልፀው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል። ምስክሩ ፍርድ ቤት ቀርበው በዚህ መልክ እያስረዱ ፊርማው የምስክሩ ፊርማ ነው ተብሎ የሚወሰድበት ምክንያት የለም። ስለዚህ ይግባኝ ባይ የሟች ኑዛዜ ነው በማለት በማስረጃነት ያቀረቡት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት ፎርማቱን ጠብቆ ያልተዘጋጀ መሆኑ ስለተረጋገጠ የስር ፍርድ ቤት ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም በማለት የወሰኑ ሲሆን ሶስተኛው ዳኛ በበኩላቸው በውሣኔው ባስቀመጡት የሐሣብ ልዩነት፣ ኋግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የወሐሮ ዘነበች ቦጋለ ኑዛዜ ሕጉ የሚጠይቀውን መሰፈርት ያሟላ መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ ሲመረመር አንዱ ምስክር ያልፈረመበት መሆኑን የመሠከረ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቦታው ተገኝቶ ኑዛዜ ሲደረግ የሰማ መሆኑን መስክሯል። የኑዛዜውን ይዘትና የተናዘዙበትን ሁኔታ አስመልክቶ ከሌሎች ምስክሮች ጋር የሚስማማ መልኩ መስክሯል። የምስክሮች ቃል ከኑዛዜው ጋር በይዘቱ የተስማማ ነው ነገር ግን የቀረበው ኑዛዜ ተናዛዥዋ ያአውራጣል ምልክታቸውን አድርገውበታል ተብሎ የቀረበ ቢሆንም ያውራጣት ምልክት ነው ተብሎ የተቀመጠው ምልክት በእስክርቢቶ የተሞጫጨረ እንጂ በእርግጥም የጣት አሻራ አለመሆኑን በአይን ስመለከተው በግልጽ ለይቸዋለሁ። ስለዚህ እንደብዙሀኑ ድምጽ ምስክረ አልፈረመበትም

በሚል ብቻ ሣይሆን ተናዛዥዋ የአውራጣት ምልክታቸውን ያላደረጉበትም በመሆኑ ጭምር ኑዛዜው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881ሐ3ሐ ላይ የተመለከተውን መስፈርት ስላላሟላ ከብዙሀኑ ደምጽ በአካሄድ ብቻ በሐሣብ ተለይቻለሁ በማለት ወስነዋል፡፡ቃ

ከላይ ካነሣናቸው በፍርድ ቤት ታይተው ከተወሰኑ ጉዳዮች የምንረዳው አንድ ኑዛዜ በሕግ ማሟላት የሚገባውን ፎርማሊቲ በተሟላ ሁኔታ ካላሟላ ፈራሽ እንደሚሆን ነው፡፡ ምክነየቱም ሕጉ የኑዛዜ ፎርም አስመልክቶ ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች እጅግ ጥበቅና ተናዛዡ በሕይወት ዘመኑ የሚያደርገው ኑዛዜ ከሞተ በኋላ ውጤት እንዲኖረው ከፈለገ ሊከተላቸው የሚገቡ አስገዳጅ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ተናዛዡ ሕጉ ካስቀመጠው ፎርም አንዷን ሣያሟላ የሚተወው ኑዛዜ ፈራሽ አንደሚሆን አውቆም ሆነ ማየውቅ የሕጉን ፎርማሊቲ አንዷን እንኳን ሣያሟላ ኑዛዜ ጥሎ ካለፈና በዙዛዜው ተፈጻሚነት ክርክር ከተነሣ ኑዛዜው ፈራሽ ይኖንበታል፡፡ ሰለዚህ የኑዛዜ ፎርም ለኑዛዜ በሕግ ፊት ዋጋ መሃር እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ይገባናል፡፡

5.3.3 ኑዛዜው ያልተሻረ ወይም ውድቅ ያልሆነ መሆኑ

አንድ ኑዛዜ በሕጉ የተደነገጉትን የሥረ ነገር ሁኔታዎች አሟልቶ መገኘቱና በሕጉ በተደነገገው ፎርም መሠረት መፈፀሙ ብቻውን ሟች በሞተ ጊዜ ኑዛዜውን ውጤት ለማሰጠትና ለማስፈፀም አያስችልም፡፡ በሕጉ የተደነገጉትን የሥረ ነገር ሁኔታዎች በሟሟላት ሕጉ በሚደነግገው ፎርም መሠረ የተፈፀሙ ኑዛዜ ዋጋ የሚኖረው ሟች ኑዛዜውን ያልሻረው ወይም ኑዛዜው ውድቅ ያልሆነ እንደሆነ ነው፡፡

እዚህ ላይ መታየት ያለበት የኑዛዜ መሻር እና የኑዛዜ ውድቅ መሆን አንድና ተመሣሣይ አለመሆናቸው ነው፡፡ የኑዛዜ መሻርና Revocation of will የኑዛዜ ውድቅ መሆን /Lapse of will/ በተለይ በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ውስጥ የተለያዩ ጽንሰ ሀሣቦች ናቸው፡፡

5.3.3.1 የኑዛዜ መሻር/ Revocation of will/

የኑዛዜ መሻር የሚለውን ጽንሰ ሀሣብ ብዙ የሕግ ሙሁራን በብዙ መንገድ ይተረጉሙታል። የኑዛዜ መሻር የሚለው ስንጸ ሀሣብ ተናዛዡ ኑዛዜውን ካደረገ በኋላ ያደረገው ኑዛዜ ውጤት እንዳይኖረው አስቦ የሚፈጽመውን ማናቸውንም ድርጊት አጠ ቃለን ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው። ለግንዛቤአችን ይረዳን ዘንድ በ /Blackes Law Dictionary/ የተሰጠውን ትርጉም ብንመለከት፣' Revocation of will is recalling, annulling or rendering in operative of an existing will by some subsequent act of the testator which may be, by making a new will inconsistant with the terms of the first, or by destroying the old will or by disposing of the property to which it is related or other wise በማለት ይተረጉመዋል።ኑዛዜ በማናቸውም ጊዜ በተናዛዙ የሚሻር ተግባር መሆኑ ይኸም የኑዛዜ አይነተኛ ባህሪ መሆኑን አይናል። ሆኖም ኑዛዜ መሻር የራሱ የሚከተሉት ልዩ ባህሪያት አሉት።

- ኑዛዜ ለመሻር በመጀመሪያ በሕግ ፊት ውጤት ያለው ኑዛዜ መኖር ይኖርበታል። ምክንያቱም ማንም ቢሆን የሌለን ኑዛዜ ለመሻርና ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው ለማድረግ አይችልም።
- ኑዛዜው መሻር የሚችለው ኑዛዜውን ያደረገው ሰው ብቻ ነው። ኑዛዜ የመሻር ተግባር በውክልና የሚሠራ ተግባር አይደለም። በመሆኑም ኑዛዜውን ካደረገው ሰው ፈቃድ ውጭ ኑዛዜውን ሌላ ሰው ሊሽረው የማይችል መሆኑ፣
- ኑዛዜውን ለመሻር አንድ ሰው ችሎታ ሊኖረው ይገባል። ይኸ ማለት አንድ ሰው ኑዛዜ ካደረገ በኋላ ችሎታ ካጣ ኑዛዜውን መሻር የማይችል መሆኑ ባትዛዜ መሻር ልብ ባህሪ ነው።
- ተናዛዡ ኑዛዜውን የመሻር ስልጣኑ ኑዛዜየን አልሽርም ብሎ በሚገባው ማናቸውም ስምምነት ወይም ውል ሊገደብ አይችልም። ማናቸውም ኑዛዜን ላለመሻር የሚደረግ ውል በሕግ ፊት ውጤት የማይኖረው መሆኑ

- ተናዛዡ ያደረገውን ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ወይም ከፊፀመው የኑዛዜ ውስጥ ግማሹን ወይም አንዷን ክፍል ብቻ በመሻር ሌላው የኑዛዜ ክፍል ለመተው የሚችል መሆኑ ናቸው።

ተናዛዡ ኑዛዜው የሚሽረው በሁለት አይነት መልኩ እንደሆነ በውርስ ሕግ ዙሪያ የተጻፉ በርካታ ጽሑፎች ያሣያሉ። ይኸም፣ኑዛዜውን በግልጽ በመሻር/ Express Revocation/ እና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚፈፀም የኑዛዜ መሻር Implied Revocation

ናቸው::የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ከላይ ያነሣናቸውን የኑዛዜ መሻር ልዩ ባህሪያትና ኑዛዜ በግልጽና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚሻርበትን ሁኔታ አካትቶ እናገኘዋለን::

ሀ. በግልጽ ኑዛዜን ስለመሻር

በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ተናዛዡ በሁለት አይነት መንገድ ኑዛዜውን በግልጽ ለመሻር ይችላል:: የመጀመሪያው ተናዛዡ ኑዛዜዎቹ ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ በሚያስፈልገው ፎርም ዓይነት ግልጽ አድርጐ በማሣወቅ ኑዛዜውን የሻረው እንደሆነ ነው:: በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 898/1 በግልጽ እነደተመለከተው በዚህ አኳኋን ተናዛዡ ኑዛዜው በግልጽ ለመሻር እንደሚችል ያመለክታል::ሆኖም እዚህ ላይ ኑዛዜዎቹ '' ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ በሚያስፈልገው ፎርም የሚለው አባባል መታየት አለበት:: ይኸ ማለት በቃል የተደረገን ኑዛዜ በቃል ኑዛዜ በግልጽ የተደረገን ኑዛዜ በግልጽ በተደረገ ኑዛዜ በተናዛዡ እጅ ጽሑፍ የተደረገን ኑዛዜ በተናዛዡ እጅ ጽሁፍ በተደረገ ኑዛዜ ፎርም ዓይነት ብቻ ነው መሻር የሚችለው ተብሎ መተርጐም አለበት ወይስ፣ ከዚህ ሰፋ ባለ ሁኔታ በግልጽ የተደረገን ኑዛዜ በእጅ ጽሑፍ በተደረገ ፎርም የሚለው አከራካሪ ነጥብ ነው::

የኑዛዜ መሠረታዊ ባህሪ በተናዛዡ በፈለገ ሠዓት ሊሽረው የሚችለው ከመሆኑ አንጻር በተናዛዡ ኑዛዜውን የመሻር ስልጣን በሚያጣብብ መልኩ የሕጉ ድንጋጌ መተርጐም የለበትም::በዚህአንጻር ስናየው በግልጽ ያደረገውን ኑዛዜ በተናዛዡ እጅ ጽሑፍ ኑዛዜ ለማድረግ ማሟላት የሚገባቸውን ፎርማሊቲዎች አሟልቶ ቀደም ሲል ያደረገውን ኑዛዜ በግልጽ እስከሻረ ድረስ ሟች ከሞተ በኋላ እንዲፈጽም የማይፈልገውን ኑዛዜ የሕጉን ድንጋጌ አጥብቦ በመተርጐም ውጤት መስጠቱ ተገቢ አይሆንም:: በመሆኑም በቃል የተደረገን ኑዛዜ በእጅ ጽሑፍ ወይም በግልጽ በተደረገ ኑዛዜ ፎርሞ በማሟሉት ለመሻር ሌሎቹንም በዚሁ አይነት መንገድ ለመሻር ይችላል የሚል አተረጓጐም የሚከተሉ አሉ:: ሁለተኛው መንገድ ተናዛዡ በግልጽ ቀደም ሲል አድርጐት የነበረውን ኑዛዜ የሚሽርበት መንገድ ከፊተኛው ኑዛዜ ጋር አብሮ ሊፈፀም የማይችል ሌላ ኑዛዜ ያደረገ እንደሆነ ነው::
ብዙ ኑዛዜዎች አንድ ሰው ባደረገ ጊዜ ኑዛዜዎቹ አብረው ተፈጻሚ የማሆኑ ከሆነ አብረው ሊፈፀሙ የሚችሉበት መጠን አብረው ተፈጻሚወች አደሚሆኑና ሁለት ኑዛዜዎች ቃላት ሁለቱም ሊፈፀሙ ያልተቻለ እንደሆነ በኋላ የተደረገው ኑዛዜ ውስጥ ላለው ቃል ምርጫ እንደሚሰጥ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 898 ይደነግጋል:: በመሆኑም በኋላ የተደረገው ኑዛዜ በፊት ከተደረገው ኑዛዜ ጋር የሚቃረን ከሆነ

ተናዛዡ ኑዛዜውን በግልጽ እንደሻረ እንደሚቆጠር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 898/2/ ድንጋጌ ያሣያል። የሌሎች አገር ህጐች በዚህ ዓይነት የሚደረግ የኑዛዜ መሻርን ተግባር በተዘዋዋሪ የተደረገ የኑዛዜ መሻር/implied Rivocation of will/ በማለት የሚሰይሙት ቢሆንም በኢትዮጵያ ውርስ ሕግ ደግሞ ግልጽ የሆነ የኑዛዜ መሻር በሚለው ርእስ እንደተካተተ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 898 ተደንግጓል።

/ለ/ በተዘዋዋሪ መንገድ ኑዛዜን ስለመሻር

ተናዛዡ ኑዛዜውን የሚሽርበት ሌላው መንገድ ኑዛዜዋ ዋጋ አንዳይኖረው የሚያደርጉ ሌሎች ተግባራትን በመፈፀም በተዘዋዋሪ መንገድ በመሻር ነው። ተናዛዡ ኑዛዜውን ለመሻር ወይም ለመለወጥ ያለውን ሀሣብ በቂ አድርጐ በመግለጽ አይነት ኑዛዜውን ራሱን በማጥፋት በመቅደድ የኑዛዜውን አነጋገር በመሠረዝ ኑዛዜውን ወይም ኑዛዜው ውስጥ የተመለከተውን አንድ ቃል ለመሻር ይችላል።ተናዛዡ በሕግ የሚፀና ኑዛዜ ካደረገ በኋላ ከላይ የተጠቀሱትን ግዙፍ ተግባራት / Physical act/ ባደረገው ኑዛዜ ላይ ከፈፀመ ኑዛዜውን እንደሻረ እንደሚቆጠርና ተናዛዡ እነዚህን የህይል ተግባራት በፈፀመ ቁጥር ኑዛዜውን የመሻር ፍላጐት አለው ተብሎ እንደሚገመት እንደዚሁም የኑዛዜው መጥፋት ወይም መሠረዝ የተናዛዡ ተግባር ነው ተብሎ እንደሚቆጠር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 899/2እና 899/3/ ባሚደነግጉ ሲሆን በእነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች የተቀመጠ የሕግ ግምቶች ሊስተባበሉ የሚችሉ የሕግ ምቶች በመሆናቸው ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ለማስተባበልና ሚች ኑዛዜውን ያልሻረው መሆኑን ለማስረዳት እንደሚቻል መገንዘብ ይገባል። ሌላው ተናዛዡ ኑዛዜውን በተዘዋዋሪ የሚሽርበት መንገድ በኑዛዜ የተሰጠን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ተናዛዡ ፈቅዶ ለሌላ ሰው ያስተላለፈው እንደሆነ ነው። እዚህ ላይ ንብረቱን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚለው ተናዛዡ በስጦታ ወይም በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ የንብረቱን የባለቤትነት መብት ለሌላ ሰው ያስተላለፈው እንደሆነ ነው።

ተናዛዡ በኑዛዜ ውስጥ በስጦታ የሰጠውን ንብረት ባለቤትነት የሌላ ሶስተኛ ወገን ካስተላለፈ ኑዛዜው ተፈጻሚ እንዳይሆን ግልጽ ሀሣብ ያለው መሆኑን ስለሚያሣይ የንብረቱ ባለቤትነት ተመልሶ በእሱ እጅ ቢገባም ተናዛዡ በመጀመሪያ ያደረገው ኑዛዜ ውጤት እንደማይኖረው እና ኑዛዜውን በተዘዋዋሪ መንገድ እንደሻረው እንደሚቆጠር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 900 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል። እንደዚሁም ኑዛዜውን የሻረው ኑዛዜ በድጋሚ መሻሩ የበፊቱን ኑዛዜ እንዲሠራ /ዋጋ እንዲኖረው አያደርግም/።

አንድ ኑዛዜ ዋጋ የሚኖረው ተናዛዙ በህይወት ዘመኑ በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ያልሻረው ሲሆን ብቻ መሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነጥብ ነው::ጭጠሦንወንሕኃ ቅኞ ለፌኃ 899 ቃኞኸጽ ዓቃከዋ 2 ኋ 3 ልያ ኞዕከኴኸሦ ኞቅኞ ኞጋሩዮ ኞጸኸቄዛሕ ፉነትሸኣኸቃ ኞትጵጸዱሦ ገቆጋ ኞትሸጫጸኞኞኋ ጸኸቄዛሕፓዮቃ ትቃ ዏኸዩኣኸ ኣያጋ ቸጸቄዩኣኸ ኞትሸክኣኸቃ ሙኸዱያ ኞዕኋቄሂ ፅኞቨኃ ቃጫጅጸ ኞቅኞ ኞጋሦ ኞትሸዴጵከጐኸኋ ቆጠፅጎቃ ኞትሸቨክኸ ኋዩኣኸዕዕፅ

5.3.3.2 **የኑዛዜ ውድቅ መሆን**/Lapse of will/

የኑዛዜ ውድቅ መሆን ወይም /Lapse of will/ **የሚለውን ጽንሰ ሀሣብ ከኑዛዜ መሻር ጋር አንድ አድርጐ የመመልከት ችግር አለ:: በስነ ሕግ ጥናት ውስጥ**

" Lapse" **የሚለው ቃል** The termination or failure of aright or aprivilage through neglect to execrcise it within some limit of time or through failure of some contingence" **ማለት ነው:: የኑዛዜው ውድቅ መሆን ስንል አንድ ኑዛዜ ከተፈፀመ በኋላ ሕጉ በሚያዝዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተናዛዡ ማድረግ የሚገባውን ባለማድረጉ ወይም ተናዛዡ ኑዛዜ ከተፈፀመ በኋላ አንድ ክስተት በመፈጠሩ፣ ኑዛዜው ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው ሕጉ ክልከላ ሲያደርግበት ነው:: ኑዛዜን መሻር በተናዛዡ የሚፈፀም ተግባር ሲሆን ኑዛዜ ውድቅ የሚሆነው ደግሞ በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ግልፅ ትዕዛዝ ነው:: በመሆኑም የኑዛዜ ውድቅ መሆን ምንጩና መሠረቱ የሕጉ ድንጋጌ ነው:: በአጠቃላይ አንድ ኑዛዜ ውድቅ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች የሚያስቀምጠው ሕግ አውጭው ነው:: በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ውስጥ ኑዛዜ ውድቅ ሊሆን የሚችልባቸው በርካታ ምክንያቶች ተቀምጠዋል::የመጀመሪያው ተናዛዡ በሕግ እንዲፈጽም የታዘዘውን ድርጊት ባለመፈፀሙ የሚመጣ ነው:: ኑዛዜው የተደረገው በተናዛዡ የእጅ ጽሁፍ በሆነ ጊዜ ኑዛዜው በተደረገ በሰባት ዓመት ውስጥ ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም ፍርድ መዝገብ ቤት ዘንድ ያልተቀመጠ እንደሆነ ውድቅ ሊሆን እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 907 ይደነግጋል:: ሌሎቹ ምክንያቶች ኑዛዜው ከተደረገ በኋላ የተከሰቱትን ክስተቶች የሚመለከቱ ናቸው:: እነርሱም**

- **ተናዛዡ ኑዛዜ ካደረገ በኋላ ልጅ ከወለደ ወይም አንድ ተወላጅ ተወልዶ በተተኪነት ውርሱን ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆነ**
- **ባል ለሚስቱ ወይም ሚስት ለባሏ ኑዛዜ ካደረጉ በኋላ ጋብቻው በሞት ሣይሆን በሌላ ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ**

- ኑዛዜ የተደረገለት ሰው ከተናዛዡ በፊት የሞተ ወይም ኑዛዜውን ለመቀበል ያልቻለ ወይም ያልፈቀደ እንደሆነ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 902 እና 904 እስከ 907 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያስረዳሉ::

እዚህ ላይ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ሚች ኑዛዜ ካደረገ በኋላ ልጅ ቢወለድም ዳኞች ኑዛዜውን አይተው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 905 ድንጋጌዎች መሠረት ኑዛዜ ቢከፈል ውጤት እንዲኖረው የማድረግ ስልጣን እንዳላቸውና ከተናዛዡ በፊት የሞተው ሰው ጠ ቅላላ የኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሲሆን የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚው ከሚች ቀደም ቢሞትም የእሱ ተተኪዎች በውርሱ ሊካፈሉ እንደሚችሉ እንደዚሁም ኑዛዜ ተጠ ቃሚው ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተደርጐለት ከሆነ ሚች የስጋ ዘመድ ወራሽ በማጣቱ ንብረቱ ለመንግስት የሚገባ በሆነ ጊዜ የልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚው ወራሾች እሱን ተክተው በሚች ውርስ ሊካፈሉ እንደሚችሉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 908 የተደነገገ መሆኑን ነው::

5.4 የኑዛዜ ይዘትና ትርጓሜ

እስካሁን ካደረግናቸው ገለጻዎች አንድ ኑዛዜ ለመፈፀም ችሎታ ያለው ሰው ኑዛዜ የማድረግና ኑዛዜውን የመሻር ሥልጣን እነዳለው አይተናል:: ሆኖም አንድ መመለስ ያለበት አብይ ጥያቄ አለ:: እሱም ተናዛዡ በኑዛዜው ምን ምን ጉዳዮችን ማካተት ይችላል ሚች የተወው ኑዛዜስ እንዴት ይተረጐማል የሚለው ነው::

5.4.1 የኑዛዜ ይዘት /Content of will/

ኑዛዜ ስንል አብዛኛው የተለመደውና በህሊናችን የሚቃጭልብን ተግባር ሚች ከሞተ በኋላ ስለንብረቱ አከፋፈል እና ድልድል የሚሰጠው መመሪያ ነው:: ሆኖም አንድ ሰው በኑዛዜው ሊያካትተው የማገባው ጉዳይ የንብረት ማስተላለፍ ጉዳይ ብቻ ሣይሆን ስለ ቀብሩ ስርዓት አፈጻጸም አካለ መጠን ላላደረሱ ልጆች ሞግዚት ወይም አስተዳዳሪ መሾም፣ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ወራሾቹን ከውርስ መንቀል የውርሱን አጣሪ መሾምና ሌሎች እሱ ከሞተ በኋላ ሊፈፀሙ ስለሚገባቸው ተግባራት በኑዛዜው ውስጥ ማካተት ይችላል:: በአጠቃላይ ሚች የሚከተሉትን ተግባራት በኑዛዜው ውስጥ ለማካተት ይችላል::

ሀ/ <u>ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ማድረግ፣</u>

አንድ ሰው ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ አደረገ የሚባለው አንድ ወይም ለብዙ ሰዎች የሆኑ ሰዎችን ሀብቱን በጠቅላላ ወይም ከመላ ንብረቱ አንዱን ክፍል በባለቤትነት በሙሉ ባለሀብትነት ወይም በሌኃ ርእስትነት የሚያወርስበት የኑዛዜ ቃል ነው::አንድ ሰው ባደረገው ኑዛዜ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ /Legacy by Universal title/ አድርጓል ለማለት

